ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ



አዘጋጅ፦

መ/ር በትረ ማርያም አበባው

የፊደል ግድፈቶች ብዙ ልታገኙ ትችላላችሁ። ስሕተት ብታገኙ እያስተካከላችሁ አንብቡት

በመ/ር በትረ ማርያም አበባው

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

❤ግእዝ ❤ክፍል ❤አንድ

ፊደል

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ለእያንዳንዱ ፊደል ምሥጢረ ሥላሴን እና ምሥጢረ ሥጋዌን የሚገልጡ ትርጉም ሰጥተዋል ። ቸ: ሸ: ቨ: ኘ: ኸ: ዠ: ጀ: ጨ: የግእዝ ፊደላት አይደሉም።

ሀ ብሂል

- ሀልወቱ ለአብ እምቅድመ ዓለም = የአብ መኖር ከዓለም በፊት ነው ማለት ነው።

ሁ ብሂል

- ኪያሁ ተወከሉ ።በእርሱ (በእግዙአብሔር) ታመኑ።

ሂ ብሂል

- አስተይዎ ብሂዐ = አይሁድ ጌታን ሐምጣጤ አጠጡት ማለት ነው።

ሃ ብሂል

- ሃሌ ሉያ ።ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ማለት ነው።

ሄ ብሂል

- በኵለሄ ሀሎ ። እግዙአብሔር በሁሉ ቦታ እና ጊዜ አለ ማለት ነው።

ህ ብሂል

- ህልው እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር አለ ማለት ነው።

ሆ ብሂል

- ኦሆ ይቤ ወመጽአ። እሺ ብሎ መጣ ማለት ነው ።አዳምን ለማዳን እግዙአብሔር በፈቃዱ ሥጋን መዋሐዱን ያመለክታል።

ለ ብሂል

- ለብሰ ሥጋ ዙኣነ ።እግዙአብሔር የእኛን ሥጋ ተዋሐደ ማለት ነው።

ሉ ብሂል

- ሣህሉ ለእግዙአብሔር ። የእግዙአብሔር ይቅር ባይነት ማለት ነው።

ሊ ብሂል

- ከሃሊ እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ማለት ነው።

ላ ብሂል

- ላሜድ ልዑል እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር ልዑል ነው ማለት ነው።

ሌ ብሂል

- መቅለሌ ዕጹብ ። ጭንቀትን (ጭንቅን) የሚያቀል እግዙአብሔር ማለት ነው።

ል ብሂል

- መስቀል ዘወልደ አብ ። የአብ ልጅ መስቀል ማለት ነው።

ሎ ብሂል

- ዘሀሎ እምቅድም ። ቅድመ ዓለም የነበረ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ሐ ብሂል

- ሐመ ወሞተ በእንቲአነ ። ክርስቶስ ስለእኛ መከራን ተቀበለ ሞተ ማለት ነው።

ሑ ብሂል

- ስብሑ ለስመ እግዙአብሔር ። የእግዙአብሔርን ሥም አመስግኑ ማለት ነው።

ሒ ብሂል

- መንጽሒ ። ከበደል የሚያነጻ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ሓ ብሂል

- መፍቀሬ ንሥሓ ። ንሥሓን የሚወድ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ሔ ብሂል

- ሔት ሕያው እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር ሕያው ነው ማለት ነው።

ሕ ብሂል

- ሕያው እግዙአብሔር

ሖ ብሂል

- ንሴብሖ ለእግዙአብሔር ። እግዙአብሔርን እናመስግነው ማለት ነው።

መ ብሂል

- መንክር ግብሩ ለእግዙአብሔር ። የእግዙአብሔር ሥራው ድንቅ ነው ማለት ነው።

ሙ ብሂል

- ሙጻአ ሕግ

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ሚ ብሂል

- ዓለመ ኀታሚ ::ዓለምን የፈጠረ፣ ዓለምን የሚያኖር ዓለምን የሚያጠፋ እግዙአብሔር ነው ማለት ነው::

ማ ብሂል

- ፌማ መንፈስ ቅዱስ :: መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው::

ሜ ብሂል

- ሜም ምዑዜ እግዙአብሔር :: እግዙአብሔር ምዑዜ ነው ማለት ነው::

ም ብሂል

- አምላከ ሰላም :: የሰላም አምላክ እግዙአብሔር ማለት ነው::

ሞ ብሂል

- ሞተ በሥጋ :: በሥጋ ሞተ ማለት ነው::

ሠ ብሂል

- ሠረቀ በሥጋ እምድንግል :: ቃል ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ ማለት ነው::

ሡ ብሂል

- መንበረ ንግሡ::

ሢ ብሂል

- ሢመተ መላእክት :: የመላእክት ሹመት ማለት ነው::

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ሣ ብሂል

- ሣህል ወርትዕ ። ይቅርታና ቅንነት ማለት ነው።

ሜ ብሂል

- ሜሞሙ ለካህናት ። እግዙአብሔር ካህናትን ሾመ ማለት ነው።

ሥ ብሂል

- ንጉሥ እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር ንጉሥ ነው ማለት ነው።

ሦ ብሂል

- አንገሦ ለአዳም ። እግዙአብሔር አዳምን አነገሠው ማለት ነው።

ረ ብሂል

- ረግዐ ሰማይ ወምዘድር በጥበቡ ። በእግዙአብሔር ጥበብ ሰማይና ምድር ረጋ ማለት ነው።

ሩ ብሂል

- በኩሩ ለአብ ። ወልድ የአብ አንድያ ልጁ ማለት ነው።

ሪ ብሂል

- ዘይሰሪ አበሳ ። በደልን ይቅር የሚል እግዙአብሔር ማለት ነው።

ራ ብሂል

- ጌራ መድኃኒት ።

ሬ ብሂል

- ሬስ ርኡስ እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር አለቃ ነው ማለት ነው።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ር ብሂል

- ርግብ መንፈስ ቅዱስ :: መንፈስ ቅዱስ ርግብ ማለት ነው::

ሮ ብሂል

- ፈጠሮ ለዓለም :: እግዙአብሔር ዓለምን ፈጠረው ማለት ነው::

ሰ ብሂል

- ሰብአ ኮነ ከማነ :: እግዙአብሔር ወልድ እንደኛ ሰው ሆነ ማለት ነው::

ሱ ብሂል

- ፋሲልያሱ::

ሲ ብሂል

- ዘይሜሲ ለኩሉ ሥጋ:: ደማዊ ፍጥረታትን ሁሉ የሚመግብ እግዙአብሔር ነው ማለት ነው::

ሳ ብሂል

- ሳምኬት ስቡሕ እግዙአብሔር እግዙአብሔር ምስጉን ነው ማለት ነው::

ሴ ብሂል

- ለባሴ ሥጋ :: ሥጋን የተዋሐደ እግዙአብሔር ቃል ማለት ነው::

ስ ብሂል

- ለብስ ለዕሩቃን :: ለታረዘት ልብስ እግዙአብሔር ነው ማለት ነው::

ሶ ብሂል

- መርሶ ለአሕማር ::

ቀ ብሂል

- ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ = በመጀመሪያ ቃል ነበር ማለት ነው።

ቁ ብሂል

- ጽድቁ ለኃጥእ ።

ቂ ብሂል

- ፈራቂሁ ለዓለም ።ዓለምን የፈጠረ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ቃ ብሂል

- ቃልየ አጽምዕ ። አቤቱ ቃሌን ስማ ማለት ነው።

ቄ ብሂል

- ሰዋቄ ኃጥኣን ።

ቅ ብሂል

- ጻድቅ እግዙአብሔር ። እግዙአብሔር እውነተኛ ነው ማለት ነው።

ቆ ብሂል

- ቆፍ ቅሩብ እግዙአብሔ ። እግዙአብሔር ቅርብ ነው ማለት ነው።

ክፍል 2 ይቀጥላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

❤ግእዝ ❤ክፍል ❤ሁለት

ፊደል

- በግእዜ ቋንቋ በእሳቱ "ሰ" መጻፍ ያለበትን በንጉሡ "ሠ"፣ በዓይኑ "ዐ" መጻፍ ያለበትን በአልፋው "አ"፣ በብዘኃኑ "ኀ" መጻፍ ያለበትን በሀሌታው "ሀ" ወይም በሐመሩ "ሐ"፣ በጸሎቱ "ጸ" መጻፍ ያለበትን በፀሐዩ "ፀ" ከጻፍነው ወይም ካቀያየርነው የትርጉም ለውጥ ስለሚያመጣ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ለምሳሌ ሰአለ፣ ቢልና ሠዐለ ቢል ትርጉማቸው የተለያየ ነው። ሰአለ ለመነ ማለት ሲሆን ሠዐለ ደግሞ ሳለ ማለት ነው። ሠረቀ ወጣ ማለት ሲሆን ሰረቀ ሰረቀ ማለት ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ቃል በየትኛው ፊደል እንደሚጻፍ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል። ቀጥለን ባለፈው ያቋረጥነው የፊደላት ትርጉም እንጽፋለን።

በ ብሂል

- በትሕትናሁ ወረደ ለቤዛ ኵሉ ዓለም። ዓለምን ሁሉ ለማዳን በትሕትናው ሰው ሆነ።

ቡ ብሂል

- ጥበቡ ለአብ። የአብ ጥበቡ ማለት ነው።

ቢ ብሂል

- ረቢ ነአምን ብከ። መምህር ክርስቶስ ሆይ እናምንሀለን ማለት ነው።

ባ ብሂል

- ባዕድ እም አማልክተ ሐሰት። ከሐሰት አማልክት የተለየ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ቤ ብሂል

- ቤት ባዕል እግዙአብሔር እግዙአብሔር ባዕለጸጋ ነው ማለት ነው።

ብ ብሂል

- ብርሃነ ቅዱሳን። የቅዱሳን ብርሃን ማለት ነው።

ቦ ብሂል

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

- አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌሁ። ከእግዙአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ማለት ነው።

ተ ብሂል

- ተሰብአ ወተሠገወ እማርያም እምቅድስት ድንግል። ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰው ሆነ ማለት ነው።

ቱ ብሂል

- መዜራእቱ ለአብ።የአብ ክንዱ ማለት ነው።

ቲ ብሂል

- ተአኪቲ እግዙአብሔር እግዙአብሔር ተመስጋኝ ነው ማለት ነው።

ታ ብሂል

- ታው ትጉህ እግዙአብሔር። እግዙአብሔር ትጉህ ነው ማለት ነው።

ቴ ብሂል

- ከሣቴ ብርሃን። ብርሃንን የሚገልጥ ማለት ነው።

ት ብሂል

- ትፍሥሕት ወሐሴት። ፍጹም ደስታ ማለት ነው።

ቶ ብሂል

- ነአምን ልደቶ ለክርስቶስ። የክርስቶስን መወለድ እናምናለን ማለት ነው።

ነ ብሂል

- ነሥአ ደዌነ ወጸረ ሕማመነ። ክርስቶስ ደዌያችንን ነሣ መከራችንንም ተሸከመ ማለት ነው

ኑ ብሂል

- ዝኅኑ ለባሕር።.

ኒ ብሂል

- ኮናኒ እግዙአብሔር እግዚአብሔር ገዢ ነው ማለት ነው።

ና ብሂል

- መና እስራኤል።

ኔ ብሂል

- መድኃኔ ዓለም። የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ማለት ነው።

ን ብሂል

- መኮንን እግዙአብሔር። እግዚአብሔር መኮንን ነው ማለት ነው።

ኖ ብሂል

- ኖላዊ እግዙአብ ሔር። እግዚአብሔር ጠባቂ ነው ማለት ነው።

ኃ ብሂል

- ኃብአ ርእሶ።

ኆ ብሂል

- እኁዜ አቅርንቲሁ።

ኂ ብሂል

- ዘልማዱ ኂሩት። በጎነት ልማዱ የሆነ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ኃ ብሂል = ኃያል በኃይሉ እግዚአብሔር።እግዚአብሔር ኃያል ነው ማለት ነው።

ጌ ብሂል

- ጌር እግዙአብሔር ቸር ነው ማለት ነው።

ጎ ብሂል

- ጎብስት ለርኁባን። ለተራቡት ጎብስት እግዙአብሔር ነው ማለት ነው።

ኖ ብሂል

- ኖጎተ ገነት ወልድ። የገነት ቁልፍ ወልድ ነው ማለት ነው።

አ ብሂል

- አአኩቶ ወእሴብሖ ለእግዙአብሔር። እግዙአብሔርን ፈጽሞ አመሰግነዋለሁ።

ኡ ብሂል

- ሙጻኡ ለቃል።

ኢ ብሂል

- ለሊሁ ተንሣኢ ወለሊሁ አንሣኢ።ክርስቶስ ራሱ ተነሺ ራሱ አንሺ ማለት ነው።

ኣ ብሂል

- ኣሌፍ ፈጣሬ ኩሉ ዓለም ቀዳማይ ወደኃራዊ።

ኤ ብሂል

- አምጻኤ ዓለማት እግዙአብሔር። ዓለማትን ከአለመኖር ያመጣ የፈጠረ እግዚአብሔር ማለት ነው።

እ ብሂል

- እግዙአብሔር እግዙእ። እግዙአብሔር ጌታ ነው ማለት ነው።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ኦ ብሂል

- እግዙኦ። አቤቱ ጌታ ሆይ ማለት ነው።

ከ ብሂል

- ከሃሊ እግዙአብሔር። እግዙአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ማለት ነው።

ኩ ብሂል

- ዐርኩ ለመርዓዊ። የሙሽራው ሚዛ ማለት ነው።

ኪ ብሂል

- ኪያሁ ንሰብል። እርሱን ጌታን እናስተምራለን። አንድም ስለእርሱ እንሰብካለን።

ካ ብሂል

- ካፍ ከሃሊ እግዙአብሔር። እግዙአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ማለት ነው።

ኬ ብሂል

- ሰባኬ ወንጌል ነዋ በማእከለ አኃው።

ክ ብሂል

- ክብሮሙ ለመላእክት። የመላእክት ክብራቸው ማለት ነው።

ኮ ብሂል

- ዘረዳእኮ ለአብርሃም። አብርሃምን የረዳሀው እግዚአብሔር ማለት ነው።

ወ ብሂል

- ወረደ እምሰማያት። ከሰማያት ወረደ ማለት ነው።

ዉ ብሂል = ጼው ለምድር። የምድር ጨው ማለት ነው።

ዊ ብሂል

- ናዜራዊ። ኢየሱስ ናዜራዊ ነው ማለት ነው።

ዋ ብሂል

- ዋው ዋሕድ እግዙአብሔር። እግዙአብሔር አንድ ነው ማለት ነው።

ዌ ብሂል

- ዛናዌ ትፍሥሕት። ደስታን የሚናገር ማለት ነው።

ው ብሂል

- ሥግው ቃል ። ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው።

ዎ ብሂል

- ቤዘዎ ለዓለም። ዓለምን አዳነው ማለት ነው።

ክፍል 3 ይቀጥላል።

ምንጭ ፦ የሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው መጽሐፈ ግሥ ወሰዋስው ።

❤ግእዝ ❤ክፍል ❤ሦስት

ፊደል

- የመጀመሪያው ፊደል ምሳሌ "ሀ" ግእዝ ይባላል። "ሁ" ካዕብ ይባላል። "ሂ" ሣልስ ይባላል። "ሃ" ራብዕ" ይባላል። "ሄ" ኃምስ ይባላል። "ህ" ሳድስ ይባላል። "ሆ" ሳብዕ ይባላል። ስለዙህ የ"መ" ራብዕ ማን ነው ብትባል "ማ" እያልክ የሁሉንም ማወቅ ይገባህል ማለት ነው።

- አንዳንድ ፊደላት ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ቢመስለንም ግን ልዩነት እንዳላቸው ጠንቅቀን ማወቅ አለብን። ምሳሌ የወ ካእብ "ዉ" ሲሆን ሳድሱ "ው" ነው። የሀ ግእዝ "ሀ" ሲሆን ራብዑ "ሃ" ነው። የአ ግእዝ "አ" ሲሆን ራብዑ "ኣ" ነው። የየ ሣልስ "ዩ" ሲሆን ሳድሱ "ይ" ነው።

- እነዚህንም ካቀያየርናቸው የትርጉም ለውጥ ስለሚያመጡ መጠንቀቅ አለብን። ምሳሌ ሞአ ቢል አሸነፈ ማለት ነው። ሞኣ ቢል ግን አሸነፉ ማለት ነው። ስለዚህ ፊደላት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ክፍል ሦስት የፊደላት ትርጉም እነሆ፦

ዐ ብሂል

- ዐቢይ እግዚአብሔር ። እግዚአብሔር ታላቅ ነው ማለት ነው።

ዑ ብሂል

- በግዑ ለእግዚአብሔር። የእግዚአብሔር በግ ማለት ነው።

ዒ ብሂል = ለሊሁ ሠዋኢ ወለሊሁ ተሠዋኢ። ኢየሱስ ራሱ መሥዋእት አቅራቢ ራሱ መሥዋእት ነው ማለት ነው።

ዓ ብሂል

- ዓይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ። ጌታ ሆይ የሰው ሁሉ ሰውነት አንተን ተስፋ ያደርጋል ማለት ነው።

ዔ ብሂል

- ዐቢይ እግዙአብሔር።

ዕ ብሂል

- ብፁዕ እግዙአብሔር።እግዙአብሔር ብፁዕ ነው ማለት ነው።

ዖ ብሂል

- ሞዖ ለሞት ወተንሥአ። ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ ተነሳ ማለት ነው።

ዘ ብሂል

- ዘኵሎ ይእኅዜ እግዙአብሔር። ሁሉን የያዘ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ዘ ብሂል

- ምርጡዘ ለሐንካስ

ዙ ብሂል

- ናዚዙ። የሚያረጋጋ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ዚ ብሂል

- ዚይ ዜኩር እግዚአብሔር።

ዛ ብሂል

- አኃዛ ዓለም በእራኁ። ዓለምን በመሐል እጁ የያ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ዜ ብሂል

- ሐዋዜ ሕገ እግዙአብሔር። የእግዙአብሔር ሕግ መልካም ነው ማለት ነው።

ዝ ብሂል

- አግአዝ ለአዳም። አዳምን ነጻ አወጣው ማለት ነው።

የ ብሂል

- የማነ እግዙአብሔር። የእግዙአብሔር ቀኝ ማለት ነው።

ዩ ብሂል

- ዕበዩ ለእግዙአብሔር። የእግዙአብሔር ታላቅነት ማለት ነው።

ዪ ብሂል

- መስተስርዪ። ኃጢኣትን የሚያስተሰርይ ማለት ነው።

ያ ብሂል

- አንተ ኬንያሁ።

ዬ ብሂል

- ዐሣዬ ሕይወት። ሕይወትን የሚያድል ማለት ነው።

ይ ብሂል

- ሲሳይ ለርኁባን።

ዮ ብሂል = ዮድ የማነ እግዙአብሔር።

ደ ብሂል

- ደመረ መለኮቶ ምስለ ሥጋነ ወሥጋነ ምስለ መለኮቱ። እግዙአብሔር ወልድ ቃሉን ከሥጋችን ሥጋችንን ከቃሉ አዋሐደ ማለት ነው።

ዱ ብሂል

- ፈዋሴ ዱያን ። ሕመምተኛን የሚፈውስ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ዲ ብሂል

- ቃለ ዓዋዲ።

ዳ ብሂል

- ዳሌጥ ድልው እግዙአብሔር።

ጄ ብሂል

- ዐማዴ ሰማይ ወምድር።

ድ ብሂል

- ወልድ ዋሕድ።

ዶ ፈነወ

- ዋሕዶ ወተሰብአ ።

ገ ብሂል

- ገባሬ ሰማያት ወምድር። ሰማይና ምድርን የፈጠረ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ጐ ብሂል

- ለአስካለ ሕይወት ሐረጉ።

ጊ ብሂል

- ጊዛ ገቢር ለእግዙአብሔር።

ጋ ብሂል

- ጋሜል ግሩም እግዙአብሔር።

ጌ ብሂል

- ጽጌ ቅዱሳን።

ግ ብሂል

- ሐጋጌ ሕግ።

ጎ ብሂል

- ሰርጎሙ ለሐዋርያት።

ጠ ብሂል

- ጠቢብ እግዙአብሔር። እግዙአብሔር ጠቢብ ነው ማለት ነው።

ጡ ብሂል

- ውስጡ ለሰብእ እግዙአብሔር።

ጢ ብሂል

- መያጢሆሙ ለኃጥኣን።

ጣ ብሂል = የውጣ እንተ አሐቲ ሕርመታ።

ጤ ብሂል

- ጤት ጠቢብ እግዙአብሔር።

ጥ ብሂል

- ስሉጥ ወርኡስ እግዙአብሔር።

ጦ ብሂል

- ሦጦ ለመንፈስ ቅዱስ ላእሌነ።

ጸ ብሂል

- ጸራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ።

ጹ ብሂል

- ኮጹ መዓዚ ሰብእ።

ጺ ብሂል

- ሠራጺሁ ለዓለም። ዓለምን የሚቀድስ እግዙአብሔር ማለት ነው ።

ጻ ብሂል

- ጻጻሰ ወንጌል።

ጼ ብሂል

- አክራጼ ኃጢኣት። ከኃጢኣት የሚያነጻ እግዙአብሔር ማለት ነው።

ጽ ብሂል

- ጵርስፎራ። ሥጋ ወደሙ ማለት ነው።

ጶ ብሂል

- ጶሊስ።

ጳ ብሂል

- ጳጋ ወጽድቅ እግዙአብሔር።

ጱ ብሂል

- ገጹ ለአብ።

ጲ ብሂል

- ሐዋጺ ነፍሰ ትሑታን። የትሑታንን ሰውነት የሚጎበኝ እግዙአብሔር ማለት ነው ።

ጳ ብሂል

- ጳዴ ጳድቅ እግዙአብሔር።

ጴ ብሂል

- አእቃጴ ሰኮና።

ጵ ብሂል

- ጽንሑ ተስፋሁ ለአብ።

ጶ ጸም

- ትፈውስ ቁስለ ነፍስ። ጾም የነፍስን ቁስል ታድናለች።

ፀ ብሂል

- ፀሐየ ጽድቅ እግዙአብሔር ። የእውነት ፀሐይ እግዙአብሔር ነው ማለት ነው።

ፁ ብሂል = ዮም ሠረፁ ጽጌ በረከት።

ፂ ብሂል

- መላፂ ዘክልኤ አፉሁ።

ፃ ብሂል

- ፋፃ መንፈስ ቅዱስ።

ፄ ብሂል

- ሕፄሁ ለዳዊት ።

ፅ ብሂል

- ዕፅ አብርሃም ዘሠፀረ ለምሥዋዕ።

ፆ ብሂል

- ማዕፆ አፉሆሙ ለጻድቃን።

ፈ ብሂል

- ፈጠረ ዓለመ በጥበቡ። ዓለምን በጥበቡ ፈጠረ ማለት ነው።

ፉ ብሂል

- ምዕራፉ ለዓለም።

ፊ ብሂል

- ፊደለ ወንጌል።

ፋ ብሂል

- አልፋ ወኦ

ፈ ብሂል

- ጎዳፈ ነፍሳት።

ፍ ብሂል

- ፍኖት ለጎበ አቡሁ።

ፎ ብሂል

- ፎራ ጎብስተ ቁርባን።

ፐ ብሂል

- ፓፓኤል ሥሙ ለእግዙአብሔር ።

ፑ ብሂል

- ኖፑ አስካለ ወንጌል።

ፒ ብሂል

- ፒላሳሁ።

ፓ ብሂል

- ፓንዋማንጦን።

ፔ ብሂል

- እግዙአብሔር።

ፕ ብሂል

- ሮፕ ጽኑዕ እግዙአብሔር።

ፖ ብሂል

- በቀዳሚ ገብረ እግዙአብሔር ሰማየ ወምድረ። በመጀመርያ እግዙአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ማለት ነው።

ክፍል 4 ይቀጥላል

ምንጭ፦ የሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው መጽሐፈ ግሥ ወሰዋስው

❤ግእዝ ❤ክፍል ❤አራት

የግእዝ አኀዝ

❖ አኀዜ አኀዝ ጀመረ ቆጠረ ከሚለው የግእዜ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ቁጥር ማለት ነው። የግእዜ ቋንቋ

የራሱ የሆነ መቁጠሪያ ቁጥር አለው። በግእዜ ቋንቋ በዋናነት 20 መሥራች ቁጥሮች አሉ።እነዙህም፦

ቁጥሩ ሲነበብ በአማርኛ

፩.....አሐዱ.....አንድ

፪.....ክልኤቱ.....ሁለት

፫.....ሠለስቱ.....ሦስት

፬.....አርባዕቱ.....አራት

፭.....ኀምስቱ.....አምስት

፮.....ስድስቱ.....ስድስት

፯.....ሰብዓቱ.....ሰባት

፰.....ሰምንቱ.....ስምንት

፱.....ተስዐቱ.....ዘጠኝ

፲.....አሠርቱ.....አስር

፳.....ዕሥራ.....ሃያ

፴.....ሠላሳ.....ሠላሳ

፵.....አርብዓ.....አርባ

፶.....ኃምሳ.....አምሳ

፷.....ስድሳ/ስሳ.....ስልሳ

፸.....ሰብዓ.....ሰባ

፹.....ሰማንያ.....ሰማንያ

፺.....ተስዓ.....ዘጠና

፻.....ምእት.....መቶ

፼.....እልፍ.....አስር ሺ

፲፼.....አሠርቱ እልፍ/አእላፍ.....መቶ ሺ

፼፼.....አእላፋት.....አንድ ሚልየን

፲፼፼.....አሠርቱ አእላፋት/ትእልፊት.....አሥር ሚልየን

፼፼፼.....ትእልፊታት.....መቶ ሚልየን

፲፼፼፼.....ምእልፊት.....አንድ ቢልየን

፼፼፼፼.....ምእልፊታት.....አሥር ቢልየን

ከዚህ በላይ ያሉ ቁጥሮች ዘርፍ በማያያዜ እስከፈለግነው ድረስ መቁጠር እንችላለን።

ለምሳሌ 10000000000000000000 ይህ ቁጥር ምእልፊተ ምእልፊታት ይባላል። ምእልፊት ሲባዚ በምእልፊት እንደማለት ያለ ነው።

- ✓ አንደኛ መንገድ፦ከ1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች

ለምሳሌ 29ን ወደ ግእዜ ቁጥር ለውጥ ቢባል 20+9=፳+፱=፳፱ ይሆናል ይህም ሲነበብ ዕሥራ ወተስዓቱ ይላል። ተጨማሪ ለምሳሌ 84ን ወደ ግእዜ ቁጥር ለመለወጥ 80+4=፹+፬=፹፬ ይሆናል ይህም ሲነበብ ሰማንያ ወአርባዕቱ ይላል። ከ1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች በዙህ መንገድ ይሄዳሉ ማለት ነው።

- ✓ #ሁለተኛ #መንገድ

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ከ100 እስከ 10000 ያሉ ቁጥሮች

፻ ይህ አንድ መቶ ከሆነ ሁለት መቶ ሦስት መቶ አራት መቶ ለማለት ፊት ለፊቱ ላይ ከአንድ እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መጠቀም ነው። ይኽውም፦

፩፻.....አሐዱ ምእት....አንድ መቶ

፪፻.....ክልኤቱ ምእት...ሁለት መቶ

፫፻.....ሠለስቱ ምእት.....ሦስት መቶ

፬፻....አርባዕቱ ምእት.....አራት መቶ

፭፻....ኀምስቱ ምእት....አምስት መቶ

፮፻....ስድስቱ ምእት....ስድስት መቶ

፯፻.....ሰብዓቱ ምእት....ሰባት መቶ

፰፻....ሰመንቱ ምእት...ስምንት መቶ

፱፻.....ተስዓቱ ምእት.....ዘጠኝ መቶ

፲፻.....አሠርቱ ምእት.....አንድ ሺ

ይላል ማለት ነው።ከዙህ በኋላ በእነዙህ መካከል ያለውን ቁጥር ለምሳሌ 208ን በግእዜ ጻፍ ብትባል 200ን እንዳለ ትወስድና ስምንትን መጨመር ነው ይሄውም ፪፻፰ ይላል። ሲነበብ ክልኤቱ ምእት ወሰመንቱ ይላል።

ሌላ በተጨማሪ 975ን በግእዜ ጻፍ ብትባል 900ን እንዳለ ትወስድና 75ን መጨመር ነው።75ን ከአንድ እስከ መቶ ባለው አካሄድ መሠረት 70+5=፸+፭=፸፭ ሰብዓ ወኀምስቱ ይሆናል። ስለዙህ 975 በግእዜ ፱፻፸፭ ይሆናል ሲነበብ ተስዓቱ ምእት ሰብዓ ወኀምስቱ ይላል ማለት ነው።በግእዜ ቋንቋ አንድ ሺ ስንል አሥር መቶ እንደማለት ያለ ሆኖ አሠርቱ ምእት ይባላል።ሁለት ሺ ስንል ደግሞ ዕሥራ ምእት ይላል።ሃያ መቶ እንደማለት ነው። እንዲህ እያለ ዘጠኝ ሺ ተስዓ ምእት ይላል ዘጠና መቶ እንደማለት ነው። አሥር ሺ ሲደርስ መቶ መቶ ከማለት ይልቅ የራሱ መሥራች እልፍ የሚል ስያሜ ያለው ቁጥር ነው።

፲፱.....አሠርቱ ምእት.....አንድ ሺ

፳፱.....ዕሥራ ምእት.....ሁለት ሺ

፴፱.....ሠላሳ ምእት.....ሦስት ሺ

፵፱.....አርብዓ ምእት....አራት ሺ

፶፱.....ኃምሳ ምእት.....አምስት ሺ

፷፱.....ስድሳ ምእት.....ስድስት ሺ

፸፱.....ሰብዓ ምእት.....ሰባት ሺ

፹፱.....ሰማንያ ምእት.....ሰምንት ሺ

፺፱.....ተስዓ ምእት.....ዘጠኝ ሺ

፼.....እልፍ.....አሥር ሺ

ይላል።በዚህ መካከል ያሉ ቁጥሮችን ለማንበብና ለመጻፍ ለምሳሌ 2014 ዓ.ም የሚለውን ስንጽፍ 2000ን እንዳለ ወስደን 14ን መጨመር ነው። ይኽም ፳፻፲፬ ይላል። ሲነበብ ዕሥራ ምእት አሠርቱ ወአርባዕቱ ይላል።

ሌላ ለምሳሌ 5500ን በግእዜ ለመጻፍ 5000ን እንዳለ ወስደን 500ን መጨመር ነው።ይኽውም ፶፻ፎ ይላል ሲነበብ ኃምሳ ምእት ወኃምስቱ ምእት ይላል። ሌላ የመጨረሻ ምሳሌ 9999ን በግእዜ ጻፍ ብትባል።9000ን እንዳለ ትወስዳለህ ከዙያ 900ን እንዳለ ትወስዳለህ ከዙያ 90ን እንዳለ ትወስዳለህ ከዙያ 9ን ትወስዳለህ። ስለዚህ ፺፻፱፻፺፱ ይሆናል ሲነበብ ተስዓ ምእት ወተስዓቱ ምእት ተስ ዓ ወተስዓቱ ይላል።

❖ ጥያቄ የሚከተሉትን ቃላት ወደ ግእዝ ለውጥ።

1) 79
2) 56
3) 563
4) 843
5) 6423

❤ግእዝ ❤ክፍል ❤አምስት (፭)

እስከ መቶ ሚልየን ቁጥሮች

❖ እንግዲህ 10ሺ አንድ እልፍ ነው። 20ሺ ሁለት እልፍ ይሆናል። እንዲህ እያልን ስንቆጥር

፩፼.....አሐዱ እልፍ.....10ሺ

፪፼.....ክልኤቱ እልፍ.....20ሺ

፫፼.....ሠለስቱ እልፍ.....30ሺ

፬፼.....አርባእቱ እልፍ.....40ሺ

፭፼.....ኀምስቱ እልፍ.....50ሺ

፮፼.....ስድስቱ እልፍ.....60ሺ

፯፼.....ሰብዓቱ እልፍ.....70ሺ

፰፼.....ስምንቱ እልፍ.....80ሺ

፱፼.....ተስዓቱ እልፍ.....90ሺ

፲፼.....አሠርቱ እልፍ....100ሺ

፳፼.....ዕሥራ እልፍ.....200ሺ

፴፼.....ሠላሳ እልፍ.....300ሺ

፵፼.....አርብዓ እልፍ.....400ሺ

፶፼.....ኃምሳ እልፍ.....500ሺ

፷፼.....ስድሳ እልፍ.....600ሺ

፸፼.....ሰብዓ እልፍ.....700ሺ

፹፼.....ሰማንያ እልፍ.....800ሺ

፺፼.....ተስዓ እልፍ.....900ሺ

፼፼.....አእላፋት..... .አንድ ሚልየን

አሠርቱ እልፍ በሌላ ስያሜ አእላፍ እየተባለ ይጠራል።ስለዚህ ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት።

- ለምሳሌ 46435 በግእዜ ጻፍ ብትባል። ፡4*10000+60*100+4*100+30+5 ይሆናል። ይህም በግእዝ ፬*፼+፷*፻+፬*፻+፴+፭ ይሆንና በአንድ ላይ ፬፼፷፻፬፻፴፭ ይላል ሲነበብ አርባእቱ እልፍ ወስድሳ ምእት ወአርባእቱ ምእት ሠላሳ ወኀምስቱ ይላል።

ሌላ ምሳሌ 9845347 በግእዜ ጻፍ ብትባል። 90*10000+8*10000+40*100+5*100+30+4 ማለት ነው። ይህ በግእዜ ሲትካ ፺*፼+፹*፼+፵*፻+፭*፻+፴+፬ ይሆናል በአንድ ላይ ፺፼፹፼፵፻፭፻፴፬ ይሆናል ሲነበብም። ተስዓ እልፍ ወስምንቱ እልፍ አርብዓ ምእት ወኃምስቱ ምእት ሠላሳ ወአርባእቱ ይላል ማለት ነው።

- ✓ #አራተኛ #አካሄድ

ከአንድ ሚልየን እስከ መቶ ሚልየን

፩፼፻...አሐዱ አእላፋት...1 ሚልየን

፪፻፪...ክልኤቱ አእላፋት..2 ሚልየን

፫፻፪...ሠለስቱ አእላፋት..3 ሚልየን

፬፻፪...አርባዕቱ አእላፋት..4 ሚልየን

፭፻፪...ኀምስቱ አእላፋት..5 ሚልየን

፮፻፪....ስድስቱ አእላፋት..6 ሚልየን

፯፻፪....ሰብዓቱ አእላፋት..7 ሚልየን

፰፻፪....ስምንቱ አእላፋት..8 ሚልየን

፱፻፪....ተስዓቱ አእላፋት..9 ሚልየን

፲፻፪..አሠርቱ አእላፋት..10 ሚልየን

፳፻፪...እሥራ አእላፋት...20 ሚልየን

፴፻፪....ሠላሳ አእላፋት..30 ሚልየን

፵፻፪..አርብዓ አእላፋት..40 ሚልየን

፶፻፪....ኃምሳ አእላፋት..50 ሚልየን

፷፻፪....ስድሳ አእላፋት..60 ሚልየን

፸፻፪....ሰብዓ አእላፋት..70 ሚልየን

፹፻፪.ሰማንያ አእላፋት..80 ሚልየን

፺፻፪.....ተስዓ አእላፋት..90 ሚልየን

፻፻፪.....ትእልፊታት....100 ሚልየን

በተለየ አስር ሚልየን በሌላ ስያሜ ትእልፊት ይባላል። ክፍል 6 ይቀጥላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

❤ግዕዝ ❤ክፍል ❤ስድስት (፮)

ከ100ሚልየን እስከ 10 ቢልየን

፩፼፼....አሐዱ ትእልፊታት..100M

፪፼፼..ክልኤቱ ትእልፊታት..200M

፫፼፼...ሠለስቱ ትእልፊታት..300M

፬፼፼..አርባዕቱ ትእልፊታት..400M

፭፼፼...ኀምስቱ ትእልፊታት..500M

፮፼፼...ስድስቱ ትእልፊታት..600M

፯፼፼...ሰብዓቱ ትእልፊታት..700M

፰፼፼...ስምንቱ ትእልፊታት..800M

፱፼፼...ተስዓቱ ትእልፊታት..900M

፲፼፼.....አሠርቱ ትእልፊታት..1B

፳፼፼.....እሥራ ትእልፊታት...2B

፴፼፼.....ሠላሳ ትእልፊታት...3B

፵፼፼.....አርብዓ ትእልፊታት...4B

፶፼፼.....ኃምሳ ትእልፊታት...5B

፷፼፼.....ስድሳ ትእልፊታት...6B

፸፼፼.....ሰብዓ ትእልፊታት...7B

፹፼፼.....ሰማንያ ትእልፊታት..8B

፺፼፼.....ተስዓ ትእልፊታት...9B

፻፼፼.....ምእልፊታት...10B

አሠርቱ ትእልፊታት በሌላ ስያሜ ምእልፊት ይባላል።ሌላው ከላይ "M" ያልኩት ሚልየንን ሲሆን "B" ያልኩት

ደግሞ ቢልየንን ነው።ከዙህ ቀጥሎ ባለውም "B" ስል ቢልየን ማለቴን ማስተዋል ይገባል።

ከ10 ቢልየን በላይ ያሉ ቁጥሮች

፩፼፼፼..አሐዱ ምእልፊታት..10B

፪፼፼፼..ክልኤቱ ምእልፊታት..20B

፫፼፼፼..ሠለስቱ ምእልፊታት..30B

፬፼፼፼..አርባዕቱ ምእልፊታት..40B

፭፼፼፼..ኀምስቱ ምእልፊታት..50B

፮፼፼፼..ስድስቱ ምእልፊታት..60B

፯፼፼፼..ሰብዓቱ ምእልፊታት..70B

፰፼፼፼..ስምንቱ ምእልፊታት..80B

፱፼፼፼..ተስዓቱ ምእልፊታት..90B

፲፼፼፼..አሠርቱ ምእልፊታት..100B

፳፼፼፼..ዕሥራ ምእልፊታት...200B

፴፼፼፼..ሠላሳ ምእልፊታት...300B

፵፼፼፼..አርብዓ ምእልፊታት..400B

፶፼፼፼..ኃምሳ ምእልፊታት....500B

፷፼፼፼..ስድሳ ምእልፊታት....600B

፸፼፼፼..ሰብዓ ምእልፊታት....700B

፹፼፼፼.ሰማንያ ምእልፊታት..800B

፯፻፻፻...ተስዓ ምእልፊታት....900B

፻፻፻፻...አእላፊ ትእልፊታት...1T

"T" ያልኩት ትሪልየን ለማለት ነው። እንዲህ እንዲህ እያለ ከዙህ በላይ ያሉትን ቁጥሮች ዘርፍ እያስያዝን እስከ ፈለገን ድረስ መቁጠር እንችላለን። B ያልኩት ቢልየን ለማለት ነው ።

❖ በዚህ አንድ ምሳሌ ልሥራና የዛሬውን ትምህርት ልጨርስ።

98764532246967ን ዘጠኝ ትሪልየን ስምንት መቶ ሰባ ስድስት ቢልየን አራት መቶ ሃምሳ ሦስት ሚልየን ሁለት መቶ አርባ ስድስ ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባትን በግእዜ ለመጻፍ ፦

9*1000000000000+80*10000000000+7*10000000000+60*100000000+4*100000000+50*1000000+3*1000000+20*10000+4*10000+60*100+9*100+60+7 ይህም በግእዜ ሲለወጥ፱*፻፻፻፻፻፻+፹*፻፻፻፻፻+፯*፻፻፻፻፻+፷*፻፻፻፻+፬*፻፻፻፻+፶*፻፻፻+፫*፻፻፻+፷*፻፻+፳*፻+፷+፯ይሆናል።ይህምሲጠቀለልይ፻፻፻፻፻፻፻፹፻፻፻፻፻፯፻፻፻፻፻፷፻፻፻፻፬፻፻፻፻ ፶፻፻፻፫፻፻፻፷፻፻፳፻፻፷፻ይ፻፷፯ ይሆናል።

ሲነበብም። ተስዓቱ አእላፊ ትእልፊታት ሰማንያ ምእልፊታት ወሰብዓቱ ምእልፊታት ስድሳ ትእልፊታትወአርባእቱ ትእልፊታት ኃምሳ አእላፋት ወሠለስቱ አእላፋት ወዕሥራ እልፍ ወአርባእቱ እልፍ ስድሳ ምእት ወተስዓቱ ምእት ስድሳ ወሰብዓቱ ይላል። ወይም ደግሞ በሌላ አገላለጽ ይ፻፻፻፻፻፻፹፯፻፻፻፻፻፷፬፻፻፻፻፶፫፻፻፻፻፷፱፻፻፻፷፬፻፻፷፯ ተስዓቱ አእላፊ ትእልፊታት ሰማንያ ወሰብዓቱ ምእልፊታት ስድሳ ወአርባእቱ ትእልፊታት ኃምሳ ወሠለስቱ አእላፋት ዕሥራ ወአርባእቱ እልፍ ስድሳ ወተስዓቱ ምእት ስድሳ ወሰብዓቱ ይሆናል።

❤ግዕዝ ❤ክፍል ❤ሰባት (፯)

መራሕያን

❖ በግእዜ ቋንቋ ቁልፍ የሆኑ አሥር መራሕያን አሉ። መራሕያን የሚለው ቃል መርሐ መራ ከሚለው የግእዜ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ መሪዎች ማለት ነው።መራሕያን በሰዋስው ውስጥ ሴትና ወንድን፣ አንድና ብዙን፣ ሩቅና ቅርብን የሚያሳውቁን ቁልፍ ቃላት ናቸው።

❖ 10ሩ መራሕያን የሚባሉትም

በግእዜ.....በአማርኛ.....English

1) ውእቱ.....እርሱ.....He

2) ውእቶሙ/እሙንቱ....እነርሱ (ወ).....They

3) ይእቲ.....እርሷ.....She

4) ውእቶን/እማንቱ....እነርሱ (ሴ)....they

5) አንተ.....አንተ.....you

6) አንትሙ.....እናንተ (ወ)....you

7) አንቲ.....አንቺ.....you

8) አንትን.....እናንተ (ሴ)....you

9) አነ.....እኔ.....I

10) ንሕነ.....እኛ.....We

እኒህ ናቸው።እኒህም በተለያየ አከፋፈል ይከፈላሉ።በጾታ (Gender) ስንከፍላቸው ሴት እና ወንድ ናቸው። ለሴት የሚሆኑ መራሕያን "አንቲ፣ ይእቲ፣ ውእቶን/እማንቱ፣ አንትን" ናቸው። ለወንድ የሚሆኑ መራሕያን ደግሞ "ውእቱ፣

ውእቶሙ/እሙንቱ፣ አንተ፣ አንትሙ" ናቸው። አስተውል በግእዜ ቋንቋ ሴቶችን እናንተ ስንልና ወንዶችን እናንተ ስንል የተለያየ ነው።

- በእንግሊዘኛው ደግሞ ሴቶችን እናንተ ስንል፣ ወንዶችን እናንተ ስንል፣ አንዱን ወንድ አንተ ስንል፣ እና አንዷን ሴት አንቺ ስንል በሁሉም ተመሳሳይ ነው "You" ነው። በግእዜ ሴቶችን እናንተ ስንል አንትን እንላለን። ወንዶችን እናንተ ስንል አንትሙ እንላለን። እንዲሁም ሴቶችን እና ወንዶችን እነርሱ ስንል ወንዶችን እነርሱ ስንል ውእቶሙ/እሙንቱ እንላለን። ሴቶችን እነርሱ ስንል ውእቶን/እማንቱ እንላለን። ሴት እና ወንድ ተቀላቅለው ካሉ ደግሞ ውእቶሙ/እሙንቱ፣ አንትሙ እየተባለ በወንዶች አንቀጽ ይነገራል። ከመራሕያን ለሴትም ለወንድም የሚያገለግሉ፣ ጾታ የማይለዩ "አነ፣ እና ንሕነ" ናቸው።

ሴትም እኔ ስትል "አነ" ትላለች። ወንድም እኔ ሲል "አነ" ይላል። ወንዶችም እኛ ሲሉ "ንሕነ" ይላሉ። ሴቶችም እኛ ሲሉ "ንሕነ" ይላሉ። ሌላው መራሕያን በነጠላና (Singular) በብዘ (Plural) ይከፈላሉ። ነጠላ የሚባሉት አንድን ግለሰብ የሚያሳውቁ ናቸው እኒህም፦ አነ፣ ውእቱ፣ ይእቲ፣ አንቲ እና አንተ ናቸው።

- ብዙ የሚባሉት ደግሞ ንሕነ፣ውእቶሙ/እሙንቱ፣ ውእቶን/እማንቱ፣ አንትሙ እና አንትን ናቸው። በሌላ አከፋፈል ቅርብ መደብና ሩቅ መደብ ተብለው ይከፈላሉ። ቅርብ መደብ የሚባሉት በቅርበት የምንናገራቸውን ነው። እኒህም አነ፣ ንሕነ፣ አንተ፣ አንትሙ፣ አንትን፣ አንቲ ናቸው። በአጭሩ አንደኛ መደብ (first person) እና ሁለተኛ መደቦች (second person) ቅርብ መደብ ይባላሉ። ሩቅ መደብ የሚባሉት ሦስተኛ መደቦች (third person) ናቸው እኒህም "ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ ይእቲ፣ ውእቶን" ናቸው። ከ10ሩ መራሕያን ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ ይእቲ፣ አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ፣ አነ እና ንሕነ ተነስተው ይነበባሉ። እሙንቱ እና እማንቱ ወድቀው ይነበባሉ (ሥርዓተ ንባባቸው ወዳቂ ንባብ ነው)። አንትን እና ውእቶን ተጥለው ይነበባሉ (ሥርዓተ ንባባቸው ተጣይ ነው)።

የመራሕያን አገልግሎት

- ✓ መራሕያን በአገልግሎታቸው በሦስት ይከፈላሉ። እኒህም የስም ምትክ (Pronoun) ሆነው ሲያገለግሉ፣
  - አመልካች ቅጽል (Demonsrtrative pronoun) ሆነው ሲያገለግሉ እና ነባር አንቀጽ (auxilary verb) ሆነው ሲያገሉ ናቸው።መራሕያን የስም ምትክ ሆነው የሚያገለግሉት ከግስ (verb) በፊት ሲመጡ ነው።የስም ምትክ ሆነው ሲያገለግሉ የሚኖራቸውም ትርጉም ከላይ ከ1-10 የተጻፈው ነው።
  - ለምሳሌ ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ሲል "ተዐቢ" የሚለው ቃል ግሥ ስለሆነ ይእቲ ደግሞ ከግሥ በፊት ስለመጣ የሚኖረው ትርጉም "እርሷ" ይሆናል ማለት ነው። በዚህም መሠረት ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ሲል እርሷ ከኪሩቤል ትበልጣለች ማለት ነው። መራሕያን ነባር አንቀጽ ሆነው ሲያገለግሉ የሚኖራቸው ትርጉም እንደሚከተለው ነው።

ግእዜ.....አማርኛ.....English

1) ውእቱ..ነው፣ ነበረ፣ አለ..Is, was, be
2) ውእቶሙ/እሙንቱ...ናቸው፣ ነበሩ፣ አሉ....are, were,
3) ይእቲ....ናት፣ ነበረች፣ አለች... Is, was
4) ውእቶን/እማንቱ.....ናቸው፣ ነበሩ፣ አሉ.....are, were
5) አንተ...ነህ፣ ነበርክ፣ አለ, are, were
6) አንትሙ...ናችሁ፣ ነበራችሁ፣ አላችሁ....are, were
7) አንቲ....ነሽ፣ ነበርሽ፣ አለሽ... are, were
8) አንትን.....ናችሁ፣ ነበራችሁ፣ አላችሁ...are, wer

9) አነ.....ነኝ፣ ነበርኩ፣ አለሁ....am, was

10) ንሕነ....ነን፣ ነበርን፣ አለን, are, were

- መራሕያን እንደ ነባር አንቀጽ ሲያገለግሉ መሆንን እና መኖርን ያሳውቃሉ። እንደ ነባር አንቀጽ የሚተረጎሙትም ከስም (noun) ወይም ከዓረፍተ ነገር (sentence) በኋላ ሲመጡ ነው።
- ማርያም ይእቲ እሙ ለክርስቶስ ሲል "ይእቲ" የሚለው መራሒ ማርያም ከሚለው ስም በኋላ ስለመጣ ሊተረጎም የሚችለው በነባር አንቀጽ ነው። ስለዙህም የክርስቶስ እናቱ ማርያም ናት ይላል ማለት ነው።
- በተጨማሪም ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ሲል "ውእቱ" የሚለው መራሒ "ከዓረፍተ ነገር(ከስም) በኋላ ስለመጣ በነባር አንቀጽነቱ ይተረጎማል። ስለዙህም በመጀመሪያ ቃል ነበር ተብሎ ይተረጎማል።

መራሕያን አመልካች ቅጽል ሆነው ሲያገለግሉ የሚኖራቸው ትርጉም ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ግእዜ.....አማርኛ....English

1) ውእቱ.....ያ.....That

2) ውእቶሙ/እሙንቱ...እነዙያ...Those

3) ይእቲ.....ያች....that

4) ውእቶን/እማንቱ....እነዙያ....those

5) አንተ.....አንተ....you

6) አንትሙ.....እናንተ...you

7) አንቲ.....አንቺ.....you

8) አንትን.....እናንተ.....I

9) አነ.....እኔ.....we

10) ንሕነ.....እኛ ይላል።

መራሕያን በአመልካች ቅጽልነት የሚተረጎሙት ከስም በፊት (before a noun) ሲመጡ ነው።

- ለምሳሌ ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ከሚለው ዓረፍተ ነገር "ውእቱ" የሚለው መራሒ "ቃል" ከሚለው ስም በፊት የመጣ ስለሆነ በአመልካች ቅጽልነቱ ይተረጎማል። ስለዚህም "ያ ቃል ሥጋ" ሆነ ተብሎ ይተረጎማል። በነባር አንቀጽ ጊዛ "ውእቱ" በተለየ በ10ሩም መራሕያን ይተረጎማል። ለምሳሌ "አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም" ቢል። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ይላል። ውእቱ "ናችሁ" ተብሎ ተተርጉሟል። ነኝ፣ ነሽ፣ ናት....ወዘተ እያለ በ10ሩም ይተረጎማም።

✓ ሁለት መራሕያን ተከታትለው ሲመጡ የመጀመሪያው መራሒ በስም ምትክ ይተረጎማል። ቀጥሎ ያለው መራሒ ደግሞ በነባር አንቀጽ ይተረጎማል።

✓ ለምሳሌ "አነ ውእቱ ገብርኤል መልአክ ዘእቀውም በቅድመ እግዚአብሔር ቢል" አነ የሚለው መራሒና "ውእቱ" የሚለው መራሒ ተከታትለው መጥተዋል።

✓ ስለዚህ የመጀመሪያው በስም ምትክ እኔ ተብሎ ይተረጎማል። ሁለተኛው ደግሞ በነባር አንቀጽነቱ "ነኝ" ተብሎ ይተረጎማል። ስለዙህ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል መልአክ እኔ ነኝ ተብሎ ይተረጎማል።

ድርብ እና ተሳቢ መራሕያን

- በባለቤትነት የሚያገለግሉ ሌላ ዓይነት 10 መራሕያን አሉ እነዙህም ድርብ መራሕያን ይባላሉ።።

ከነትርጉማቸው እንደሚከተለው ናቸው።።

ግእዜ.....አማርኛ.....English

1) ለሊሁ.....እርሱ ራሱ.....himself
2) ለሊሆሙ...እነርሱ ራሳቸው(ወ)....themselves
3) ለሊሃ.....እርሷ ራሷ.....herself
4) ለሊሆን....እነርሱ ራሳቸው(ሴ)...themselves
5) ለሊከ.....አንተ ራስህ.....yourself
6) ለሊክሙ.....እናንተ ራሳችሁ(ወ).....yourselves
7) ለሊኪ.....አንቺ ራስሽ....yourself
8) ለሊክን.....እናንተ ራሳችሁ(ሴት)....yourselves
9) ለልየ.....እኔ ራሴ.....myself
10) ለሊነ.....እኛ ራሳችን...ourselves ይላል።።በምሳሌ ለማየት ያህል።።ለሊነ ነአምር ኩሎ ዘኮነ ሲል እኛ ራሳችን የሆነውን ሁሉ እናውቃለን ማለት ነው።።

- ሌላው የምንመለከተው ደግሞ ተሳቢ መራሕያንን ነው።።እነዚህም 10 ሲሆኑ።። እንደሚከተለው ናቸው፦

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ግእዜ.....አማርኛ.....English

1) ኪያሁ.....እርሱን.....Him

2) ኪያሆሙ..እነርሱን(ወ)...Them

3) ኪያሃ.....እርሷን.....Her

4) ኪያሆን....እነር ሱን(ሴ)....Them

5) ኪያከ.....አንተን.....you

6) ኪያክሙ.....እናንተን(ወ)....you

7) ኪያኪ.....አንቺን.....you

8) ኪያክን....እናንተን(ሴ)....you

9) ኪያየ.....እኔን.....Me

10) ኪያነ.....እኛን.....Us

በምሳሌ ለማየት ያህል ኪያከ እግዙኦ ነአኩት ሲል አቤቱ አንተን እናመሰግንሀለን ተብሎ ይተረጎማል።

በመጨረሻም "የዘ" ዜርዜር በ10ሩ መራሕያን ሲዘረዘር እንመለከታለን።

ግእዜ.....አማርኛ.....English

1) ዙኣሁ.....የእርሱ.....his

2) ዙኣሆሙ..የእነርሱ(ወ)...Their

3) ዙኣሃ.....የእርሷ.....Her

4) ዙኣሆን....የእነርሱ...their

ዙ የሚለው በስሕተት ነው ትክክለኛው 'ዚ' ነው

5) ዙኣከ....የአንተ....Your/Yours

6) ዙኣክሙ...የእናንተ(ወ)...your/yours

7) ዙኣኪ.....የአንቺ....your/yours

8) ዙኣክን....የእናንተ(ሴ)....your/yours

9) ዙኣየ.....የእኔ.....My/Mine

10) ዙኣነ.....የእኛ.....Our/Ours ይላል።

በእንግሊዘኛ "My/mine" ያለው በግእዝ ዚኣየ ነው። በምሳሌ እንመልከተው። ዘርፍ ሲይዝ በእንግሊዘኛው "My" ያለውን ቃል ሲይዝ። ዘርፍ ካልያዘ ደግሞ "Mine" የሚለውን ይይዛል። በግእዘ ግን በትርጉም ያው ተመሳሳይ ነው።

አማርኛ.....የእኛ ሀገር ቆንጆ ናት

ግእዜ.....ሠናይት ይእቲ ሀገረ ዙኣነ

English....Our Country is beautiful

ይላል። ቀጣዩን ምሳሌ እይና አመዛዝን።

አማርኛ.....ኢትዮጵያ የእኛ ናት

English.....Ethiopia is ours

ግእዜ.....ዚኣነ ይእቲ ኢትዮጵያ ይላል ማለት ነው።

#ጥያቄዎች

1) ስለ ግእዜ ቋንቋ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ.የራሱ የሆነ ሥር ዓተ ንባብ አለው

ለ.የራሱ የሆነ ፊደል አለው

ሐ.የራሱ የሆነ ቁጥር አለው

መ.ሁሉም

2) ሦስተኛ መደብ ነጠላ የሴት ጾታ መራሒ ማን ናት?

ሀ. ውእቱ

ለ. ይእቲ

ሐ. አንቲ

መ. አነ

3) ሁለተኛ መደብ መራሒ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) እሙንቱ

ለ) አንትሙ

ሐ) አንትን

መ) ለ እና ሐ

4) "2015" በግዕዜ ቁጥር ሲጻፍ?

ሀ. ፪፼፲፭

ለ. ፳፻፲፭

ሐ. ፪፻፻፭፩

መ. ፳፻፩፳

5) መራሒው አመልካች ቅጽል የሆነበት ዓረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ) ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ

ለ) ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም

ሐ) አነ ውእቱ ፍኖተ ሕይወት

መ) ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል

6) ሠለስቱ እልፍ አርብዓ ወሰመንቱ በአኃዜ ሲገለጥ.....ይሆናል?

ሀ. ፫፬፵፯፰

ለ. ፫፬፵፯፳

ሐ. ፫፻፬፵፯፰

መ. ፫፻፬፵፯፳

7) "አቤቱ አንተን እናመሰግናለን" የሚለው ወደ አማርኛ ሲተረጎም ምን ይሆናል?

ሀ. ኪያከ እግዙኦ ንሴብሕ

ለ. ኪያከ እግዙኦ ነአኵት

ሐ. ለሊከ እግዙኦ ንሴብሕ

መ. ሀ እና ለ

8) "አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም" ከሚለው ዓረፍተ ነገር የውእቱ አገልግሎት ምንድን ነው?

ሀ. አመልካች ቅጽል

ለ. ነባር አንቀጽ

ሐ. የስም ምትክ

መ. አጸፋ

9) ከሚከተሉት ውስጥ "አእላፋት" የሚለውን ቁጥር የሚተካ አጋዜ የትኛው ነው?

ሀ. ፻፻፻

ለ. ፻፻፻፻

ሐ. ፻፻፻፻፻

መ. ፲፻፻፻

10) ከሚከተሉት መራሕያን ሥርዓተ ንባቡ ተጣይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አንትን

ለ. አንትሙ

ሐ. ውእቶሙ

መ. አንቲ

ረድኤተ እግዙአብሔር አይለየን::

ክፍል 11 ይቀጥላል::

❤ ግእዝ ❤ ክፍል ❤ ፲፩

የግስ ዝርዝር በመራሕያን

❖ አንድ ግሥ በአሥሩ መራሕያን ሲዘረዘር እንደሚከተለው ነው።

#አንደኛ #አካሄድ

1) በውእቱ ጊዜ ምንም የሚጨመር ነገር የለም። ምሳሌ አእመረ ብሎ አወቀ ይላል።

2) በውእቶሙ ጊዜ መድረሻ ፊደሉን ወደ ካዕብ መለወጥ ነው። ይኸውም አእመሩ ብሎ አወቁ ይላል።

3) በይእቲ ጊዜ መድረሻ ፊደሉ ላይ "ት" ፊደልን መጨመር ነው። ይኸውም አእመረት ብሎ አወቀች ይላል።

4) በውእቶን ጊዜ መድረሻ ፊደሉን ወደ ራብዕ መለወጥ ነው። አእምራ ብሎ አወቁ ይላል።

5) በአንተ ጊዜ ቅድመ መድረሻውን ሳድስ ለውጦ "ከ" ፊደልን መጨመር ነው።አእመርከ ብሎ አወቅህ ይላል።

6) በአንትሙ ጊዜ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ለውጦ "ክሙ" ፊደልን መጨመር ነው። አእመርክሙ ብሎ አወቃችሁ ይላል።

7) በአንቲ ጊዜ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ቀይሮ "ኪ" ፊደልን መጨመር ነው። አእመርኪ ብሎ አወቅሽ ይላል።

8) በአንትን ጊዜ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ቀይሮ "ክን" ፊደልን መጨመር ነው። አእመርክን ብሎ አወቃችሁ ይላል።

9) በአነ ጊዛ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ቀይሮ "ኩ" ፊደልን መጨመር ነው።አእመርኩ ብሎ አወቅሁ ይላል።

10) በንሕነ ጊዛ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ቀይሮ "ነ" ፊደልን መጨመር ነው።አእመርነ ብሎ አወቅን ይላል።

- አብዚኛው ግሥ ይህንን መስሎ ይዘረዘራል። አስተውል በሁለተኛ መደቦችና በአንደኛ መደቦች ጊዛ ቅድመ መድረሻውን ወደ ሳድስ ቀይሮ ባእድ ቀለማትን "ከ፣ ክሙ፣ ኪ፣ ክን፣ ነ፣ ኩ"ን ይጨምራል። በላይኛው አካሄድ አንድ ምሳሌ እንመልከትና የተለየ አካሄድ ያላቸውን ግሦች እንመለከታለን።

መራሒ.....ግእዝ.....አማርኛ

1) ውእቱ አፍቀረ ወደደ
2) ውእቶሙ አፍቀሩ ወደዱ
3) ይእቲ አፍቀረት ወደደች
4) ውእቶን አፍቀራ ወደዱ
5) አንተ አፍቀርከ ወደድክ
6) አንትሙ አፍቀርክሙ ወደዳችሁ
7) አንቲ አፍቀርኪ ወደድሽ
8) አንትን አፍቀርክን ወደዳችሁ
9) አነ አፍቀርኩ ወደድኩ
10) ንሕነ አፍቀርነ ወደድን

- አስተውል በግእዜ ቋንቋ ወንዶችን ወደዳችሁ ስንልና ሴቶችን ወደዳችሁ ስንል የተለያየ ነው። ወንዶችን ወደዳችሁ ስንል አፍቀርክሙ እንላለን። ሴቶችን ወደዳችሁ ስንል ደግሞ አፍቀርክን እንላለን።
- ወንዶች ወደዱ ስንል አፍቀሩ እንላለን። ሴቶችን ወደዱ ለማለት አፍቀራ እንላለን። ሴት እና ወንድ ተቀላቅለው ካሉ ደግሞ በወንድ አንቀጽ አፍቅርክሙ፣ አፍቅሩ እንላለን ማለት ነው።ሁለት ፊደል ሆነው በ"ሀ" እና በ"አ" የሚጨርሱ ግሦችም ይህንኑ መስለው ይዘረዘራሉ።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ምሳሌ 1፦ ግእዝ አማርኛ

1) ውእቱ ኖኅ ረዘመ

2) ውእቶሙ ኖኅ ረዘሙ

3) ይእቲ ኖኅት ረዘመች

4) ውእቶን ኖኅ ረዘሙ

5) አንተ ኖኅከ ረዘምክ

6) አንትሙ ኖኅክሙ ረዘማችሁ

7) አንቲ ኖኅኪ ረዘምሽ

8) አንትን ኖኅክን ረዘማችሁ

9) አነ ኖኅኩ ረዘምኩ

10) ንሕነ ኖኅነ ረዘምን ይላል።

በ"አ" ሲጨርሱ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ምሳሌ 2፦ ግእዝ አማርኛ

1) ውእቱ ሦዐ ሠዋ

2) ውእቶሙ ሦዑ ሠዉ

3) ይእቲ ሦዐት ሠዋች

4) ውእቶን ሦዓ ሠዉ

5) አንተ ሦዕከ ሠዋህ

6) አንትሙ ሦዕክሙ ሠዋችሁ

7) አንትን ሦዕክን ሠዋችሁ

8) አንቲ ሦዕኪ ሠዋሽ

9) አነ ሥዕኩ ሠዋሁ

10) ንሕነ ሥዕነ ሠዋን ይላል።

- አስተውል በሁለት ፊደል ጨርሰው መድረሻቸው "አ፣ዐ" ወይም "ሀ፣ ኀ፣ ሐ" የሆኑ ግሦች የሚዘረዘሩት በዚህ መልኩ ነው። ሦስትና ከዙያ በላይ ፊደል ያላቸው በሀ እና በአ የሚጨርሱ ግሦች ግን የተለየ አካሄድ ስላላቸው ቀጣዩ ክፍል ላይ ተመልከት።

- የእለቱ ጥያቄዎች ፦

የሚከተሉትን ግሶች ከላይ ባለው መሠረት በ10ሩ መራሕያን ዘርዝር

1) ቦአ.....ገባ

2) ቀደሰ....አመሰገነ

3) ዴገነ.....ተከተለ

ክፍል 12 ይቀጥላል።

ግእዝ ክፍል ፲፪

❖ በ"ነ" የሚጨርስ ግሥ ልክ ክፍል ፲፩ ላይ እንዳየነው አካሄድ የሚዘረዘር ሲሆን በንሕነ ብቻ የተለየ አካሄድ አለው። ይኽውም "ነ"ን ይጎርድና "ጠብቆ" እንዲነበብ ያደርገዋል።

መራሒ ግእዝ አማርኛ

1) ውእቱ ወጠነ ጀመረ
2) ውእቶሙ ወጠኑ ጀመሩ
3) ይእቲ ወጠነት ጀመረች
4) ውእቶን ወጠና ጀመሩ
5) አንተ ወጠንከ ጀመርክ
6) አንትሙ ወጠንክሙ ጀመራችሁ
7) አንቲ ወጠንኪ ጀመርሽ
8) አንትን ወጠንክን ጀመራችሁ
9) አነ ወጠንኩ ጀመርኩ
10 ንሕነ ወጠ[ነ] ጀመርን

✓ አስተውል ውእቱ ወጠነ ሲል እና ንሕነ ወጠነ ሲል በጽሑፍ ተመሳሳይ ቢሆኑም በንባብ ይለያያሉ። ንሕነ ወጠነ ሲል [ነ] ጠብቆ ይነበባል። ውእቱ ወጠነ ሲል ግን ላልቶ ይነበባል።

✓ የገብረ ቤቶች በአሥሩ መራሕያን ሲዘረዘሩ በአንደኛ መደቦች ማለትም በአነ እና በንሕነ እና በሁለተኛመደቦች ማለትም በአንተ፣ በአንትሙ፣ በአንቲ፣ እና በአንትን ጊዛ ቅድመ መድረሻቸውን ወደ ግእዜ ለውጠው ይዘረዘራሉ። የገብረ ቤት የሚባሉት ሦስት ፊደል ያላቸው ግሦች ሆነው መነሻቸው

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ግእዝ መካከለኛው ሳድስ መጨረሻው ግእዜ የሆኑ ግሦች ናቸው። ለምሳሌ ሠምረ የሚለው ግሥ የገብረ ቤት ይባላል። ምክንያቱም መጀመሪያ ሦስት ፊደል ያለው ሲሆን በመቀጠል "ሠ" ግእዜ ነው። "ም" ሳድስ ነው። "ረ" ግእዜ ነው።

ስለዚህ የገብረ ቤቶች እንደሚከተለው ይ□ረ□ራሉ።

መራሒ.....ግእዜ.....አማርኛ

1) ውእቱ ገብረ ሠራ
2) ውእቶሙ ገብሩ ሠሩ
3) ይእቲ ገብረት ሠራች
4) ውእቶን ገብራ ሠሩ
5) አንተ ገበርከ ሠራህ
6) አንትሙ ገበርክሙ ሠራችሁ
7) አንቲ ገበርኪ ሠራሽ
8) አንትን ገበርክን ሠራችሁ
9) አነ ገበርኩ ሠራሁ
10 ንሕነ ገበርነ ሠራን

በ"ቀ፣ ከ፣ ገ" የሚጨርሱ ግሦች በአሥሩ መራሕያን ሲ□ረ□ሩ በአንደኛ መደብ በአነ ብቻ እና በሁለተኛ መደቦች በአንተ፣ በአንትሙ፣ በአንቲ፣ በአንትን ጊዛ "ከ" ጎርደው ጠብቀው ይነበባሉ። ለምሳሌ ሰበከ አስተማረ ይል የነበረው ሰበከ አስተማርክ ይላል እንጂ ሰበክከ አይልም።አስተማርክ ሲል ያለው "ሰበከ" ከ ጠብቆ ይነበባል።

በምሳሌ እንመልከት።

ምሳሌ 1፦ ግእዜ አማርኛ

1) ውእቱ ሰበከ አስተማረ

2) ውእቶሙ ሰበኩ አስተማሩ

3) ይእቲ ሰበከት አስተማረች

4) ውእቶን ሰበካ አስተማሩ

5) አንተ ሰበ[ከ] አስተማርክ

6) አንትሙ ሰበ[ክ]ሙ አስተማራችሁ

7) አንትን ሰበ[ክ]ን አስተማራችሁ

8) አንቲ ሰበ[ኪ] አስተማርሽ

9) አነ ሰበ[ኩ] አስተማርኩ

10) ንሕነ ሰበክነ አስተማርን

- በዚህ ምልክት [ ] የተቀመጡ ቃላት ጠብቀው እንደሚነበቡ ለማመልከት ነው።አስተውል በጽሑፍ ደረጃ ውእቱ ሰበከ ሲልና አንተ ሰበከ ሲል ተመሳሳይ ቢሆንም በንባብ ግን ይለያያል። አንተ ሰበከ ከሚለው "ሰበከ" ሲል "ከ" ይጠብቃል። አነ ሰበኩ በሚለውና ውእቶሙ ሰበኩ በሚለው መካከልን በጽሐፍ ተመሳሳይነት ቢኖርም በንባብ አነ ሰበኩ ከሚለው "ኩ" ይጠብቃል። በዙያኛው ላልቶ ይነበባል ማለት ነው። ቀጥለን ከምናያቸው የቀ እና የግ ግሦችም ይህንኑ ይመስላል። የአነ እና የአንተ ሲጠብቅ የውእቱ እና የውእቶሙ ላልቶ ይነበባል።

ምሳሌ 2፦ ግእዜ አማርኛ

1) ውእቱ አጥመቀ አጠመቀ

2) ውእቶሙ አጥመቁ አጠመቁ

3) ይእቲ አጥመቀት አጠመቀች

4) ውእቶን አጥመቃ አጠመቁ

5) አንተ አጥመ[ቀ] አጠመቅህ

6) አንትሙ አጥመ[ቅ]ሙ አጠመቃችሁ

7) አንቲ አጥመ[ቂ] አጠመቅሽ

8) አንትን አጥመ[ቅ]ን አጠመቃችሁ

9) አነ አጥመ[ቁ] አጠመቅሁ

10) ንሕነ አጥመቅነ አጠመቅን ይላል ማለት ነው።

❖ የእለቱ ጥያቄዎች፦

የሚከተሉትን ግሦች በ10ሩ መራሕያን ዘርዜር።

1) ሠምረ...ወደደ

2) ሠረቀ....ወጣ

ግእዝ ክፍል ፲፫

❖ ሦስት ፊደልና ከዙያ በላይ ይሆነ በ"ሀ፣ኀ፡ሐ" ወይም በ"አ፣ዐ" የሚጨርስ ግሥ ሲዘረዜር በአንደኛ መደቦችና በሁለተኛ መደቦች ግዛ ቅድመ መድረሻውን ራብዕ አድርጎ ይዘረዘራል።

ምሳሌ 1፦ ግእዜ አማርኛ

1) ውእቱ መጽአ መጣ

2) ውእቶሙ መጽኡ መጡ

3) ይእቲ መጽአት መጣች

4) ውእቶን መጽኣ መጡ

5) አንተ መጻእከ መጣህ

6) አንትሙ መጻእክሙ መጣችሁ

7) አንቲ መጻእኪ መጣሽ

8) አንትን መጻእክን መጣችሁ

9) አነ መጻእኩ መጣሁ

10) ንሕነ መጻእነ መጣን

ምሳሌ፦2 ግእዜ አማርኛ

1) ውእቱ መርሐ መራ

2) ውእቶሙ መርሑ መሩ

3) ይእቲ መርሐት መራች

4) ውእቶን መርሓ መሩ

5) አንተ መራሕከ መራሕ

6) አንትሙ መራሕክሙ መራችሁ

7) አንቲ መራሕኪ መራሽ

8) አንትን መራሕክን መራችሁ

9) አነ መራሕኩ መራሑ

10) ንሕነ መራሕነ መራን

- ❖ የክህለ ቤት ሆነው መድረሻ ቀለማቸው "የ" የሆኑ ግሦች ሲዘረዘሩ በአንደኛና በሁለተኛ መደቦች "የ"ን ይጎርዱና ቅድመ መድረሻቸውን ወደ ሣልስ ቀይረው ይዘረዘራሉ።
- ❖ የክህለ ቤት የሚባሉት መነሻቸው ሳድስ መካከላቸው ሳድስ መጨረሻቸው ግእዜ የሆኑ ሦስት ፊደል ያላቸው ቃላት ናቸው።

መራሒ	ግእዜ	አማርኛ
1) ውእቱ	ርእየ	አየ
2) ውእቶሙ	ርእዩ	አዩ
3) ይእቲ	ርእየት	አየች
4) ውእቶን	ርእያ	አዩ
5) አንተ	ርኢከ	አየህ
6) አንትሙ	ርኢክሙ	አያችሁ
7) አንቲ	ርኢኪ	አየሽ
8) አንትን	ርኢክን	አያችሁ
9) አነ	ርኢኩ	አየሁ
10) ንሕነ	ርኢነ	አየን

❖ የእለቱ ጥያቄዎች፦

የሚከተሉትን ግሦች በ10ሩ መራሕያን ዘርዜር።

1) ጥዕየ....ዳነ

2) ተፈሥሐ....ተደሰተ

3) ረብዐ.....አራት አደረ

ግእዝ ክፍል ፲፬

የስም ዝርዝር በመራሕያን

➢ #አንደኛ #አካሄድ

በሳድስ የሚጨርሱ ሥሞች እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ (ይረባሉ)። ለምሳሌ "ሀገር" የሚለውን በአሥሩ

መራሕያን ለመዘርዘር፦

1) በውእቱ ጊዛ መድረሻ ፊደሉን ወደ ካዕብ መቀየር ነው። ሀገሩ ይላል ትርጉሙ አገሩ ማለት ነው።

2) በውእቶሙ ጊዛ መድረሻ ፊደሉን ወደ ሳብዕ ቀይረው "ሙ" ፊደልን ይጨምራሉ። ሀገሮሙ ይላል ትርጉሙ አገራቸው ማለት ነው።

3) በይእቲ ጊዛ መድረሻ ፊደሉን ወደ ራብዕ ይቀይራል።ሀገራ ይላል። ትርጉሙ አገሯ ማለት ነው።

4) በውእቶን ጊዛ መድረሻ ፊደላቸውን ወደ ሳብዕ ቀይሮ "ን" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገሮን ይላል። ትርጉሙ አገራቸው ማለት ነው።

5) በአንተ ጊዛ "ከ" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርከ ብሎ አገርህ ይላል።

6) በአንትሙ ጊዛ "ክሙ" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርክሙ ብሎ አገራችሁ ይላል።

7) በአንቲ ጊዛ "ኪ" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርኪ ብሎ አገርሽ ይላል።

8) በአንትን ጊዛ "ክን" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርክን ብሎ አገራችሁ ይላል።

9) በአነ ጊዛ "የ" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርየ ይላል አገሬ ማለት ነው።

10) በንሕነ ጊዛ "ነ" ፊደልን መጨመር ነው። ሀገርነ ብሎ አገራችን ይላል።

በሳድስ የሚጨርሱ ስሞች ብዘ ጊዛ የሚረቡት በዙህ ሕግ መሠረት ነው። አንድ ምሳሌ ልጨምር። ለምሳሌ "ማኅደር" የሚለው ስም መድረሻ ፊደሉ "ር" ሳድስ ስለሆነ ከላይ ባለው ሕግ መሠረት ይረባል ማለት ነው።

ይኽውም እንደሚከተለው ነው።

	መራሒ	ግእዝ	አማርኛ
1)	ውእቱ	ማኅደሩ	ቤቱ
2)	ውእቶሙ	ማኅደሮሙ	ቤታቸው
3)	ይእቲ	ማኅደራ	ቤቷ
4)	ውእቶን	ማኅደሮን	ቤታቸው
5)	አንተ	ማኅደርከ	ቤትህ
6)	አንትሙ	ማኅደርክሙ	ቤታችሁ
7)	አንቲ	ማኅደርኪ	ቤትሽ
8)	አንትን	ማኅደርክን	ቤታችሁ
9)	አነ	ማኅደርየ	ቤቴ
10)	ንሕነ	ማኅደርነ	ቤታችን

- #ሁለተኛ #አካሄድ

ከሳድስ ውጭ ባሉ ፊደላት የሚጨርሱ ሥሞች ደግሞ በአሥሩ መራሕያን ሲዘረዘሩ የተለየ አካሄድ አላቸው።

ለምሳሌ "ደብተራ" የሚለውን ቃል ብንወስድ የመጨረሻ ፊደሉ "ራ" ከሳድስ ውጭ ስለሆነ የተለየ አረባብ አለው።ይኽውም እንደሚከተለው ነው።

1) በውእቱ ጊዛ "ሁ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራሁ ይላል ትርጉሙ ድንኳኑ ማለት ነው።

2) በውእቶሙ ጊዛ "ሆሙ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራሆሙ ይላል ትርጉሙ ድንኳናቸው ማለት ነው።

3) በይእቲ ጊዛ "ሃ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራሃ ይላል። ድንኳኗ ማለት ነው።

4) በውእቶን ጊዛ "ሆን" ፊድልን መጨመር ነው። ደብተራሆን ብሎ ድንኳናቸው ይላል።

5) በአንተ ጊዛ "ከ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራከ ብሎ ድንኳንህ ይላል።

6) በአንትሙ ጊዛ "ክሙ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራክሙ ብሎ ድንኳናችሁ ይላል።

7) በአንቲ ጊዛ "ኪ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራኪ ብሎ ድንኳንሽ ይላል።

8) በአንትን ጊዛ "ክን" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራክን ብሎ ድንኳናችሁ ይላል።

9) በአነ ጊዛ "የ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራየ ይላል ድንኳኔ ማለት ነው።

10) በንሕነ ጊዛ "ነ" ፊደልን መጨመር ነው። ደብተራነ ብሎ ድንኳናችን ይላል።

ተጨማሪ ምሳሌ "ሥጋ" የሚለውን ሥም በ10ሩ መራሕያን ለመዘርዘር።

	መራሒ ግእዝ	አማርኛ
1)	ውእቱ	ሥጋሁ ሥጋው
2)	ውእቶሙ	ሥጋሆሙ ሥጋቸው
3)	ይእቲ	ሥጋሃ ሥጋዋ
4)	ውእቶን	ሥጋሆን ሥጋቸው
5)	አንተ	ሥጋከ ሥጋህ
6)	አንትሙ	ሥጋክሙ ሥጋችሁ
7)	አንቲ	ሥጋኪ ሥጋሽ
8)	አንትን	ሥጋክን ሥጋችሁ
9)	አነ	ሥጋየ ሥጋየ
10	ንሕነ	ሥጋነ ሥጋችን

- #ሦስተኛ #አካሄድ

ብዚትን የሚያመለክቱ ስሞች (Plural Nouns) በአሥሩ መራሕያን በሚ□ረ□ሩበት ጊዛ መድረሻቸውን ወደ ሣልስ ቀይረው ይዘረዘራሉ። በአንቲ እና በአነ ዜርዜር ጊዛ ግን መድረሻቸውንም ሳድስ አድርገው ይዘረዘራሉ።

በምሳሌ እንመልከት። አዕይንት ማለት ዓይኖች ማለት ነው። ይህ በ10ሩ መራሕያን ሲዘረዘር ምንም እንኳ የመጨረሻ ፊደሉ ሳድስ ቢሆንም ነገር ግን ዓይኖች ሲል ብዚትን ስለሚያመለክት የተለየ አካሄድ አለው።

	መራሒ ግእዝ	አማርኛ
1)	ውእቱ	አዕይንቲሁ ዓይኖቹ
2)	ውእቶሙ	አዕይንቲሆሙ ዓይኖቻቸው
3)	ይእቲ	አዕይንቲሃ ዓይኖቿ
4)	ውእቶን	አዕይንቲሆን ዓይኖቻቸው

5) አንተ አዕይንቲከ ዓይኖችህ

6) አንትሙ አዕይንቲክሙ ዓይኖቻችሁ

7) አንቲ አዕይንትኪ ዓይኖችሽ

8) አንትን አዕይንቲክን ዓይኖቻችሁ

9) አነ አዕይንትየ ዓይኖቼ

10) ንሕነ አዕይንቲነ ዓይኖቻችን ይላል።

❖ አስተውል በአነ እና በአንቲ ጊዛ መድረሻው "ት" ሳድስ ሲሆን በሌሎች ግን "ቲ" ሣልስ ነው። ለምሳሌ መልክአ ማርያም ላይ "ሰላም ለአዕይንትኪ" ይላል እንጂ ሰላም ለአዕይንቲኪ አይልም።

አንዳንድ ሥሞች ከላይ ያለውን ሕግ የማይጠብቁ ይኖራሉ። ለምሳሌ "አብ" አባት የሚለው በአሥሩ መራሕያን ሲዘረዘር አቡሁ፣ አቡሆሙ፣ አቡሃ፣ አቡሆን፣ አቡከ፣ አቡክሙ፣ አቡኪ፣ አቡክን፣ አቡየ፣ አቡነ ይላል። "እም...እናት" የሚለው ግን በመጀመሪያው አካሄድ ይሄዳል ይሄውምኑ እሙ፣ እሞሙ፣ እማ፣ እሞን፣ እምከ፣ እምክሙ፣ እምኪ፣ እምክን፣ እምየ፣ እምነ ይላል ማለት ነው።

❖ መልመጃ

የሚከተሉትን ሥሞች በአሥሩ መራሕያን ዘርዝር

1) ደብር.....ተራራ

2) ፍቅር.....ፍቅር

3) መሰንቆ.....መሰንቆ

ግእዝ ክፍል ፲፭

ባለቤት እና ተሳቢ

- በግእዜ ቋንቋ አንድ ቃል ባለቤት ሲሆንና ተሳቢ ሲሆን የተለያየ ቅርጽ ይኖረዋል። ለምሳሌ "ሀገር" የሚለው ቃል በዓረፍተ ነገር ውስጥ በባለቤትነት (Subject) ሲያገለግል "ሀገር" የሚል ሲሆን በተሳቢነት (Object) ሲያገለግል ግን "ሀገረ" ይላል። አንድ ቃል ተሳቢ ሲሆን ሲተረጎም "ን" ፊደልን ያመጣል።
- ለምሳሌ እግዙአብሔር ፈጠረ ሰማየ ብንል ሲተረጎም እግዙአብሔር ሰማይን ፈጠረ ማለት ነው። "ሰማይ" ያለው ቃል ተሳቢ ሲሆን "ሰማየ" ማለቱን ልብ ማድረግ ነው።ሰማይ ተፈጥረ በእግዙአብሔር ቢል ግን ሰማይ በእግዙአብሔር ተፈጠረ ማለት ስለሆነ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት "ሰማይ" ስለሆነ ባለበት ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ አንድን ቃል ተሳቢ ለማድረግ ስንፈልግ የራሱ የሆኑ ሕጎች አሉ። እነርሱን እንመልከት።

- #አንደኛ #አካሄድ

መድረሻ ቀለማቸው "ሳድስ" የሆኑ ቃላት ተሳቢ በሚሆኑበት ጊዛ መድረሻ ቀለሙ ወደ "ግእዜ" ይለወጣል።

ይህም ለምሳሌ "መንግሥት" የሚለው ቃል ተሳቢ ሲሆን "መንግሥተ" ይላል። ማለት ነው። ሳድስ"ት" ወደ ግእዜ "ተ" መለወጡን አስተውል። ተጨማሪ ምሳሌዎች፦

ባለቤት ተሳቢ

ፍቅር ፍቅረ

ምድር ምድረ

ጎብስት ጎብስተ

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ሕይወት ሕይወተ

ለምሳሌ "ሕይወትን አገኘን" በሚለው ቃል ውስጥ "ሕይወት" የሚለው ቃል "ን"ን ተሳቢ ስላመጣ ወደ

ግእዜ ሲተረጎም "ሕይወተ ረከብነ" ይላል። ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ እንዲል።

#ሁለተኛ #አካሄድ

መድረሻ ቀለማቸው "ካእብ" የሆኑ ቃላት ተሳቢ በሚሆኑበት ግእዜ መድረሻ ቀለማቸውን ወደ "ሳብዕ" ይቀይራሉ። ለምሳሌ "ቤቱ ያምራል" ስንል እና "ቤቱን አሳመረ" ብንል ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር "ቤቱ" የሚለው ቃል በባለቤትነት ሲያገለግል በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ያለው "ቤቱን" ያለው ቃል ግን ተሳቢ ነው። በግእዜ ሲተረጎም "ቤቱ ያምራል" ያለው ቃል "ቤቱ ይሤኒ" ይላል። "ቤቱን አሳመረ" የሚለው ቃል ደግሞ "አሠነየ ቤቶ" ይላል ማለት ነው። በዙህ ጊዛ ካእብ "ቱ" ወደ ሳብእ "ቶ" እንደተለወጠ አስተውል።

ተጨማሪ ምሳሌዎች፦

ባለቤት ተሳቢ

መንግሥቱ መንግሥቶ

ሀገሩ ሀገሮ

ደሙ ደሞ

ፍቅሩ ፍቅሮ

መንግሥቱን ሰጠን የሚለውን ዓረፍተ ነገር ወደ ግእዜ ለመለወጥ "መንግሥቶ አወፈየን" እንላለን። አስተውል "መንግሥቶ" ብሎ መድረሻ ቀለሙን "ሳብእ" ያደረገው ተሳቢ ስለሆነ ነው። "መንግሥቱ" የሚለው በባለቤትነት ሲያገለግም ለምሳሌ " መንግሥቱ ዘለዓለም ወምኩናኩኒ ለትውልደ ትውልድ" ይላል።

#ሦስተኛ #አካሄድ

መድረሻ ቀለማቸው "ሣልስ" የሆኑ ቃላት ተሳቢ ሲሆኑ መድረሻ ቀለማቸውን ወደ "ኃምስ" ይለውጣሉ።

ለምሳሌ "ሌባን አታቅርብ" የሚለውን አማርኛ ወደ ግእዜ ለመተርጎም ብንፈልግ "ሌባን" የሚለው ቃል ተሳቢ ነው። በግእዜ ሌባ "ሰራቂ" ነው። ይህ ደግሞ ተሳቢ ሲሆን "ሰራቄ" ይላል። ስለዙህ ሙሉ ዓረፍተ ነገሩ "ኢታቅርብ ሰራቄ" ይላል ማለት ነው።

ተጨማሪ ምሳሌዎች፦

ባለቤት ተሳቢ

ጸሐፊ ጸሐፌ

ሠዓሊ ሠዓሌ

ቀታሊ ቀታሌ

ገባሪ ገባሬ

ግእዝ ክፍል ፲፮

ከክፍል ፲፭ የቀጠለ

#አራተኛ #አካሄድ

መድረሻ ቀለማቸው "ራብእ፣ ኃምስ፣ እና ሳብእ" የሆኑ ቃላት ተሳቢ ሲሆኑ ምንም ዓይነት የፊደል ለውጥ አያመጡም።ይህም ማለት ለምሳሌ "ጽጌ" የሚለው ቃል መድረሻ ቀለሙ "ጌ" ኃምስ ስለሆነ ተሳቢ ሲሆን ያው ራሱ "ጽጌ" ይላል እንጂ ምንም ለውጥ አያመጣም ማለታችን ነው።

በምሳሌ ለማየት ያህል "ንብ አበባን ትወዳለች" ብንልና "አበባ በንብ ይወደዳል" ብንል ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር "አበባ" ተሳቢ ሲሆን ከሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ደግሞ "አበባ" ባለቤት ነው። ወደ ግእዝ ቋንቋ በምንተረጉምበት ጊዜ የመጀመሪያው "ንህብ ታፈቅር ጽጌ" ይላል። ሁለተኛው "ጽጌ ይትፈቀር በንህብ" ይላል። በሁለቱም ላይ "ጽጌ" ተመሳሳይ ነው። በአማርኛ ትርጉም ግን ይለያል ማለት ነው።

ተጨማሪ ምሳሌዎች፦

ባለቤት ተሳቢ

መሰንቆ መሰንቆ

ከበሮ ከበሮ

እንዙራ እንዙራ

ትሕትና ትሕትና

ራማ ራማ

ቅዳሴ ቅዳሴ

ዜማሬ ዜማሬ

- #አምስተኛ #አካሄድ

ሥሞች ተሳቢ በሚሆኑበት ጊዜ በመድረሻ ፊደላቸው ለወንዶች ግእዘ "ሀ"ን ለሴቶች ራብዑ "ሃ"ን ያመጣሉ::ይህም ማለት ለምሳሌ አዳም ሔዋንን ወደደ ብንል "አዳም" ባለቤት፣ "ሔዋን" ተሳቢ፣ "ወደደ" ደግሞ ማሰሪያ አንቀጹ ነው:: ይህ ወደ ግእዜ ሲተረጎም "አዳም አፍቀረ ሔዋንሃ" ይላል ማለት ነው::በተገላቢጦሽ "ሔዋን አዳምን ወደደች" የሚለው ወደ ግእዜ ሲተረጎም ደግሞ "ሐዋን አፍቀረት አዳምሀ" ይላል ማለት ነው::

ተጨማሪ ምሳሌ፦

ባለቤት ተሳቢ

ኢየሱስ ኢየሱስሀ

ኤርምያስ ኤርምያስሀ

ማርያም ማርያምሃ

ኤልሳቤጥ ኤልሳቤጥሃ

ይላል ማለት ነው:: ለምሳሌ "እምኩሉ እለት ሰንበተ አክበረ:: ወእምኩሉ አንስት ማርያምሃ አፍቀረ" ቢል:: ከእለት ሁሉ ሰንበትን አከበረ:: ከሴት ሁሉ ደግሞ ማርያምን ወደደ ማለት ነው::

- #ስድስተኛ #አካሄድ

ተናባቢ ቃላት ባለቤት ሲሆኑ እና ተሳቢ ሲሆኑ ተመሳሳይ ነው:: መጀመሪያ "ተናባቢ ቃላት" የሚባሉት ሁለት የግእዝ ቃላት አንድ ላይ ተጣምረው በአንድ ትንፋሽ ሲነበቡ ነው:: ለምሳሌ "ቤተመንግሥት" የሚለው ቃል ቤት እና መንግሥት ከሚሉት ቃላት የወጣ "ተናባቢ ቃል" ነው:: ሁለት ቃላት በአንድ ላይ ሲጣመሩ የራሱ የሆነ ሰዋስዋዊ ሕግ አለ ይኽውም ሳድሱ ወደ ግእዜ፣ ሣልሱ ወደ ኃምስ ይለወጣል::

ራብዕ፣ ኃምስ እና ሳብዕ ሲናበቡ አይለወጡም:: ለምሳሌ "መንግሥት" እና "ሰማያት" የሚሉ ቃላት ሲናበቡ "መንግሥተ ሰማያት" ይላል:: አስተውል

"መንግሥት" ከሚለው ቃል የመድረሻ ፊደሉ ሳድሱ "ት" ወደ ግእዜ "ተ" ተቀይሯል።

ሌላው "መጋቢ" የሚለው ቃል እና "ሐዲስ" የሚለው ቃል ሲናበብ "መጋቤ ሐዲስ" ይላል። አስተውል ሣልሱ "ቢ" ወደ ኃምስ "ቤ" ተቀይሯል። ውዳሴ እና ማርያም የሚሉ ሁለት ቃላት ሲናበቡ ውዳሴ ማርያም ይላል "ሴ" ኃምስ ስለሆነ አልተለወጠም። መሰንቆ እና ዳዊት ሲናበቡ "መሰንቆ ዳዊት" ይላል። "ቆ" ሳብዕ ስለሆነ አልተለወጠም። ትሕትና እና ማርያም የሚሉ ሁለት ቃላት ሲናበቡ "ትሕትና ማርያም" ይላም። "ና" ራብዕ ስለሆነ አልተለወጠም።

ተጨማሪ ምሳሌዎች።

ቃል 1 ቃል 2 ሲናበብ

ሊቅ ሊቃውንት ሊቀሊቃውንት

ማይ ዮርዳኖስ ማየዮርዳኖስ

መጋቢ ብሉይ መጋቤብሉይ

ፈጣሪ ሰማያት ፈጣሬሰማያት

ዜማሬ መላእክት ዜማሬመላእክት

እንዙራ ስብሐት እንዙራስብሐት

ከበሮ ማኅሌት ከበሮማኅሌት

እንግዲህ ተናባቢ ቃላት ተሳቢ ሲሆኑ ምንም የሚለወጥ ፊደል የለም። ለምሳሌ "ሊቀ ሊቃውንትን አከብራለሁ" ስንል እና "ሊቀ ሊቃውንት መጣ" ብንል። ከመጀመሪያው ያለው ሊቀሊቃውንት "ተሳቢ" ከሁለተኛው ያለው "ባለቤት" ነው። ሁለቱም ወደ ግእዜ በሚተረጎሙበት ጊዛ "ሊቀ ሊቃውንት" የሚለው ቃል ላይ የሚለወጥ ቃል የለም። ይኽውም። አከብር ሊቀ ሊቃውንት፣ ሊቀ ሊቃውንት መጽአ ይላል ማለት ነው።

#ሰባተኛ #አካሄድ

የሥም ዜርዜር በመራሕያን ሲዘረዘሩ እና ተሳቢ ሲሆኑ ሁለት መንገድ አለ።ሁለቱንም አይተን የዛሬ ትምህርታችንን እንጨርስ።

መራሒ ባለቤት ተሳቢ

ውእቱ ቤቱ ቤቶ

ውእቶሙ ቤቶሙ ቤቶሙ

ይእቲ ቤታ ቤታ

ውእቶን ቤቶን ቤቶን

አንተ ቤትከ ቤተከ

አንትሙ ቤትክሙ ቤተክሙ

አንቲ ቤትኪ ቤተኪ

አንትን ቤትክን ቤተክን

አነ ቤትየ ቤትየ

ንሕነ ቤትነ ቤተነ

በሳድስ የሚጨርሱ ቃላት ይህንን መስለው ይሄዳሉ። ከሳድስ ውጭ ያሉ ቃላት ግን ባለቤታቸው እና ተሳቢያቸው ተመሳሳይ ነው። ሥጋሁ የሚለው ሲሳብ ሥጋሁ ይላል እንጂ ሥጋሆ አይልም።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

#ስምንቱ #አርእስተ #ግስ

የግስ አርእስት የሚባሉት 8 ናቸው። እነርሱም፦

ግእዝ.....አማርኛ

1) ቀተለ.....ገደለ

2) ቀደሰ.....አመሰገነ

3) ተንበለ.....ለመነ

4) ባረከ.....አመሰገነ

5) ዴገነ.....ተከተለ

6) ክህለ.....ቻለ

7) ጦመረ.....ጸፈ

8) ማህረከ.....ማረከ ናቸው።

- ✓ ቀተለ ደግሞ የሁሉም ርእስ ስለሆነ ርእሰ አርእስት ይባላል። የአንድን ግሥ አርእስት ማወቅ እንዴት እንደሚዘረዘር ፍንጭ ስለሚሰጥ አርእስተ ግሥ የተባሉትን መለየት ያስፈልጋል።
- ✓ የጦመረ ቤት የሚባለው መነሻው ሳብእ የሆነ ግሥ ነው።

ለምሳሌ፦

ግእዜ.....አማርኛ

ሞቅሐ.....አሰረ

ሞርቅሐ.....ላጠ

ኖለወ.....ጠበቀ

- ✓ የክህለ ቤት የሚባለው ደግሞ መነሻው ሳድስ የሆነ ግሥ ነው።ምሳሌ፦

ግእዜ.....አማርኛ

ብህለ.....አለ

ርእየ.....አየ

ጥዕየ.....ዳነ

- ✓ የዴገነ ቤት የሚባለው ደግሞ መነሻው ኃምስ የሆነ ግሥ ነው። ምሳሌ፦

ግእዜ.....አማርኛ

ሴሰየ.....መገበ

ቄቅሐ.....ፈተገ

ጼወወ.....ማረከ

- ✓ 3 ፊደል ሆኖ በራብዕ የሚነሳ ከሆነ ደግሞ የባረከ ቤት ይባላል። ምሳሌ፦

ግእዜ.....አማርኛ

ናፈቀ.....ተጠራጠረ

ማ ሰነ.....ጠፋ

- ✓ 4 እና ከዙያ በላይ ፊደል ያለው ሆኖ በራብዕ የሚጀምር ግሥ ደግሞ የማህረከ ቤት ይባላል።

ግእዜ.....አማርኛ

ጻዕደወ.....ነጭ ሆነ

ማህረከ.....ማረከ

- ✓ የተንበለ ቤት የሚባለው 4 ፊደል ባለው ግሥ መነሻው ግእዝ ሆኖ ከመነሻው ቀጥሎ ሳድስ ከሆነ ነው። 5 ፊደል ባለው ግስ ደግሞ መካከለኛው ወይም ድኅረ መነሻው ፊደል ሳድስ ሆኖ ሌላው ግእዝ ከሆነ ነው።

ለምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

አእመረ.....አወቀ

አመድበለ.....አከማቸ

አስቆረረ.....አስጠላ

- ✓ የቀተለ ቤት የሚባለው ደግሞ ላልቶ የሚነበብ በግእዜ የሚጀምር ፍጹም ሳድስ የሆነ ግሥ ነው። ምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

ሀለበ.....አለበ

ሰበከ.....አስተማረ

- ✓ የቀደሰ ቤት የሚባለው ደግሞ በግእዜ የሚጀምር ጠብቆ የሚነበብ ሦስት እና ከዙያ በላይ የሆነ ቃል ነው።

ለምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

ሐወጸ.....ጎበኘ

ጸውዐ.....ጠራ

ተፈሥሐ.....ተደሰተ

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው 8ቱ የግሥ አርእስት ሲሆን አንዳንድ ጊዛ በየቅኔ ቤቱ የተወሰነ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ከእነዙህ ከ8ቱ በተጨማሪ አንድን ግሥ ለማርባት የሚጠቅሙን ግሦች አሉ። እነዚህም፦

ግእዝ.....አማርኛ

1) ሜመ.....ሾመ

2) ቆመ.....ቆመ

3) ገብረ.....ሠራ

4) ጎሠ.....ፈለገ

- የሜመ ቤት የሚባለው ሁለት ፊደል ሆኖ በኃምስ የሚጀምር ግሥ ነው።

ምሳሌ፦

ግእዜ.....አማርኛ

ቄሐ.....ተፋ

ሬመ.....ከፍ ከፍ አለ

- የቆመ ቤት የሚባለው ደግሞ ሁለት ፊደል ሆኖ በሳብዕ የሚጀምር ግሥ ነው።

ምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

ኖኀ.....ረዘመ

ሎሀ.....ጻፈ

ሞአ.....አሸነፈ

- የገብረ ቤት የሚባለው ደግሞ መነሻው ግእዜ ከዙያ ቀጥሎ ያለው መካከለኛው ሳድስ መድረሻው ግእዜ የሆነ ቃል ነው።

ምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

ሠምረ.....ወደደ

ሐብረ.....አንድ ሆነ

- ሁለት ፊደል ያላቸው "ኀሠ"ን የመሠሉ መነሻቸውም መድረሻቸውም ግእዝ የሆኑ ቃላት ደግሞ ብዙ ጊዜ መድረሻ ፊደሉን ሁለት ጊዜ ደግመው ሊነገሩ የሚችሉ ናቸው።

ለምሳሌ ኀሠ ብሎ ፈለገ ይላል። እንደገና መድረሻውን ደግሞ ኀሠሠ ብሎ ፈለገ ይላል።

ተጨማሪ ምሳሌ፦

ግእዝ.....አማርኛ

ነደ.....ነደደ

ጠበ.....ብልሀተኛ ሆነ

ከዚህ በላይ ያየናቸው ቃላት ካሁን በኋላ ለምንማረው ትምህርት መሠረታዊ የሆኑ ናቸው።

ግእዝ ክፍል ፲፯

ሰራዊት

አርእስታቸውን ወይም አለቃቸውን የሚመስሉ ነገር ግን የተወሰነ የፊደላት አቀማመጥ ልዩነት ያላቸው ቃላት ሠራዊት ይባላሉ።

- ለምሳሌ ቀተለ አርእስት ነው። ነገር ግን የቃሉ ሆሄያት አደራደር "ቀተለ" ከሚለው ቃል የተለዩ ሆነው አረባባቸው ግን ቀተለን የሚመስሉ ቃላት የቀተለ ሠራዊት ይባላሉ። እኒህም፦

ግእዝ.....አማርኛ

1) ጎቤተ.....አገለገለ
2) ተኬሰ.....መታ፣ጠመጠመ
3) ሰኮተ.....ወለወለ፣ ሠራ (የመንገድ)

ከዚህ እንደምንመለከተው ጎቤተ እና ተኬሰ መካከላቸው ኃምስ ነው። ሰኮተ ደግሞ መካከሉ ሳብዕ ነው። በሆሄያት አደራደር ከቀተለ የተለየ ቢሆንም ነገር ግን ቀተለን መስለው ስለሚረቡ የቀተለ ሠራዊት ተብለዋል።

- የቀደሰ ሠርዌ የሚባለው ደግሞ የሚከተለው ነው።

ግእዝ.....አማርኛ

1) አንገለገ.....አከማቸ

የቀደሰ ሠርዌ አንድ አንገለገ ብቻ ነው። ይህ ምንም እንኳ የሆሄያት አደራደሩ የተንበለን ቤት መስሎ ቢገኝም ባረባብም ባነባበብም ቀደሰን መስሎ ስለሚገኝ የቀደሰ ሠርዌ ይባላል።

- የተንበለ ሠራዊት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ግእዝ.....አማርኛ

1) ቀበያውበጠ.....ቀላወጠ
2) ቀንጦሰጠ....ተሰለፈ/አሰለፈ
3) ዘርዜቀ.....ነፋ (የወንፊት)

ከዙህ እንደምታዩት ከተንበለ የሆዜያት አደራደር የተለየ አደራደር ቢኖራቸውም ተንበለን መስለው ስለሚወርዱ የተንበለ ሠራዊቶች ተብለዋል።

- የማህረከ ሠራዊቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ግእዝ.....አማርኛ

1) አንቃዕደወ.....አንጋጠጠ
2) ሰካዕለወ.....መነጠረ
3) አናሕሰየ.....አቃለለ/ይቅር አለ

ናቸው ከላይ እንደገለጥነው የማህረከ ቤቶች በራብዕ ይጀምራሉ ብለን ነበር። ነገር ግን እነዙህ ሠራዊቶች በግእዜ ጀምረዋል። ነገር ግን አረባባቸው ወይም አወራረዳቸው ማህረከን መስሎ ስለሚረባ የማህረከ ሠራዊት ይባላሉ።

- የሴሰየ ሠራዊቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ግእዝ.....አማርኛ

1) አሌለየ.....ማለደ/ገሠገሠ
2) አቅዛዘየ.....ቅዜዜ ቅዜዜ አለ
3) አንጌገየ.....ተቅበዘበዘ

ይህም የሴሰየ ቤቶች በኃምስ ይነሳሉ ብለን ነበር። እነዚህ ሠራዊቶች ግን በግእዜ ተነስተዋል። አረባባቸው ግን የሴሰየን ስለሚመስል የሴሰየ ወይም የዴገነ ሠራዊት ተብለዋል።

- የጦማረ ሠራዊቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ግእዝ.....አማርኛ

1) አልኖሰሰ.....ሹክ ሹክ አለ
2) አክሞሰሰ....ፍግግ ፍግግ አለ
3) ሶርየመ.....ለምድ አወጣ
4) ጎርየመ.....አገመ

እነዙህ ደግሞ የጦመረ ሠራዊቶች ናቸው። ሶርየመ እና ጎርየመ መነሻቸውም ጦመረን ይመስላል። አልኖሰሰ እና አክሞሰሰ ግን መነሻቸው ግእዜ ነው። ቢሆንም ግን ጦመረን መስለው የሚረቡ ስለሆነ የጦመረ ሠራዊት ይባላሉ።

- የክህለ እና የባረከ ሠራዊት የላቸውም። ማለት በሆሄያት አደራደርም ራሳቸውን የመሰለ ቃል እንጂ በሆሄያት አደራደር ተለይቶ ሲረባ ግን እነርሱን የሚመስል ቃል የለም ማለታችን ነው። እኒህን ጠንቅቆ ማወቅ ለቀጣዩ ትምህርታችን ወሳኝነት ስላለው ጠንቅቀን መላልሰን እናንብበው።

ረድኤተ እግዙአብሔር አይለየን።

ግእዝ ክፍል ፲፰

አእማድ

- አእማድ የሚባሉት አምስት ናቸው እነዚህም፦

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ቀተለ ገደለ
2) ተደራጊ ተቀትለ ተገደለ
3) አስደራጊ አቅተለ አስገደለ
4) ተደራራጊ ተቃተለ ተገዳደለ
5) አደራራጊ አስተቃተለ አገዳደለ

አንዳንድ ግሦች በአምስቱም አእማድ ላይዘልቁ ይችላሉ። ለምሳሌ ተሞተ አይባልም። አንዳንዱ ግሥ በአራቱ አንዳንዱ ግሥ በሦስቱ አንዳንዱ ግሥ ደግሞ በሁለቱ አእማድ ብቻ ሊዘልቅ ይችላል።

የስምንቱን አርእስተ ግሥ አእማድ ካወቅን የሌላውንም በአጭሩ ልንረዳው እንችላለን። ከላይ መጀመሪያ ላይ የቀተለን አርእስት አይተናል።

- ቀጥለን የቀደሰን እንመልከት፦

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ቀደሰ አመሰገነ
2) ተደራጊ ተቀደሰ ተመሰገነ
3) አስደራጊ አቀደሰ አስመሰገነ
4) ተደራራጊ ተቃደሰ ተመሰጋገነ
5) አደራራጊ አስተቃደሰ አመሰጋገነ

ይላል። በአስደራጊ ከአቀደሰ በተጨማሪ አቅደሰ፣ አስተቅደሰ ይላል። ተደራራጊው እና አደራራጊው ማለትም ተቃደሰ እና አስተቃደሰ ላልተው ይነበባሉ። ቀደሰ፣ ተቀደሰ እና አቀደሰ ግን ጠብቀው ይነበባሉ።

- ቀጥለን የተንበለን እንመልከት፦

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ተንበለ ለመነ
2) ተደራጊ ተተንበለ ተለመነ
3) አስደራጊ አተንበለ አስለመነ
4) ተደራራጊ ተተናበለ ተለማመነ
5) አደራራጊ አስተተናበለ አለማመነ ይላል።

- የባረከ ቤት ደግሞ እንደሚከተለው ነው፦

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ባረከ አመሰገነ
2) ተደራጊ ተባረከ ተመሰገነ
3) አስደራጊ አባረከ አስመሰገነ
4) ተደራራጊ ተባረከ ተመሰጋገነ
5) አደራራጊ አስተባረከ አመሰጋገነ

- የማሕረከ ደግሞ ቀጣዩ ነው።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ማሕረከ ማረከ
2) ተደራጊ ተማሕረከ ተማረከ
3) አስደራጊ አማሕረከ አስማረከ

4) ተደራራጊ ተማሓረከ ተመራረከ

5) አደራራጊ አስተማሓረከ አመራረከ

➢ የሴሰየ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ሴሰየ መገበ

2) ተደራጊ ተሴሰየ ተመገበ

3) አስደራጊ አሴሰየ አስመገበ

4) ተደራራጊ ተሴያሰየ ተመጋገበ

5) አደራራጊ አስተሴያሰየ አመጋገበ

የሴሰየ ቤት በተደራራጊ ከተሴያሰየ በተጨማሪ ተሲያሰየ፣ ተሰያሰየ ይላል።
በአደራራጊ ደግሞ ከአስተሴያሰየ በተጨማሪ አስተሲያሰየ አስተሰያሰየ ይላል።

➢ የክህለ ቤትን እንመልከት።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ክህለ ቻለ

2) ተደራጊ ተክህለ ተቻለ

3) አስደራጊ አክሃለ አስቻለ

4) ተደራራጊ ተካሃለ ተቻቻለ

5) አደራራጊ አስተካሃለ አቻቻለ።

- የጦመረ ቤት ነው።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ጦመረ ጻፈ

2) ተደራጊ ተጦመረ ተጻፈ

3) አስደራጊ አጦመረ አስጻፈ

4) ተደራራጊ ተጡዋመረ ተጻጻፈ

5) አደራራጊ አስተጡዋመረ አጻጻፈ

በተደራራጊ ከተጡዋመረ በተጨማሪ ተጥዋመረ፣ ተ ጦዋመረ ተጠዋመረ ይላል። በአደራራጊም ከአስተጡዋመረ በተጨማሪ አስተጠዋመረ ፣ አስተጦዋመረ፣ አስተጥዋመረ ይላል።የስምንቱ አርእስት አእማድ ይህን ይመስላል።

- ከዚህ በተጨማሪ የቆመን፣ የሚመን፣ እና የገብረን ቤቶች እንይና የዛሬውን ትምህርታችንን እናጠቃልላለን።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ቆመ ቆመ

2) ተደራጊ ተቆመ ተቆመ**

3) አስደራጊ አቀመ አስቆመ

4) ተደራራጊ ተቃወመ ተቋቋመ

5) አደራራጊ አስተቃወመ አቋቋመ

ለቆመ በተደራጊ ተቆመ አይባልም። ነገር ግን ቆመን የመሰሉ ግሦች ቢመጡ ይህንን ይመስላል ለማለት ተቆመ አልን እንጂ አይባልም። ለምሳሌ ሞአ....አሸነፈ ማለት ነው። በተደራጊ ተሞአ....ተሸነፈ ይላል። መስቀል ሞአ ሞት ተሞአ (መስቀል አሸነፈ ሞት ተሸነፈ) እንዲል ድጓ።

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ሤመ ሾመ

2) ተደራጊ ተሠይመ/ተሤመ ተሾመ

3) አስደራጊ አሤመ አስሾመ

4) ተደራራጊ ተሣየመ ተሻሻመ

5) አደራራጊ አስተሣየመ አሻሻመ

ይላል። በመጨረሻም የገብረን ቤት እንመልከት፦

ግእዜ አማርኛ

1) አድራጊ ገብረ አደረገ

2) ተደራጊ ተገብረ ተደረገ

3) አስደራጊ አግበረ አስደረገ

4) ተደራራጊ ተጋበረ ተደራረገ

5) አደራራጊ አስተጋበረ አደራረገ ይላል ማለት ነው።

ስለዚህ በዚህ መልኩ አእማደ ግሥን ማውጣት እንችላለን ማለት ነው።

ግእዝ ክፍል ፲፱

ዐበይት አናቅጽ እና አሥራው

፮) ከመ..... እንደ፣እንዲ፣እንዲያ፣እንዳ፣እንድ ይሆናሉ።በቀዳማይ በካልዓይ አንቀፅ ይነገራሉ።ከመ ተወልደ ሲል እንደተወለደ ማለት ነው። ከመገብረ ሲል እንዳደረገ ማለት ነው። ከመይገብር ሲል እንዲያደርግ ይላል። ከመእትወለድ ሲል እንድወለድ ማለት ነው። ከመን "ዘ፣በ" ያዳምቁታል። ዘከመ ይቤ መጽሐፍ፣ በከመ ይቤ መጽሐፍ ይላል።

፯) እስመ፣በዘ፣አርአያ..... እንደ፣እንዳ፣እንዲ፣እንዲያ፣እንድ ይሆናሉ። በቀዳማይ በካልዓይ ይነገራሉ። አርአያ አንቀፅ ይወሰንበታል። ማለትም የሚገቡት "ሠርዐ፣ ሰምዐ፣ ወሰነ፣ ሐገገ፣ ዐለመ፣ ረቀቀ፣ ጸሐፈ፣ መሀረ፣ ሰበከ" በሚሉት ግሦች ነው። አርአያ ሰምዐ፣ አርአያ ወሰነ ይላል። በእስመ እና በ"በዘ" ግን አንቀፅ አይወሰንባቸውም።

ምሳሌ በዘገብረ ጥበበ ተዐውቀ ጥበብን እንዳደረገ ታወቀ ማለት ነው። አእምሩ እስመ ተንሥአ ክርስቶስ ሲል ክርስቶስ እንደተነሣ እወቁ ማለት ነው። በ□በጽሐ በልዐ ሲል እንደደረሰ በላ ማለት ነው።

ግእዝ ክፍል ፴፰

፳) እመ፣ሶበ.....ቢ፣ባ፣ቢ፣ቢያ፣ብ ይሆናሉ።በቀዳማይ አንቀፅ በካልዓይ አንቀፅ ይነገራሉ። እመተሐውር ሲል ብትሄድ ማለት ነው። እመይበልዕ ሲል ቢበላ ማለት ነው። "እመ" ተለይቶ 'ሂ፣ኒ"ን ትራስ እያደረገ በቀዳማይ በካልዓይ ይነገራል።እመይጸግብ ወይም እመኒ ኢይጸግብ ወይም እመሂ ኢይጸግብ ይላል። ትርጉሙ ባይጠግብ ማለት ነው።

፳፩) እም.....ከ፣ካ፣ወዲያ፣ወዲህ ይሆናል።"እንተ፣እለ፣ዘ፣አመ፣ከመ"ን በር ከፋች ይዝ ይነገራል።ምሳሌ እምከመ ወሀብከነ ሲሳየ ዘእለት ወአራዘ ዘዓመት የአክለነ ዜንቱ ሀብት" ይላል።እምከመ ወሀብከነ ያለው ከሰጠኽን ማለት ነው። እምዘረወዩ አግማሊሁ ነሥአ ኢያውብር አዕኑገ ዘወርቅ ይላል። በዙህ እምዘረወዩ ያለው ከረኩ ወዲያ ማለት ነው።

፳፪) እመ....ከ፣ካ ይሆናል።እመን "ለ" ያዳምቀዋል።እመ በቀዳማይ በካልዓይ አንቀፅ ይነገራል። ምሳሌ እመ እግዙአብሔር ኢሐነፀ ቤተ ከንቶ ይጸምው እለ የሐንጹ ይላል። እግዙአብሔር ቤትን ካልሠራ የሚሠሩት በከንቱ ይደክማሉ ማለት ነው።

፳፭)እስከ.....እስኪ፣እስካ፣እስኪያ፣እስክ ይሆናል።በትርፍ አማርኛ ድረስ ይሆናል።"ነ፣ኅበ፣አመ፣ሶበ"ን በር ከፋች ይዝም ሳይዜም በቀዳማይ በካልዓይ ይነገራል። ምሳሌ፦ እስከ ይመጽእ ሲል እስኪመጣ ማለት ነው። እስከ እገብር ሲል እስካደርግ ማለት ነው። እስከ ትመጽእ ሲል እስክትመጣ ማለት ነው።

እስከ አመይመጽእ ወልደ እጓለእመሕያው ሲል የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ ማለት ነው። ፍጻሜ ያለው ፍጻሜ የሌለው እስከ አለ። ፍጻሜ ያለው እስከ ሲገባ እስከ አመ ይመጽእ ወልደ እጓለእመሕያው ያለው ነው። ፍጻሜ የሌለው እስከ ሲገባ ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት ይላል።

፳፮) አመ፣ሶበ፣ጊዛ፣ ዕለተ፣ዓመተ፣ መዋዕለ....ጊዛ ጊዛያት ዘመን ዘመናት ይሆናሉ። በቀዳማይ በካልዓይ ይነገራሉ። ምሳሌ፦ ሶበ ጸዋእክዎ ለእግዙአብሔር ሲል እግዙአብሔርን በጠራሁት ጊዜ ተብሎ ይተረጎማል። ጊዜ "በ"ን ይዝም ሳይዜም ይነገራል። በን ሳይዜ ጊዜ ጸዋእኩኪ በአስተብቁዖ ይላል ።በን ይዝ ደግሞ በጊዜ ይመጽእ ሐዳስ በዓለ ቤት ይላል።

ዕለተን "አመ፡ብ" ያዳምቁታል። በዕለተ በላእክሙ/አመ ዕለተ በላእክሙ እንትኮ በለሰ ሞተ ትመውቱ።በለስን በበላችሁ ጊዛ ሞትን ትሞታላችሁ ማለት ነው። አመ ዕለተ እጼውዐከ በምጠራህ ጊዛ ይላል። መዋዕለ ሲገባ በመዋዕለ ነግሠ ሰሎሞን ተፈሥሑ እስራኤል ይላል። ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ እስራኤል ተደሰቱ ማለት ነው።

ዓመተ ሲገባ በዓመተ ሞተ ያዜያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዙአብሔር ይላል።ያዜያን በሞተ ጊዛ እግዙአብሔርን አየሁት ማለት ነው። ጊዛ/ሶበ/አመ ተሰቅለ ክርስቶስ ፀሐይ ጸልመ ይላል።

፲፫) እንተ፣ዘ፣እለ.....የ ይሆናሉ። በቀዳማይ በካልዓይ አንቀፅ ይነገራሉ። ዘመጽአ ሲል የመጣ ማለት ነው። ዘይመጽእ ሲል የሚመጣ ማለት ነው።ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዙአብሔር እንዲል። ባለቤት ሲኖር ቅጽል ባለቤት ሲቀር በቂ ይሆናሉ። ዘ በአንድም በብዘም ይገባል።

ምሳሌ ዘከብሩ ብሎ የከበሩ ይላል። ዘከብረ ብሎ የከበረ ይላል። ለሴት ሲሆን እንተ መጽአት የመጣች ይላል። እለ መጽኡ ሲል ለብዘዎች የመጡ ተብሎ ይተረጎማል።

፲፬) ኀበ፣ኀበኀበ፣ከመ፣ከመከመ፣ እንተ፣ለለ፣በበ.....እየ ይሆናሉ። እንተ በቀዳማይ አንቀጽ ይገባል።ነፍስ ርኅብት እንተ ጸግበት ተአኵተከ ይላል። ከመ፣ከመከመ፣ ኀበ፣ኀበኀበ፣ለለ በቀዳማይ እና በካልዓይ አንቀፅ ይገባሉ። ለለሜመ፣ ለለይሠይም ይላል ትርጉሙ እየሾመ ማለት ነው።

ወስብሐት ለእግዙአብሔር።

ግእዝ ክፍል ፶፱

እርባ ቅምር ክፍል ፩

❖ እርባ ቅምር የሰዋስወ ግእዜን አጠቃላይ አዋጅ የምንማርበት ትምህርት ነው። በጠቅላላ ሰዋስው በሁለት ይከፈላል። እኒህም ዘር እና ነባር ናቸው። ዘር የሚባሉት ከግሥ የሚወጡ ስሞችን፣ ቅጽሎችን፣ እና ሌሎችንም እርባታዎችን ነው። ነባር የሚባሉት ደግሞ ከግሥ የማይወጡ አገባቦችን፣ ስሞች፣ የሀገር የቦታ እና የሰው ስሞችን፣ እንዲሁም ቀዳማይ እያላቸው ካልዓይ ሣልሳይ የሌላቸው አንቀጾች ናቸው።

አዋጅ ፩

✓ ሳቢ ከተሳቢ ዘርፍ ከባለቤት በሁለት ነገር ይያያዚል። እኒህም 'ለ' እና 'ዘ' ናቸው ።'ዘ' በንዑስ አንቀጽ ሲነገር ብሂል ዘጊዮርጊስ ይላል። 'ለ' በንዑስ አንቀጽ ሲገባ ብሂሎቱ ለጊዮርጊስ ይላል። ብሂሉ ለጊዮርጊስ ወይም ብሂሎት ዘጊዮርጊስ ግን አይልም።

✓ ዘርፍ ከባለቤት የሚባለው መናበብ የሚችል ሁሉ ነው። ንዋዩ ለባዕል፣ ንዋይ ዘባዕል፣ ንዋየ ባዕል ሦስቱም አንድ ዓይነት ትርጉም አለው። የሀብታም ገንዘብ ማለት ነው። ከዘ በተጨማሪ "እለ እና እንተ" ዘርፍ ያያይዚሉ። "እንተ" ከብዘ ወደ አንድ፣ ከአንድ ወደ አንድ ያያይዚል። ምሳሌ ሰማይ እንተ አምላክ፣ አምላክ እንተ ሰማያት ይላል። "እለ" ከአንድ ወደ ብዘ ከብዘ ወደ ብዘ ያያይዚል። ምሳሌ መላእክት እለ አምላክ፣ መላእክት እለ ሰማያት ይላል። "ዘ" እና "ለ" ግን ሁሉንም ያያይዚሉ።

✓ የ"ለ" የዘርፍ ዘርፍ ድፋት የለውም። አስካለ ወይነ ቄርሎስ ለማለት ለቄርሎስ አስካለ ወይኑ አይልም። ቤታ ለማርያም፣ ለማርያም ቤታ፣ ቤት ዘማርያም፣ ዘማርያም ቤት፣ ቤተ ማርያም ቢል ተማሳሳይ ነው ትርጉሙ ሁሉም የማርያም ቤት ማለት ነው። ቤተ ማርያም ሲል ማርያም የቤት ዘርፍ ይባላል። ቤት ዘማርያም ሲልና ቤታ ለማርያም ሲል "ለ እና ዘ"

ዘርፍ አያያዥ ይባላሉ። ዘማርያም ቤት ሲልና ለማርያም ቤታ ሲል ደግሞ "ለ እና ዘ" ዘርፍ ደፊ ይባላሉ።

አዋጅ ፪

- ✓ የግሥ መነሻ ፊደላት መራኁት ይባላሉ። መራኁት አምስት ናቸው። እኒህም ግዕዜ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ እና ሳብዕ ናቸው።በግዕዜ ቀደሰ፣ በራብዕ ባረከ፣ በኃምስ ሴሰየ፣ በሳድስ ክህለ፣ በሳብዕ ጦመረን የመሳሰሉ ናቸው። ከእነዙህ በቀር ግሥ በካዕብ እና በሣልስ አይነሳም። የግሥ መድረሻዎች ሁለት ናቸው። እኒህም ግዕዝና ኃምስ ናቸው። በግዕዜ ከ 'ሀ' እስከ 'ፈ' ያሉ ግሦች ናቸው። በኀምስ ግን ይቤ ብቻ ነው። 'ይቤ'ም ነባር አንቀጽ ይባላል።

አዋጅ ፫

- ✓ "ወ" እስከ ሦስት ያወርዳል።ይህም ማለት ለምሳሌ ዘሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ ይላል። ይህም ዘሐመ ወዘሞተ ወዘተቀብረ ወዘተንሥአ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። 'ዘ' ለሦስቱ ማለትም ለሞተ፣ ለተቀብረ፣ እና ለተንሥአ እንደወረደችላቸው አስተውል። በዋዌ የማይወርዱ ቀለማት ሦስት ናቸው። እኒህም "ሀ፣ ከ፣ ዊ" ናቸው።
- ✓ ጸውዐ ሙሴሀ ወአሮን አይልም። ሙሴንና አሮንን ጠራ ለማለት የግድ ወአሮንሀ ማለት አለበት። አምላክ ሰማያዊ ወምድራዊ ይላል እንጂ "ወ" ያወርድልኛል ብለን አምላክ ሰማያዊ ወምድር አንልም "ወ" ሦስቱን ማለትም "ዊ፣ሀ፣ከ" ን አያወርድምና። በላዕነ ሥጋከ ወሰተይነ ደመከ ይላል እንጂ ወሰተይነ ደመ አይልም።

አዋጅ ፬

- ✓ ሳይጠሩ የሚያስሩ ሦስት ናቸው። እነዙህም ውእቱ፣ ሀለወ እና ደለወ ናቸው።ለምሳሌ አምላክ ሀያል ብሎ አምላክ ሀያል ነው ይላል። "ነው" የሚለውን ፍች ያመጣው "ውእቱ" ሳይጠራ (ሳይጻፍ) ነው። አነ በአብ ሲል ትርጉሙ እኔ በአብ አለሁ ማለት ነው። "አለሁ" የሚለውን ያመጣው "በ" ነው።

- ✓ ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ሲል ትርጉሙ ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድ ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል ማለት ነው። "ይገባል" የሚለውን ትርጉም ያመጣው "ለ" ነው። ተጠርተው የሚያሥሩ ሦስት ናቸው። እኒህም ቀዳማይ አንቀጽ፣ ካልዓይ አንቀጽና ሣልሳይ አንቀጽ ናቸው።

አዋጅ ፭

- ✓ ባዕድ ቀለማት ሦስት ናቸው። እነዙህም "መ፣ተ፣አ" ናቸው። ከእነዙህም "መ" ከግእዜ እስከ ሳብዕ ይነገራል። መ ሲገባ ቀደሰ ብሎ መቅደስ፣ ሙ ሲገባ ወረደ ብሎ ሙራድ፣ ሚ ሲገባ ነሐሰ ብሎ ሚንሓስ፣ ማ ሲገባ ጎደረ ብሎ ማጎደር፣ ሜ ሲገባ ተኬነው ብሎ ሜኮኖት፣ ም ሲገባ ቆመ ብሎ ምቅዋም፣ ሞ ሲገባ ወፀፈ ብሎ ሞፀፍ ይላል። 'ተ" በግእዜ፣ በራብዕ፣ በኃምስ እና በሳድስ ይነገራል።

- ✓ ተ ሲገባ ወደሰ ብሎ ተውዳስ፣ ታ ሲገባ ጎሠሠ ብሎ ታጎሣሥ፣ ቴ ሲገባ ረግዐ ብሎ ቴሮጋ፣ ት ሲገባ ሐረመ ብሎ ትሕርምት ይላል። "አ" በግእዜና በሳድስ ይነገራል። አ ሲገባ መሰለ ብሎ አምሳል፣ ሠገረ ብሎ እግር ማለቱን ያሳያል።

ግእዝ ክፍል ፪

አዋጅ ፮

- ➢ ከቀዳማይ አንቀጽ ላይ በባዕድነት እየተጨመሩ ካልዓይ አንቀጽን፣ ዘንድ አንቀጽን፣ እና ትእዚዜ አንቀጽን የሚያስገኙ ፊደላት አሥራው ይባላሉ። እነዙህም አራት ናቸው። "ተ፣ነ፣አ፣የ" ናቸው። እኒህም በአመል ሲገቡ ግእዝ፣ራብእ ይሆናሉ። ያለ አመል ሲገቡ ሳድስ ይሆናሉ። በግእዜ ሲገቡ አእመረ ብሎ የአምር ይላል።

- ➢ በራብዕ ሲገቡ አጽደልደለ ብሎ ያጽደለድል ይላል። በሳድስ ሲገቡ ቀደሰ ብሎ ይቄድስ ይላል። "ተ" በይእቲ፣ በአንተ፣ በአንቲ፣ በአንትሙ፣ እና በአንትን ይገባል። "የ" በውእቱ፣ በውእቶሙ፣ እና በውእቶን ይገባል። "አ" በአነ

ሲገባ "ነ" ደግሞ በንሕነ ይገባል። አሥራው በሁለተኛ መደቦች ማለትም በአንተ፣ በአንትሙ፣ በአንቲ እና በአንትን በትእዚዜ አንቀጽ አይገኙም።

አዋጅ ፭

- በአንተ ትእዚዜ ሁለት ቀለም ሆኖ በሳድስ የደረስ ሥርዓተ ንባቡ ተጣይ ነው። ኩን፣ ሑር ተጣይ ናቸው "ለ" እና "ኢ" ግን ሥርወ ቀለሙን አውርደው ጥለው ያስነሱታል። አትቁም ለማለት ኢትቁም ይላል። ቁም ለማለት ደግሞ ለትቁም ይላል። ሑር ንባቡ ተጣይ ነው። ወ ሲጨመርበት ወሑር ሲል ግን ሰያፍ ይሆናል።

አዋጅ ፮

- የ"የ" ራብዕ አመሉ "አ" ባለበት ቀለም በአሉታ በአስደራጊና በአደራራጊ ከቀዳማይ እስከቦዜ ይገኛል። የአእመረ አሉታ ኢያእመረ፣ የአእምሮ አሉታ ኢያእምሮ፣ የአእሚሮ አሉታ ኢያእሚሮ፣ የአእማሪ አሉታ ኢያእማሪ፣ ማለቱን አስታውል።

አዋጅ ፯

- አራት ዓይነት ስሞች አሉ። እነዙህም የባሕርይ ስም፣ የግብር ስም፣ የተቀብዖ ስም እና የተጽውዖ ስም ናቸው። የተጸውዖ ስም የሚባለው መጠሪያ ስማችን ነው። ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ኤልያስ፣ አበበ፣ የመሳሰሉት ናቸው። የግብር ስም የሚባለው ወታደር፣ ዶክተር፣ ተማሪ፣ ገበሬ የመሳሰሉት ናቸው። የተቀብዖ ስም የሚባላው ስንጠመቅ ስንሾም የምንሰጠው ስም ነው። ይህም ወለተ ሐና፣ ወልደ ሩፋኤል የመሳሰለው ነው። ጳጳሳት ሲሾሙ የተሰጣቸው ስምም ከዙህ ይመደባል። አቡነ ዲዮናስዮስ፣ አቡነ ማትያስ ወዘተ ነው።

- የባሕርይ ሥም ለፈጣሪ ይነገራል። ለፍጡርም ሰው፣ እንስሳት፣ ወፍ ወዘተ የባህርይ ስም ይባላል። የመድበል ስም የሚባልም አለ። እስራኤላውያን በይሁዳ አይሁድ፣ በያዕቆብ እስራኤል፣ ተብለዋል። በገቢር ጊዛ ይሁዳህ፣ እስራኤልህ ይላል። የመድበሉ ግን አይሁደ፣ እስራኤለ ይላል። በሱራፊ ሱራፌል፣ በኪሩብ ኪሩቤል ይላል። ይህም ገቢር ሲሆን ኪሩቤለ ሱራፌለ ይላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

አዋጅ ፤

- ሰሚዎች አራት ናቸው። እኒህም አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ እና አንትን ናቸው። ለምሳሌ አፍቀርከ ጽድቀ ሲል አቤቱ እውነትን ወደድክ ይላል። በዙህ "አንተ" ሰሚ ሆኖ የተነግረ ነው። አሰሚዎች ደግሞ አራት ናቸው። እነዚህም አንቀጽ፣ አገባብ፣ ዘርፍ እና ባለቤት ናቸው። የአንቀጽ ሰሚ ከፈቀደው ሆኖ ይሰማል።

- አፍቀርከ ጽድቀ፣ አፍቀርከ ጽድቀ ይላል። የአገባብ፣ የዘርፍና የባለቤት ሰሚዎች ግን ወይ በመጀመርያ ወይ በመጨረሻ ይሰማሉ። አምላክ ደምከ ውሕዘ ሲል የባለቤት ሰሚ፣ አምላክ ደመገቦከ ውሕዘ ሲል የዘርፍ ሰሚ፣ መንግሥተ ሰማይ መጽኡ ጻድቃን ኀቤኪ ሲል የአገባብ ሰሚ ይባላል።

አዋጅ ፤፩

- ዘርፍ ይዘው፣ አገባብ ወድቆባቸው ወደፊት እንጂ ወደኋላ የማይስቡ አራት ናቸው። እነዙህም ሳቢዘር፣ ንኡስ አንቀጽ፣ ሣልስ ቅጽል እና ሳድስ ቅጽል ናቸው።በሳቢዘር ሰማየ ለዕርገት ኤልያስ ተግሀ አይልም። ለዕርገት ሰማየ ኤልያስ ተግሀ ይላል እንጂ። ይህ አገባብ ወድቆበት ነው። ዘርፍ ይዝም ሰማየ ዕርገተ ኤልያስ ተዐውቀ አይልም። ዕርገተ ኤልያስ ሰማየ ተዐውቀ ቢል እንጂ።

- በንዑስ አንቀጽ ገነተ ለበዊእ ጻድቃን ተግሁ አይልም።ለበዊእ ገነተ ጻድቃን ተግሁ ይላል እንጂ። ገነተ በዊአ ጻድቃን ተዐውቀ አይልም። በዊአ ጻድቃን ገነተ ተዐውቀ ይላል እንጂ።

- በሣልስ ቅጽል ምሥጢረ ለአእማሪ ጴጥሮስ ጸውዖ እግዙአብሔር አይልም። ለጴጥሮስ አእማሪ ምሥጢረ ይላል እንጂ። ምሥጢረ አእማሬ ልብ ጴጥሮስ ተጸውዐ አይልም። ጴጥሮስ አእማሬ ልብ ምሥጢረ ተጸውዐ ይላል እንጂ።

- በሳድስ ቅጽል በኀበ እስራኤል ለክቡር ዳዊት አንገሦ ሳሙኤል አይልም። ለዳዊት ክቡር በኀበ እስራኤል አንገሦ ሳሙኤል ይላል እንጂ። በኀበ እስራኤል ክቡረ መንግሥት ዳዊት ነግሠአይልም።

አዋጅ ፲፪

- በዝርዝር ጊዜ ለገቢር ለተገብሮ የሚችሉ አራት ናቸው። እነዙህም የውእቶሙ፣ የይእቲ፣ የውእቶን እና የአነ መዘርዘር ናቸው። ይሄውም ሐነጹ ቤቶሙ፣ ተሐንጸ ቤቶሙ፣ ሐነጸት ቤታ፣ ተሐንጸ ቤታ፣ ሐነጽኩ ቤትየ፣ ተሐንጸ ቤትየ፣ ሐነጻ ቤቶን፣ ተሐንጸ ቤቶን ይላል።

ግእዝ ክፍል ፶፩

ግእዜ	አማርኛ	English
ጠፈር	ጣራ	Roof
መሠረት	መሠረት	Foundation
አረፍት	ግድግዳ	Wall
ማይ	ውሃ	Water
እሳት	እሳት	Fire
ዋካ	ብርሃን	Light
ጽልመት	ጨለማ	Darkness
ነፋስ	ነፋስ	Wind
ሰብእ	ሰው	Human
መጽሔት	መስታዎት	Mirror

❖ #የቦታ #ስሞች

ግእዜ.	አማርኛ.	English.
ሰማይ	ሰማይ	Sky
መሬት	መሬት	Earth

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ሀገር	ሀገር	Country
ደወል	አውራጃ	Province
ደብር	ተራራ	Mountain

❖ #የቤት #እንስሳት

ግእዜ.	አማርኛ.	English.
ጠሊ	ፍየል	Goat
በግዕ	በግ	Sheep
ላሕም	ላም	Cow
ብዕራይ	በሬ	Ox
ከልብ	ውሻ	Dog
አድግ	አህያ	Donkey
ባሥር	ሥጋ	Meat

❖ #የዱር #አራዊት

ግእዜ.	አማርኛ.	English.
ነምር	ነብር	Tiger
አንበሳ	አንበሳ	Lion
ሆባይ	ዝንጀሮ	Monkey
ነጌ	ዜሆን	Elephant
ዜህብ	ጅብ	Hyena
ቀኑንጽል	ቀበሮ	Fox

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

❖ #የአካል #ክፍሎች

ግእዜ.	አማርኛ.	English.
እግር	እግር	Leg
ርእስ	ራስ	Head
ስእርት	ጸጉር	Hair
እድ	እጅ	Hand
መትከፍት	ትክሻ	Shoulder
ዕዝን	ጆሮ	Ear
ዓይን	ዓይን	Eye
አፍ	አፍ	Mouth
ነፍስ	ነፍስ	Soul
ሥጋ	ሥጋ	Flesh
ግእዜ.	አማርኛ.	English.
ንጉሥ	ንጉሥ	King
ልዑል	ልዑል	Prince
ጸሎት	ጸሎት	Prayer
ሥላሴ	ሥላሴ	Trinity
ጾም	ጾም	Fasting
ምንታዌ	ሁለትነት	Dualism

ግእዝ ክፍል ፶፪

እርባ ቅምር ክፍል ፪

አዋጅ ፩

- አእማደ አርእስት የሚባሉ አምስት ናቸው። እነዙህም አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራራጊ እና አደራራጊ ናቸው። ተደራጊ በግድ ሲስብ ፩ በውድ ሲስብ ፭ ተሳቢዎችን ይስባል። በግድ አንድ ሲስብ ተሰቅለ አምላክ ይላል። አምላክ ለተሰቅለ እንደተሳበ አስተውል። በውድ አምስት ሲስብ አምላክ ተሰቅለ በመስቀል በቀራንዮ በዕለተ ዓርብ በጊዛ ቀትር ይላል።
- አድራጊ በግድ ሁለት ሲስብ ሰቀሉ አይሁድ አምላከ ይላል። በውድ ስድስት ሲስብ ኢዮአብ አሜሳይህ ቀተለ በሰይፍ በእንተ ሚመቱ እምቅንዐቱ አመ የዐርግ ጎቤሆሙ ለእስራኤል ይላል።
- ተደራራጊ በግድ ሁለት ሲስብ አቤሴሎም ተቃተለ ምስለ ኢዮአብ ይላል። በውድ ስድስት ሲስብ ተቃተለ ሳኦል ምስለ አጋግ በዙናት ህየንተ ግፍዐ እስራኤል እምቃለ ሳሙኤል እምድኅረ ዐርገ ጎቤሁ ለናዖስ አሞናዊ ይላል።
- አስደራጊ በግድ ሦስት ሲስብ ሳኦል አቅተለ ዳዊትሃ ጎልያድሃ ይላል። ትርጉሙ ሳኦል ዳዊትን ጎልያድን አስገደለ ማለት ነው። በውድ ሰባት ሲስብ ሳኦል አቅተለ ጎልያድሃ ዳዊትሃ በዕብነ ሞጸፍ በእንተ ግፍዐ እስራኤል እም ትእዚዘ እንዘ ይንእስ እምአኃዊሁ ሰብዐቱ በቤተ እሴይ አቡሁ ይላል።
- አደራራጊ በግድ ሦስት ሲስብ ዳዊት አስተወጸ አሳሔልህ ምስለ ፈረስ ይላል።
- በውድ ሰባት ሲስብ አስተቃተለ ሳሙኤል ሳኦልህ ምስለ አጋግ በዙናት ህየንተ ግፍዐ እስራኤል እመንግሥቱ አመ አዘዘ አምላክ በመሴፋ ይላል።

አዋጅ ፪

- ካባር አምስት ናቸው። እኒህም የአንቀጽ፣ የአገባብ፣ የስም፣ የቦታ እና የሰዋስው ናቸው። የአንቀጽ ቦ፣ አልቦ የመሳሰሉ ናቸው። የአገባብ እስመ፣ እንዘ የመሳሰሉ ናቸው። የስም ሙሴ፣ ኤልያስ የመሳሰሉት ናቸው። የቦታ ፋርስ፣ ባቢሎን የመሳሰሉት ናቸው። የሰዋስው ኮከብ፣ ፆም የመሳሰሉት ናቸው።

አዋጅ ፫

- ፍርቅ አምስት ናቸው።እኒህም የአንቀጽና የአገባብ፣ የሰምና የወርቅ፣ የዘርፍና የባለቤት፣ የቅጽልና የባለቤት፣ የሳቢና የተሳቢ ናቸው። የሰምና የወርቅ ዜናም መጽአ ሆሳእና የሚለውን ዓይነት ነው። ማሰሪያ አንቀጹን አልፎ ዜናም እና ሆሳእና አይመሰልም።
- የዘርፍ እና የባለቤት ደሙ በመስቀል ለአምላክ ውሕዘ የሚለው ነው። ደሙ እና ለአምላክ የሚሉት ቃል በመስቀል በሚለው ቃል ተፈራቀዋል። የቅጽልና የባለቤት አምላከ ሰማይ ክቡር ዳዊት በጎበ እስራኤል አይልም። የሳቢና የተሳቢ ሰማየ ለዕርገት አይልም።

አዋጅ ፬

- "ን" የሚሆኑ አገባባት አምስት ናቸው። እኒህም "ለ፣ በ፣ እንተ፣ ውስተ፣ ላእለ" ናቸው። 'ለ' በሰብሐ እና በዘመረ ይገባል። ሰብሑ ለስመ እግዙአብሔር ሲል የእግዙአብሔርን ስም አመስግኑ ማለት ነው። 'በ' ሲገባ ቀስተ ዮናታን ኢተቀብዐት በቅብዕ ይላል።
- የዮናታን ቀስት ቅቤን አልተቀባችም ማለት ነው። 'እንተ' ሲገባ ፈነዎሙ እንተ ባሕቲቶሙ ብቻቸውን ላካቸው ይላል። 'ላእለ' ሲገባ ነጸረ እግዙአብሔር ላእለ አቤል ይላል። 'ውስተ' ሲገባ ነጸሩ ውስተ ግብረ ጴጥሮስ ይላል። ትርጉሙ የጴጥሮስን ሥራ ተመለከቱ ማለት ነው።

አዋጅ ፭

- ✓ ከአንድ እስከ አስር ያሉ የግእዜ ቁጥሮች ሲሳቡ ካእብ የነበረው የመጨረሻ ፊደላቸው ወደ ግእዜ ይለወጣል። ይህም አሐዱ፣ ክልኤቱ፣ ሠለስቱ፣

አርባዕቱ፣ ኀምስቱ፣ ስድስቱ፣ ሰብዓቱ፣ ሰመንቱ፣ ተስዓቱ፣ አሠርቱ ያለው ሲሳብ አሐደ፣ ክልኤተ፣ ሠለስተ፣ አርባዕተ፣ ኀምስተ፣ ስድስተ፣ ሰብዓተ፣ ሰመንተ፣ ተሰዐተ፣ አሠርተ ይላል። ሥርዓተ ንባባቸውም ተጣይ ነው። "ሰ" ወዳቂ ንባብ ያላቸውን ቃለት ተነስተው እንዲነበቡ ያደርጋል። በተጨማሪም "ዘ" በሚለው ዐቢይ አገባብ ሲወድቅ "ዘሰ" ሲል ተነስቶ ይነበባል።

ግእዝ ክፍል ፱ቮ

አዋጅ ፮

- መሣግር የሚሆኑ አምስት ናቸው። እነዙህም ሀ፣ረ፣አ፣ወ፣ዘ ናቸው። ሀ መሀረ ብሎ ይሜህር ይላል። ረ ጠፈረ መብሎ ይጠፍር ይላል። አ ርእየ ብሎ ይሬኢ ይላል። ወ ወጠነ ብሎ ይዌጥን ይላል። ዘ ተዜጎረ ብሎ ይዛጎር ይላል። መሣግር ያሰኛቸው በካልዓይ አንቀጽ ርእሳቸውን ትተው የቀተለውን በቀደሰ የቀደሰውን በቀተለ የሚያረቡ ሆነው ስለተገኙ ነው።

አዋጅ ፯

- የሀገር ስም ለገቢር ለተገብሮ ይከታል። ወረደ ባቢሎን ሲል ወደ ባቢሎን ወረደ ማለት ነው። ፍጹም ሳድስ.የሆነ የሀገር ስም ግን በገቢር ጊዛ ግእዜ ያናግራል። ግብጽ፣ ጽርዕ፣ ገቢር ሲሆኑ ግብጻ፣ ጽርዐ ይላሉ።

አዋጅ ፰

- ✓ ቅጽል የሚሆኑ የሚከተሉት ናቸው። ንዑስ አገባቦች፣ ደቂቅ አገባቦች፣ አኃዜ፣ ወገን ቅጽል፣ ዘር፣ ነባር፣ ግልጠዘ እና ውስጠ ዘ ናቸው። ንዑስ፣ ደቂቅና አኃዜ በፊት በፊት ይቀጸላሉ። አይ ልሳን፣ ምንት ነገር፣ ውእቱ ሚካኤል፣ ዜንቱስ ብእሲ፣ አሐዱ አምላክ ይላል።
- ✓ ወገን ቅጽል ኢየሱስ ናዜራዊ፣ ከለዳዊ አብርሃም ይላል። ዘርዕ ደግሞ ይስሐቅ ዘርዐ አብርሃም ይላል። ነባር ቅዳሴ ጥዳ መላእክት ይላል። ግልጠዘ እና ውስጠዘ ክቡር አብርሃም ዘተለዐለ እም ኩሉ ይላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

አዋጅ ፱

- ገቢር ቃላት ሰባት አገባባትን ያመጣሉ። እኒህም ለ፣ በ፣ ምስለ፣ እም፣ ከመ፣ ኀበ፣ እስከ ናቸው። አብርሃም መሐከ ነዳየ ሲል አብርሃም ለነዳይ ራራ ማለት ነው። ቆመ ምድረ ሲል በምድር ቆመ ማለት ነው። አማኑኤል ተሰቅለ ፈያተ ሲል አማኑኤል ከሽፍቶች ጋራ ተሰቀለ ማለት ነው። ተንሥአ ቀራንዮ ሲል ከቀራንዮ ተነሳ ማለት ነው። ኪሩቤል እንደሰው ቆሙ ማለት ነው።

- በጽሐ ሀገረ ሲል ወደ ሀገር መጣ ወይም እስከ ሀገር መጣ ይላል።ከዙህ በተረፈ አማርኛ አኽሎ፣ መስሎ፣ ሆኖ፣ ብሎ፣ ተብሎ፣ አሰኝቶ፣ አድርጎ፣ ኛ፣ ነት ይሆናል። መጽአ ሰይጣን ደብረ ይላል። ሰይጣን ተራራ አህሎ/መስሎ መጣ ማለት ነው። ሰይጣን ወሀበ ለነዳይ ወርቀ ዕብነ ይላል ትርጉሙ ሰይጣን ለችግረኛ ድንጋይን ወርቅ ነው ብሎ ሰጠ ማለት ነው።

- ክርስቶስ ተሰቅለ ጎጥአ ሲል ክርስቶስ ጎጥእ ተብሎ ተሰቀለ ማለት ነው። ንጉሥ ሜሞ ለገብሩ ሊቀ ሲል ንጉሥ አገልጋዩን መሪ አድርጎ/አሰኝቶ ሾመው ማለት ነው። ሐንካሳን የሐውሩ ዜእበ ሲል ዜእበ ጅብኛ ማለት ነው። ተሠይመ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ሲል ሊቀ ሐዋርያነት ማለት ነው።

አዋጅ ፲

- ✓ "በ" ከጊዛ ከቦታ በተጨማሪ በስድስት ግሦች ይወጣል። ግሶቹም ዐብየ፣ ንእሰ፣ ዐረየ፣ ሐብረ፣ ሰክረ እና ቀደመ ናቸው። "እም"ም ከጊዛ ከቦታ በተጨማሪ በሰባት ግሶች ይወጣል። ግሶቹም ተጸነሰ፣ ነድየ፣ ርኅበ፣ ጸመ፣ ጸምአ፣ ተዐርቀ፣ ተጎረመ፣ ዐብየ፣ ንእሰ ናቸው።

አዋጅ ፲፩

- ✓ ምእላድ የሚሆኑ ቀለማት ስምንት ናቸው እነዙህም አ፣ ን፣ ት፣ ሙ፣ ይ፣ ው፣ ህ፣ ል ናቸው። ኩሎሙ፣ አድባር፣ ጻድቃን፣ ካህናት፣ አንስትያ፣ አበው፣ ኪሩቤል፣ መጣብሕ ይላል።

አዋጅ ፲፪

- ✓ ቸልታ የሚሆኑ አገባባት ፲፩ ናቸው። እኒህም እንዘ፣ ኢ፣ ወ፣ እም፣ ምስለ፣ ቦዜ፣ በ፣ ግእዜ፣ ራብእ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ናቸው።

ግእዝ ክፍል ፱፩

ዘመድ ሙሻ ዘር

❖ ሙሻ ዘር የሚባል ተናባቢ ቃል ነው። አንድም ሙሻዘር ማለት ማያያዣ ማጣበቂያ ማለት ነው። አንድ ቃል ተናቦ አገባብ ሲያወጣ ሙሻ ዘር ይባላል። ሙሻ ዘር የሚሆኑ ቀለማት ፯ ናቸው። እነዙህም ቀዳማይ አንቀጽ፣ ካልዓይ አንቀጽ፣ ሣልሳይ አንቀጽ፣ ዘንድ አንቀጽ፣ ቦዜ አንቀጽ፣ ሣልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል፣ መድበል፣ ሳቢዘር እና ንዑስ አንቀጽ ናቸው።

ከእነዙህም አምስቱ ማለትም ቀዳማይ፣ ካልዓይ፣ ሣልሳይ፣ ዘንድ፣ ቦዜ፣ ዘርዜረው ሳይናበቡ ስድስቱ ግን ማለትም ንዑስ አንቀጽ፣ ሳቢዘር፣ ሣልስ ቅጽል፣ ሳድስ ቅጽል፣ ባዕድ ቅጽል እና መድበል እየተናበቡ ዘጠኝ አገባባትን ያመጣሉ። እኒህም:- በይነ/እንበይነ/በእንተ/ህየንተ/ፍዳ/ተውላጠ/አስበ/ዕሴተ/ቤዚ/ዓይነ ስለአንድ፣ ለ፣ በ፣ እም፣ ከመ፣ ምስለ፣ ኀበ፣ እስከ፣ እንበለ እና ግእዜ ናቸው። እያንዳንዳቸው እንዴት እንደሚወጡ ቀጥለን እንመለከታለን።

ቀዳማይ፣ ካልዓይ፣ ሣልሳይ ሲቀሩ ውእቱ ከሁሉም ይመረምራል።

#ለ፣በይነ (ለ፣ስለ) ሲወጡ:-

✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለዘካርያስ አብ መዊተ ዮሐንስ ወልድ ሲል ትርጉሙ ለልጅ ዮሐንስ መሞት ለዘካርያስ አባት ይገባል ይላል።ወይም ደግሞ ስለ ልጅ ዮሐንስ መሞት ለ□ካርያስ አባት ይገባል ይላል።

✓ ሳቢዘር:- ለአምላክ ኦርዮ ሙተተ ሔዋን ቤርሳቤሕ ይላል። ትርጉሙ ለቤርሳቤሕ ሔዋን መሞት ለአምላክ ኦርዮ ይገባል። ወይም ስለ ቤርሳቤሕ ሔዋን መሞት ለኦርዮ አምላክ ይገባል ይላል።

✓ ሣልስ ቅጽል:- ነስሐ ዳዊት መስፍን ቀታሌ ቤርሳቤሕ መርዓት ኦርዮንሀ ብእሴ ይላል። ትርጉሙ ኦርዮን ሰውየን ስለ/ለ ሙሽራ ቤርሳቤሕ የገደለ ዳዊት ተጸጸተ ይላል።

#በ (በ) ሲወጣ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለአምላክ ተሰቅሎተ መስቀል ይላል። ትርጉሙ በመስቀል መሰቀል ለአምላክ ይገባል ማለት ነው።
- ✓ ሳቢዘር:- ለይሁዳ ስቅለተ መስቀል አምላከ ይላል። ትርጉሙ አምላክን በመስቀል ማሰቀል ለይሁዳ ይገባል ማለት ነው።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ተክዕወ ወይነ አማኑኤል ደም ተቀዳሔ መስቀል ጽዋዕ ይላል። ትርጉሙ በመስቀል ጽዋዕ የተቀዳ የአማኑኤል ወይን ደም ፈሰሰ ማለት ነው።

#እም (ከ) ሲወጣ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለአማኑኤል ወይን ተቀድሖተ ድንግል ቀሡት ይላል። ትርጉሙ ከድንግል እንስራ መቀዳት ለአማኑኤል ወይን ይገባል።
- ✓ ሳቢዘር:- ለያዕቆብ ወልድ ልደተ ማርያም ርብቃ ይላል። ትርጉሙ ከማርያም ርብቃ መወለድ ለወልድ ያዕቆብ ይገባል ይላል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ያስተፈሥሕ ልበ ደመ ኢየሱስ ወይን ተቀዳሔ ገቦ ቀሡት ይላል። ትርጉሙ ከእንስራ ጎን የተቀዳ የኢየሱስ ደም ወይን ልብን ያስደስታል ማለት ነው።

#ከመ፣ምስለ(እንደ፣ ከ_ጋር)ሲወጡ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለይሁዳ ገብር አቅትሎተ ፈያት አምላከ አይሁደ ይላል። ትርጉሙ አይሁድን አምላክን እንደ ሽፍታ ማስገደል ለይሁዳ ባርያ ይገባል። ለአሳሔል ገብር ተራውጾተ ፈረስ ብሎ ከፈረስ ጋር መሯሯጥ ለአሳሔል ባርያ ይገባል ይላል።
- ✓ ሳቢዘር:- ለአማኑኤል ገብር ሙተተ ፈያት ኃያላን ይላል። ትርጉሙ እንደ ኃያላን ሽፍቶች መሞት ለአማኑኤል አገልጋይ ይገባል ይላል ወይም ከኃያላን ሽፍቶች ጋር መሞት ለአማኑኤል አገልጋይ ይገባል ይላል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:- ይረውጽ ገብርኤል ላእክ ተፈናዌ ሚካኤል ወልድ ይላል። ትርጉሙ ከሚካኤል ልጅ ጋር የተላከ ገብርኤል ተማሪ ይሮጣል። የጎዜን

ይሁዳ አርጤክስስ ሰቃሌ ፈያት ኃያላን ሐማሀ ወልደ ይላል። ትርጉሙ ወልድ ሐማን እንደ ኃያላን ሽፍቶች የሰቀለ አርጤክስስ ይሁዳ ያዜናል።

ዘመድ ሙሻዘር ክፍል ፪

ኀበ፣እስከ (ወደ፣ እስከ) ሲወጡ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለገብርኤል ላእክ ተፈንዎ ድንግል ንግሥት ይላል። ትርጉሙ ወደ ድንግል ንግሥት መላክ ለገብርኤል ተማሪ ይገባል ማለት ነው። ለንጉሥ አብ አስተፋንዎተ ድንግል ንግሥት ገብርኤልሀ መሚሐ ምስለ መለኮት መስፍን ይላል። ትርጉሙ ከመለኮት መስፍን ጋር መሚሕ ገብርኤልን ወደ/እስከ ድንግል ንግሥት ማላላክ ለገብርኤል ተማሪ ይገባል ማለት ነው።
- ✓ ሳቢዘር:- ለገብርኤል ላእክ ብጽሐተ ድንግል ንግሥት ይላል። ወደ/እስከ ድንግል ንግሥት መድረስ ለገብርኤል ተማሪ ይገባል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ክቡር ውእቱ ዳዊት ገብርኤል በጻሔ ድንግል ቤርሳቤሕ ይላል። ትርጉሙ ወደ/እስከ ቤርሳቤሕ ድንግል የደረሰ ገብርኤል ዳዊት ክቡር ነው ማለት ነው።

#እንበለ (ያለ__በቀር) ሲወጣ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለአማኑኤል አቤል ተቀትሎተ ኃጢኣት ሰይፍ ይላል። ትርጉሙ ያለ ኃጢአት ሰይፍ መገደል ለአማኑኤል አቤል ይገባል ማለት ነው።
- ✓ ሳቢዘር:- ለአማኑኤል ዳዊት ንግሠተ ሐዋርያት እስራኤል በመስቀል ኬብሮን ይላል። ትርጉሙ በመስቀል ኬብሮን ያለ እስራኤል ሐዋርያት መንገሥ ለአማኑኤል ዳዊት ይገባል።

- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ክቡር ውእቱ አማኑኤል ዳዊት ተቃታሌ ኃጢኣት ሰይፍ ምስለ ጎልያድ መልአከ ሞት ይላል። ትርጉሙ ከጎልያድ መልአከ ሞት ጋር ያለ ሰይፍ ኃጢኣት የሚገዳደል ዳዊት አማኑኤል ክቡር ነው ይላል።

#ተሳቢ (ግእዜ) ሲያወጣ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ሠምረ ይሁዳ ሄሮድስ አስተቃትሎ አማኑኤል ዮሐንስ ምስለ አይሁድ ሐራሁ ይላል። ትርጉሙ ከአይሁድ ጭፍሮቹ ጋራ አማኑኤል ዮሐንስን ማገዳደል ሄሮድስ ይሁዳ ወደደ።
- ✓ ሳቢዘር:- ለንግሥት ድንግል ቅድሐተ ድንጋሌ ወይን በቢረሌሃ ልቡና ይላል። ትርጉሙ በልቡና ዋናጫዋ ድንግልና ወይንን መቅዳት ለንግሥት ድንግል ይገባል ይላል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:- ክብርት ድንግል ለባሲተ ንጽሕ ጸምር ይላል። ትርጉሙ ንጽሕና ግምጃን የለበሰች ድንግል ክብርት ናት ማለት ነው።

#ባዕድ #ሙሻዘር

- ✓ ባዕድ ሙሻዘር፣ ባዕድ ቅጽል፣ ባዕድ ዜርዜር ይባላል። ይህም አገባቡን ከእነ ዜርዜሩ አውጥቶ ዜርዜሩን ወደ ኋላ ይዘረዜራል።

"ለ፣በይነ"ን ሲዘረዜር።

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:- ለአዳም መዊተ አምላክ ይላል። ትርጉሙ ለእርሱ/ ስለእርሱ የአምላክ መሞት ለአዳም ይገባል ማለት ነው ይላል። -
- ✓ ሳቢ ዘር:-ለአዳም አብ ልደተ አማኑኤል ወልድ ይላል። ትርጉሙ ለእርሱ/ስለእርሱ የአማኑኤል ልጅ መወለድ ለአዳም አባት ይገባል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ድኅነ አዳም መዋቴ እግዙእ ይላል። ትርጉሙ ለእርሱ/ስለእርሱ ጌታ የሞተለት አዳም ዳነ ማለት ነው።

"በ"ን ሲዘረዜር

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:-ለመስቀል ተሰቅሎ አምላክ ይላል። ትርጉሙ በእርሱ የአምላክ መሰቀል ለመስቀል ይገባል።

- ✓ ሳቢ ዘር:-ለመስቀል ዓረፍት ስቅለተ አማኑኤል ወልታ ይላል። ትርጉሙ በእርሱ የአማኑኤል ጋሻ መሰቀል ለመስቀል ግድግዳ ይገባል ማለት ነው።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:- ሠናይት ርስት ተጻባኢተ ናቡቴ ልሂቅ ምስለ አክአብ ዘመድ ይላል። ትርጉሙ በእርሷ ከዘመድ አክአብ ጋር ሽማግሌ ናቡቴ የተጠላላባት ርስት ያማረች ናት ይላል።

"እም"ን ሲዘረዜር

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:-ለቤት ወጺአ ነጋዲ ይላል።ትርጉሙ ከእርሱ የነጋዴ መውጣት ለቤት ይገባል።
- ✓ ሳቢ ዘር:-ለድንግል ጽርሕ ፀአተ አማኑኤል ንጉሥ ይላል። ትርጉሙ ከእርሷ የአማኑኤል ንጉሥ መውጣት ለድንግል አዳራሽ ይገባል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ሚ ይርሕቅ ሰማይ መቅደስ አምጻኤ ገብርኤል ካህን ብሥራት ታቦተ እስከ ማርያም ባሕረ ጥምቀት ይላል። ትርጉሙ ከእርሱ እስከማርያም ባሕረ ጥምቀት የምሥራች ታቦትን ካህን ገብርኤል ያመጣበት መቅደስ ሰማይ ምንኛ ይርቃል!።

"ከመ፣ምስለ"ን ሲዘረዜር

- ▪ ንዑስ አንቀጽ:-ለፈያት ተሰቅሎ አምላክ ይላል። ትርጉሙ እንደነሱ የአምላክ መሰቀል ለፈያት ይገባል ወይም ከእነርሱ ጋር የአምላክ መሰቀል ለፈያት ይገባል ይላል።
- ▪ ሳቢ ዘር:-ለፈያት መጣብሕ ስቅለተ አማኑኤል ወልታ ይላል።
- ▪ ሣልስ ቅጽል:-ከብረ ኢዮአብ አስተቃታሌ ዳዊት አሳሔልሀ ምስለ አቤኔር ይላል። ትርጉሙ ከእርሱ ጋራ/እንደ እርሱ ከአቤኔር ጋራ አሳሔልን ዳዊት ያገዳደለለት ኢዮአብ ከበረ።

"ኀበ፣እስከ"ን ሲዘረዜር

- ▪ ንዑስ አንቀጽ:-ለባቢሎን ወሪደ ንስር ይላል። ትርጉሙ ወደ እርሱ/እስከ እርሱ የንስር መውረድ ለባቢሎን ይገባል ይላል።

- ሳቢዘር:-ለድንግል ንግሥት ሑረተ አማኑኤል ንጉሥ ይላል። ትርጉሙ ወደእርሷ/እስከእርሷ የንጉሥ አማኑኤል መሄድ ለድንግል ንግሥት ይገባል።
- ሣልስ ቅጽል:-እምነ ይእቲ ድንግል ተፈናዊተ ገብርኤል እምነ ሰማይ ይላል። ትርጉሙ ወደእርሷ/እስከእርሷ ከሰማይ ገብርኤል የተላከላት ድንግል እናታችን ናት ይላል።

"እንበለ"ን ሲዘረዜር

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:-ለእስራኤል ተናግሦ ዳዊት ምስለ ሳኦል ይላል። ትርጉሙ ያለ እርሱ ከሳኦል ጋር የዳዊት መናገሥ ለእስራኤል ይገባል ማለት ነው።-
- ✓ ሳቢዘር:- ለእስራኤል ንግሠተ ሳሙኤል ዳዊትሀ ይላል። ትርጉሙ ያለ እነርሱ ዳዊትን የሳሙኤል ማንገሥ ለእስራኤል ይገባል
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ክቡራን እስራኤል አንጋሥያነ ሳሙኤል ዳዊትሀ ይላል ትርጉሙ ያለ እነርሱ ዳዊትን ሳሙኤል ያነገሠላቸው እስራኤል ክቡራን ናቸው ይላል።

ባዕድ ሙሻዘር ክፍል ፪

#እንበለ ከተሳቢ/ግእዜ ጋር ሲወጣ

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:-ለይሁዳ ሰቂለ አምላክ ይላል።ትርጉሙ ያለ እርሱ አምላክን መስቀል ለይሁዳ ይገባል።
- ✓ ሳቢዘር:-ለይሁዳ ስቅለተ አምላክ ይላል። ትርጉም ያለ እርሱ አምላክን መስቀል ለይሁዳ ይገባል።
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-ነስሐ ይሁዳ አስቃሌ አይሁድ አምላከ ይላል ትርጉሙ ያለ እርሱ አምላክን አይሁድን ያሰቀላ ይሁዳ ተጸጸተ።

#እንበለ በአሉታ ሲገባ:-

- ✓ ንዑስ አንቀጽ:-ለመስቀል ኢተሰቅሎ አምላክ ይላል ትርጉሙ ያለ እርሱ የአምላክ አመሰቀል ለመስቀል ይገባል ማለት ነው:: -
- ✓ ሳቢ ዘር:-ለመስቀል ኢስቅለተ አምላክ ይላል ትርጉሙ ያለእርሱ የአምላክ አለመሰቀል ለመስቀል ይገባል ማለት ነው::
- ✓ ሣልስ ቅጽል:-አድኀነ ዓለመ መስቀል ኢተሰቃሌ አምላክ ይላል ትርጉሙ ያለእርሱ አምላክ ያልተሰቀለበት መስቀል ዓለምን አዳነ ማለት ነው::

ስምንቱን አገባባት ዘጠነኛው እንበለ ይበዘብዛቸዋል:: ለምሳሌ ለአዳም ኢተሰቅሎ አምላክ ቢል ያለ እርሱ የአምላክ አለመሰቀል ለአዳም ይገባል ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ በይኄሁ፣ ሎቱ እንደተበዘበዘ አስተውል:: እንዲህ እያለ እንበለ ስምንቱንም አገባቦች ይበዘብዘዛቸዋል ማለት ነው:: በዘበዘ ማለት የእነርሱን ፍች አጥፍቶ እንበለ ያዘ ማለት ነው:: የእንበለ መንገድ ለማይመረምሩ የከሃድያንን ንባብ ይመስላል::

ይህም አብ ኢተወላዴ ወልድ ሲል ያለእርሱ ወልድ ያልተወለደለት አብ ይላል:: ምሥጢሩ ለአብ ከወልድ በቀር ልጅ የሌለው ለማለት ነው:: ወልድ ስቁለ አበሳ ሲል ላልመረመረ በበደሉ ምክንያት የተሰቀለ ወልድ ሊመስለው ይችላል:: ትርጉሙ ግን ያለ ኃጢአት (ያለ በደል) የተሰቀለ ወልድ ማለት ነው:: ሙሻ ዘር በሳድስ ቅጽል፣ በባዕድ ቅጽል፣ እንዲሁም በመድበልም ከላይ ያየናቸውን መስሎ ይወጣል::

ሙሻ ዘር የመጨረሻ ክፍል

- ባለፉት ክፍሎች ዘመድ ሙሻዘርን እና ባዕድ ሙሻ ዘርን ሰዋስውን ከሰዋስው ሳቢን ከተሳቢ እያናበቡ ዘጠኝ አገባባትን ሲያወጡ አይተናል። ከዙያ ቀጥለን ደግሞ ዚሬ የመጨረሻውን ክፍል እናያለን። ሙሻዘር ከሚሆኑ ቀለማት አምስቱ ማለትም ቀዳማይ አንቀጽ፣ ካልዓይ አንቀጽ፣ ሣልሳይ አንቀጽ፣ ዘንድ አንቀጽ እና ቦዜ አንቀጽ ዘርዜረው ሳይናበቡ አገባባትን ያመጣሉ። ሲመጡም አንድና ብዘ ሴትና ወንድ ሩቅና ቅርብ አይለዩም።

ቀጥለን በምሳሌ እንመልከተው። ሄሮድስ በልዖ ርእሶ ቢል ሄሮድስ ራሱን በላ ማለት ነው። ይህ ባዕድ በራሱ ይባላል። ባዕድ ያሰኘው በልዖ በላው ተብሎ መተርጎም የነበረበትን በላ ተብሎ በመተርጎሙ ነው።

በተጨማሪም በአስሩ መራሕያን በመተርጎሙ ነው።

- #ቀዳማይ #አንቀጽ

በይኤሁ፣ሎቱ ሲወጡ:- አምላክ ፈጠሮ ኪያኪ ሔዋንሀ ይላል ትርጉሙ ለእርሱ/ስለእርሱ አንቺን ሔዋንን አምላክ ፈጠረ ማለት ነው። አስተውል ፈጠሮ ያለው ዜርዜር ፈጠረው ተብሎ ከመተርጎም ይልቅ ፈጠረ ተብሎ ተተርጉሟል። ባዕድ ያሰኘውም ይህ ነው። - ቦቱ፣ላዕሌሁ ሲወጡ:-ንጉሥ አንበሮ ኪያየ አክሊለ ይላል ትርጉሙ በእርሱ/በእርሱ ላይ እኔን አክሊል ንጉሥ አስቀመጠ ማለት ነው::

እምኔሁ ሲወጣ:-አብ አፍቀሮ ንዑሳነ ሕጻናተ ይላል ትርጉሙ ከእርሱ ትንንሽ ሕጻናትን አብ ወደደ ይላል። ከማሁ ሲወጣ:-ንጉሥ አክበሮ ሠናያተ አንስተ ይላል ትርጉሙ እንደ እርሱ የሚያምሩ ሴቶችን ንጉሥ አከበረ ማለት ነው።

ምስሌሁ ሲወጣ:-ንጉሥ አቅረቦ ምሁረ ኪያክን አንስተ ጊዛ ማዕድ ይላል ትርጉሙ ከእርሱ ጋራ በማዕድ ጊዜ እናንተን ሴቶችን ምሁሩን (የተማረውን) ንጉሥ አቀረበ ይላል። ኀቤሃ፣ እስከኔሃ ሲወጡ:- ንግሥት አብጽሐታ ዘተለወት አመተ ይላል ትርጉሙ እስከ እርሷ/ወደ እርሷ

የተከተለች የሴት አገልጋይን ንግሥት አደረሰች ይላል።

- #ካልኣይ #አንቀጽ (ትንቢት አንቀጽ) :-

ከላይ ያየነውን ቀዳማይ አንቀጽ መስሎ የሚሄድ ሲሆን ልዩነቱ በቀዳማይ ይተረጎም የነበረውን በካልዓይ እየተረጎሙ መሄድ ነው። ለምሳሌ ከላይ ከማሁ ሲወጣ በቀዳማይ ንጉሥ አክበሮ ሠናያተ አንስተ ያለውን ንጉሥ ያከብሮ ሠናያተ አንስተ ብሎ ማውጣት ማለት ነው። ትርጉሙ እንደ እርሱ የሚያምሩ ሴቶችን ንጉሥ ያከብራል ተብሎ ይተረጎማል። ሌሎችንም አገባባት በዙህ መልኩ እያደረጉ ማውጣት ነው።

- #ሣልሳይ #አንቀጽ (ትእዛዝ አንቀጽ)

ይህም አካሄዱ በቀዳማይ አንቀጽ ካየነው ጋር ይመሳሰላል። ለምሳሌ በይኄሁ/ሎቱ ሲወጡ ንጉሥ ይሞቅሐሙ ኪያሁ ፈያተ ቢል ትርጉሙ ስለእርሱ/ለእርሱ እርሱን ሽፍታውን ንጉሥ ይሰር ይላል። ሌላውንም በዚህ መልኩ ማውጣት ነው።

- #ዘንድ #አንቀጽ

ዘንድ አንቀጽም በቀዳማይ አንቀጽ ካየነው ጋር ይመሳሰላል። ልዩነቱ ዘንድ መሆኑ ብቻ ነው። ለምሳሌ ለእግዙአብሔር ይምሐሮሙ ኀጥአነ ቢል በአገባብ በይኄሁ/ሎቱ ሲወጣ ለእርሱ/ስለእርሱ ኀጥአንን ይምር ዘንድ ለእግዙአብሔር ይገባል ማለት ነው።

- #ቦዜ #አንቀጽ

ይህም ልዩነቱ ቦዜ መሆኑ እንጂ ከላይ ካየናቸው ጋር ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ ነቢያት አእሚሮሃ ምጽአተ ክርስቶስ ተነበዩ ቢል ትርጉሙ በይኄሁን/ሎቱን ሲያወጣ ለእርሱ/ስለእርሱ የክርስቶስን መምጣት ነቢያት አውቀው ተናገሩ ይላል።

- #ዘመድ #ዜርዜር

ዘመድ ዜርዜር የሚባለው በየራሱ የሚዘረዘረው ነው። ለምሳሌ አምላክ ሞቶ ለአዳም ሲል በይኄሁ/ሎቱ ይወጣሉ ትርጉሙ ስለእርሱ/ለእርሱ ለአዳም ስለ አዳም አምላክ ሞተ ማለት ነው። ቦቱ ሲወጣ:-አምላክ ተሰቅሎ ለመስቀል ይላል ትርጉሙ በእርሱ በመስቀል አምላክ ተሰቀለ ማለት ነው። እምኄሁ ሲወጣ:-ነጋዲ ወጽአ ለቤት ከእርሱ ከቤቱ ነጋዲ ወጣ ይላል።

ምስሌሆሙ፣ከማሆሙ ሲወጡ:- አምላክ ተሰቅሎሙ ለፈያት ይላል ትርጉሙ እንደነርሱ ከእነርሱ ጋራ አምላክ ተሰቀለ ማለት ነው። ጎቤሃ፣እስከኔሃ ሲወጡ:- ገብርኤል ተፈነዋ ለማርያም ይላል ትርጉሙ እስከ እርሷ ወደእርሷ ወደማርያም እስከ ማርያም ገብርኤል ተላከ ማለት ነው።

❖ #ባዕድ #ቅጽል

አገባቡ ዜርዜሩ ለባለቤት አንቀጹ ለተሳቢ ሲሆን ባዕድ ቅጽል ይባላል። አንድና ብዘ፣ ሴትና ወንድ፣ ሩቅና ቅርብ ሳያናግር ያናገረ ይመስላል። አንቀጽን፣ ተሳቢን እና አገባብን ይዘረዜራል። አንቀጽ ሲዘረዜር:-ማርያም እንተ አክበሩ ሥላሴ አበው ይላል ትርጉሙ ሥላሴ አባቶች ያከበሯት ማርያም ማለት ነው። ብእሲ ዘአክበረት ብእሲት ይላል ትርጉሙ ሴት ያከበረችው ሰው ማለት ነው። መላእክት እለፈጠርከ አንተ ወልድ ይላል ትርጉሙ አንተ ወልድ የፈጠርካቸው መላእክት ማለት ነው።

የተሳቢ ዜርዜር:- ማርያም አክበሩ አበዊሃ ይላል ትርጉሙ አባቶቿ ያከበሯት ማርያም ማለት ነው። መላእክት እለ ፈጠርከ አንተ እግዙኦሙ ይላል ትርጉሙ አንተ ጌታቸው የፈጠርካቸው መላእክት ማለት ነው።

የአገባብ ዜርዜር:- አበው እለ ከብረት ማርያም ይላል።ትርጉሙ ማርያም የከበረችላቸው አባቶች ማለት ነው። መላእክት እንተ ተፈጥሩ ወልድ ይላል ትርጉሙ መላእክት የተፈጠሩለት ወልድ ማለት ነው። ብእሲ ዘተፈጥረት ብእሲት ይላል። ሴት የተፈጠረችለት ሰው (ወንድ) ማለት ነው። እነዙህ በግልጸ ዘ ሲነገሩ ነው። ብቻ በሳድስ ቅጽል ሲነገሩ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላሉ።

አንቀጽ ሲዘረዜር:-ማርያም ወይን ትክልተ ሥላሴ ገባእት ፈረየት ፍሬ ይላል ትርጉሙ ሥላሴ ምንደኞች የተከሏት/የተከላችኋት/የተከልናት ማርያም ወይን አፈራች ይላል።ወይም ሥላሴ ምንደኞች የተከሉሽ ማርያም ወይን አፈራሽ ይላል።ወይም ሥላሴ ምንደኞች የተከልንሽ ማርያም ወይን አፈራሽ ይላል። ሥላሴ ምንደኞች የተከሉኝ/የተከላችሁኝ ማርያም ወይን ፍሬን አፈራሁ ይላል።

አገባብ ሲዘረዜር:-ድንግል ንግሥት ወልድ ይላል።ትርጉሙ ወልድ የነገሠላት ድንግል/ ወልድ የነገሥኩላት ድንግል/ ወልድ የነገሠልሽ ድንግል/ ወልድ የነገሠልኝ ድንግል/ ወልድ የነገሥክልኝ ድንግል/ ወልድ የነገሥኩልሽ ድንግል/ ወልድ የነገሥክላት ድንግል ይላል።

ተሳቢ ሲዘረዜር:-ጴጥሮስ ምሁረ አርድእት ወንጌለ ይላል ትርጉሙ ተማሪዎቹ ወንጌልን የተማሩ ጴጥሮስ ይላል። የተደራጊ አንቀጽ ከአድራጊ ከአስደራጊ ተናቦ በአድራጊ በአስደራጊ አመል ይፈታል።

ለምሳሌ አምላክ ተሰቃሌ ይሁዳ ሲል ትርጉሙ ይሁዳ የሰቀለው አምላክ ይሆናል። አምላክ ተሰቃሌ ይሁዳ አይሁደ ሲል ይሁዳ አይሁድን ያሰቀለው አምላክ ተብሎ ይተረጎማል። የአድራጊ አንቀጽ ከአስደራጊ ተናቦ በአስደራጊ አመል ይፈታል። አምላክ ሰቃሌ ይሁዳ አይሁደ ይላል ትርጉሙ ይሁዳ አይሁድን ያሰቀለው አምላክ ማለት ነው። የተደራራጊ አንቀጽ ከአደራራጊ ተናቦ በአደራራጊ አመል ይፈታል ምሳሌ አምላክ ተሰቃሌ ይሁዳ ምስለ አይሁድ ይላል።ትርጉሙ ይሁዳ ከአይሁድ ጋር ያሰቃቀለው አምላክ ማለት ነው።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ካገረ ግስ ክፍል ፭

❖ #መሣግር:- መሣግር የሚባለው በዜርዜር ጊዛ ካልዓይ አንቀጹን የቀተለን በቀደሰ፣ የቀደሰን በቀተለ፣ የገብረን በሰብሐ፣ የሰብሐን ወደ ገብረ፣ የክህለን ወደ ቀደሰ እየለዋወጠ የሚዘረዜር ማለት ነው። መሣግር የሚሆኑ ፊደላት "ሀ፣ ረ፣ አ፣ ወ፣ ዘ" ናቸው።

"ሀ":- የሰብሐን ወደ ገብረ ሲያሠግር ገንሐ ብሎ ካልዓዩ ይገንሕ ይላል። "ሀ" የቀተለን ወደ ቀደሰ ሲያሠግር መሀረ አስተማረ ብሎ ይሜህር ያስተምራል ይላል። _

"ረ":- የቀደሰን ወደ ቀተለ ሲያሠግር ጠፈረ ብሎ ካልዓዩ ይጠፍር ይላል። _

"አ":- የክህለን ወደ ቀደሰ ሲያሠግር ርእየ አየ ብሎ ይሬኢ ያያል ይላል። _

"ወ":- የቀተለን ወደ ቀደሰ ሲያሠግር ወጠነ ጀመረ ብሎ ይዌጥን ይጀምራል ይላል።

"ዘ":- የቀተለን ወደ ቀደሰ ሲያሠግር ነ፧ረ ብሎ ይኔዜር ይላል። የክህለን ወደ ቀደሰ ሲያሠግር ተዜጎረ ብሎ ይዛጎር ይላል።

❖ #ሕርመት:-በቀዳማይ መልተው በካልዓይ የሚጎድሉ ግሦች ሁለት ናቸው። እነዙህም ወህበ እና ክህለ ናቸው። እኒህም ግሦች ሕርመት ይባላሉ። አወራረዳቸውም ወህበ-ሰጠ ብሎ ይሁብ-ይሰጣል፣ የህብ-ይሰጥ ዘንድ፣ የህብ-ይስጥ ይላል። ክህለ-ቻለ ብሎ ይክል-ይችላል፣ ይክህል-ይችል ዘንድ፣ ይክህል-ይቻል ይላል።

እነዚህ ግን በአራቱ አዕማድ ሲገቡ ያጎደሉትን ቀለም ያስገኛሉ። ይኽውም ተውህበ የቆመ ቤቶች ሳድስ ቅጽላቸው በመካከል ሳድስ " ው"ን አምጥተው ይወጣሉ። ይህም ከሌሎች የተለየ ነው። ለምሳሌ የቀደሰ ሳድስ ቅጽል ቅዱስ ነው። "ዱ" ካዕብ ነው። ቆመ ብሎ ቅውም ሲል ግን "ው" ሳድስ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

'ኀሠሠ' የመሰሉ ግሦች በብዘ በካልዓት በዘንድ እና በትእዛዝ አንቀጽ፣ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት ዘርዘር ያጎድላል። ለምሳሌ "ነበበ-ተናገረ" ይላል። በብዙ ነበብክሙ-ተናገራችሁ ይላል። በካልዓይ "ትነቡትናገራላችሁ" ይላል ማለት ነው። በትእዚዜ አንቀጽ ደግሞ "ንቡ-ተናገሩ" ይላል። ተጨማሪ ምሳሌ "ኀሠሠ"ን ብንመለከት። በብዘ "ኀሠሥክሙ-ፈለጋችሁ" ይልና። በትእዛዝ አንቀጽ "ኀሡ-ፈልጉ" ይላል። 'ኀሠሡፈለጉ' ይልና በትእዚዜ "ይኀሡ-ይፈልጉ" ይላል። በአንዲት ሴት ደግሞ በዜርዜር ኀሠሠቶ-ፈለገችው ብሎ በካልዓይ አንቀጽ "ተኀሥ-ትፈልገዋለች" ይላል።

- #የንባብ ተገብሮ የትርጓሜ ገቢር የሚሆኑ ግሦች አራት ናቸው። እነዙህም "ተለቅሐ-ተበደረ፣ ተመጠወተቀበለ፣ ተጸገወ-ተሰጠ፣ ተወክፈ-ተቀበለ" ናቸው። የእነዚህም አድራጊዎቻቸው "ለ"ን ይሻሉ። ሁለቱም ግእዜ ይስባሉ። መጠወ/ጸገወ/ለቅሐ ወርቀ ለነዳይ ይላል። የንባብ ገቢር የትርጓሜ ተገብሮ የሚሆኑ ግሦች አራት ናቸው እነዙህም ሐመ-ታመመ፣ ደወየ-ታመመ፣ ጸምአ-ተጠማ፣ ርኀበ-ተራበ ናቸው።

የንባብ አስደራጊ የትርጓሜ አድራጊ አለ። ምሳሌ:- አስደራጊ አፍቀረ-ወደደ:አስወደደ፣ አእመረ-አወቀ:አሳወቀ የሚሉት ናቸው። የንባብ አስደራጊ የትርጓሜ አድራጊ፣ ተደራጊ፣ አስደራጊ አለ። ምሳሌ:- አንቀልቀለ-ተነዋወጠ፣ አነዋወጠ ይላል።

የንባብ አደራራጊ የትርጓሜ አድራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራጊ፣ አደራራጊ አለ። ለምሳሌ አስተርአየ-ታየ፣ አሳየ በይላል። የንባብ ተደራራጊ የትርጓሜ ተደራጊ አለ። ምሳሌ ተጋብአ-ተሰበሰበ ይላል።

የተገብሮ አመል በንባባቸውም በትርጓሜያቸውም የማይገኝባቸው አራት ናቸው። እነዙህም "ከብረ፣ ነግሠ፣ ሞተ፣ ቆመ" ናቸው።እሊህም ዘራቸውን ይስባሉ እንጂ ከሌላ ነገር ገብተው አይስቡም። ከብረ ክብረ፣ ነግሠ ንግሠ፣ ቆመ ቆመ፣ ሞተ ሞተ ይላል። ምሥጢራቸው ግን ተደራጊ ነው።

በፍጹም ገቢራቸው በውድ ሁለት በግድ አንድ፣ በተገብሯቸው በውድ አንድ የሚስቡ ግሦች አሉ። እኄም ላጸየ-ላጨ፣ መተረ-ቆረጠ፣ ረገዘ-ወጋ፣ ሐነቀ-አነቀ፣ ኰርዐ-መታ ናቸው። በውድ ሁለት ሲስቡ ላጸየ ሕጻነ ርእሶ ይላል ትርጉሙ ሕጻኑን ራሱን ላጨ ይላል። አሕዚብ መተርዎ ለዮሐንስ ክሳዶ ይላል ትርጉም

አሕዛብ የዮሐንስ አንገቱን ቆረጡት ማለት ነው። አይሁድ ረገዜም ለክርስቶስ ገቦሁ ይላል ትርጉሙ አይሁድ የክርስቶስን ጎኑን ወጉት ይላል። ተደራጊዎቻቸው በውድ አንድ ሲስቡ ሕጻን ተላጸየ ርእሶ ይላል ትርጉሙ ሕጻን ራሱን ተላጨ ማለት ነው።

- #አሥራወ ቀለማት በአሉታ ጊዛ በአስደራጊ በአደራራጊ ከቀዳማይ ይወጣሉ። ሲወጡም ሁለት "አ" ቢገኝ አንዱን፣ አንድ "አ" ቢገኝ ያንኑ ያስለቅቁታል። ከሁለቱ "አ" አንዱን "አ" ሲያስለቅቁ 'አእመረ-አወቀ' ለሚለው አሉታው 'ኢያእመረ-አላወቀም' ነው። አንዱን 'አ' ሲያስለቅቁ "አፍቀረ-ወደደ" ለሚለው አሉታው "ኢያፍቀረ-አልወደደም" የሚለው ነው።

- #በእርባታ ጊዛ "ተ" ን ውጠው የሚያስቀሩ ቀለማት ስድስት ናቸው እነዙህም "ሰ፣ተ፣፣ደ፣ጠ፣ጸ" ናቸው። ተሰብሐ-ተመሰገነ ብሎ ይሴባሕ-ይመሰገናል፣ ይሰባሕይመሰገን ዘንድ፣ ይሰባሕ-ይመስገን ይላል። ተጠምቀ-ተጠመቀ ብሎ ይጠመቅ-ይጠመቃል፣ ይጠመቅይጠመቅ ዘንድ፣ ይጠመቅ-ይጠመቅ ይላል።

ተደንገለ-ተጠበቀ ብሎ ይደነገል-ይጠበቃል፣ ይደንገልይጠበቅ ዘንው፣ ይደንገል-ይጠበቅ ይላል። ተተርአሰ-ተንተራሰ ብሎ ይተረአስ-ይንተራሳል፣ ይተርአስይንተራስ ዘንድ፣ ይተርአስ-ይንተራስ ይላል። ተፀምደ-አገለገለ፣ ይፀመድ-ያገለግላል፣ ይፀመድ-ያገለግል ዘንድ፣ ይፀመድ-ያገልግል ይላል።

ተዘምደ-ዘመድ ሆነ፣ ይዘመድ-ዘመድ ይሆናል፣ ይዘመድ-ዘመድ ይሆን ዘንድ፣ ይዘመድ-ዘመድ ይሁን ይላል። ነገር ግን ይህን ሕግ የማይጠብቁ ሁለት ግሦች አሉ እኒህም ተስዐ- ዘጠኝ አደረገ የሚለውና ተስዕዐ-ተገፈፈ የሚሉት ናቸው። አረባባቸውም ተስዐ ብሎ ይቴስዕ፣ ይተስዕ፣ ተስዕ ይላል። ተሥዕዐ ብሎ ይትሰዐዕ፣ ይትሰዐዕ፣ ይትሰዐዕ ይላል።

- ንዑስ አንቀጻቸውና ሳድስ ቅጽላቸው አንድ የሚሆኑ ግሦች አሉ። እኒህን ርኅበ-ተራበ፣ ጸበ-ጠበበ፣ ቀለቀለለ፣ መረ-መረረ፣ ኖኅ-ረዘመ፣ መፀ-ቦኅ(ኾመጠጠ) ናቸው። ሲነገሩም ርኅበ ካለው ርኂብ ርኂቦት ይወጣል። ሳድስ ቅጽሉ ርኂብ፣ ርኂባን፣ ረኃብ፣ ረኃባት ይላል። የቀለ ንዑስ አንቀጽ ቀሊል ቀሊሎት ነው። ሳድስ ቅጽሉ ቀሊል፣ ቀሊላን፣ ቀላል፣ ቀላላት ይላል። የጸበ ንዑስ አንቀጽ ጸቢብ ጸቢቦት ነው። ሳድስ ቅጽሉ ጸቢብ፣

ጸቢባን፣ ጸባብ፣ ጸባባት ይላል። የመሪር ንዑስ አንቀጹ መሪር መሪሮት ነው።

ሳድስ ቅጽሉ መሪር፣ መሪራን፣ መራር፣ መራራት ይላል። የኖኅ ንዑስ አንቀጽ ነዊኅ ነዊኖት ይላል። ሳድስ ቅጽሉ ነዊኅ፣ ነዊኃን፣ ነዋኅ፣ ነዋኃት ይላል። የመፀ ንዑስ አንቀጽ መሚፅ መሚየት ነው። ሳድስ ቅጽሉ መሚፅ፣ መሚፃን፣ መፃፅ፣ መፃፃት ይላል። ሌሎችም እኒህን መስለው የሚሄዱ አሉ ለምሳሌ ጸልመ-ጨለመ ንዑስ አንቀጹ ጸሊም ጸሊሞት ነው። ሳድስ ቅጽሉ ጸሊም፣ ጸሊማን፣ ጸላም፣ ጸላማት ይላል።

ረሥአ-ረሳ ንዑስ አንቀጹ ረሢእ ረሢኦት ይላል። ሳድስ ቅጽሉ ረሢእ፣ ረሢኣን፣ ረሣእ፣ ረሣኣት ይላል። ጠበ-ብልሀተኛ ሆነ ለሚለው ንዑስ አንቀጹ አንቀጹ ጠቢብ ጠቢቦት ይላል። ሳድስ ቅጽሉ ጠቢብ፣ ጠቢባን፣ ጠባብ፣ ጠባባት ይላል። ከላይ ያየናቸው ከዙህ ያየናቸው በሙሉ ንዑስ አንቀጻቸው ላልቶ ይነበባል። ሳድስ ቅጽላቸው የሴቶች ጠብቆ ይነበባል። ከወንዶችም ጸሊም፣ ጸሊማን እና ነዊኅ፣ ነዊኃን ይጠብቃሉ።

- በ"ወ" ለደረሰ ግሥ በ"ተ" ካልተነሳ በራሱ ካልተገሰሰ በመድረሻው ሳድስ ቀለም ከካልዓይ ከአንድ ከትእዚዜ የለውም። ካዕብ ነው እንጂ ሳድስ ቀለም ሲታጣ አርኀወ-ከፈተ፣ ያርኅ-ይከፍታል፣ ያርኅ-ይከፍት ዘንድ፣ ያርኅ-ይክፈት ይላል። በ"ተ" ሲነሳ ግን አለው። ይህም ተኄረወ-ቸር ሆነ፣ ይትኄረው-ቸር ይሆናል፣

ይትኄረው-ቸር ይሆን ዘንድ፣ ይትኄረው-ቸር ይሁን ይላል። በራሱ ሲገሰስ ከወወ-ቅልጥፍጥፍ አለ፣ ይከውው-ቅልጥፍጥፍ ይላል፣ ይክውው-ቅልጥፍጥፍ ይል ዘንድ፣ ይክውው-ቅልጥፍጥፍ ይበል ይላል። የሴቲቱ ሳድስ ቅጽል ግን ሳድሱን አስለቅቆ ካዕብ አድርጎ ይነገራል ሲነገርም ከተሰርገወ ስርጉት፣ ከደለወ ድሉት ይወጣል። በ"የ" ለደረሰ ግሥ በ"ተ" ካልተነሳ በራሱ ካልተገሰሰ መድረሻው በካልዓይ ሳድስ የለውም። ሣልስ ነው እንጂ። ሳድስ ሲታጣም ኀለየ-አሰበ፣ ይኄሊ-ያስባል፣ ርእየ-አየ፣ ይሬኢ-ያያል ይላል።

በ'ተ' ሲነሳ ተኀሥየተደሰተ፣ ይትኀሠይ-ይደሰታል ይላል። በራሱ ሲገስስ ጸማሕየየ-ጠወለገ፣ ይጸማሐይይ-ይጠወልጋል፣ ይጸማሕይይ-ይጠወልግ ዘንድ፣ ይጸማሕይይ-ይጠውልግ ይላል። በ"የ" በንዑስ አንቀጹና በቦዘ መካከል ሳድስ ቀለም

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

እንጂ ሣልስ ቀለም አይገኝም ሲነገርም ርእይ ርእዮት-ማየት፣ ጸግይ ጸግዮት-ማበብ ይላል። ርእዮ-አይቶ፣ ጸግዮ-አብቦ ይላል።

- በግሱ ሁሉ "ሀ" እና "አ" በመካከል ሲገኙ የሚቀድሟቸውን ቀለማት በቀዳማይ ግእዜ፣ራብእ፣ሳድስ ያደርጋሉ። ለምሳሌ ተልዕለ፣ ተልዐለ፣ ተለዐለ፣ ተላዐለ፣ ተላዕለ ብሎ ከፍ ከፍ አለ ይላል። በአምስት መንገድ ይሄዳል። በሁለት መንገድ የሚሄድም አለ። ምሳሌ:-ወዐለ፣ ዋዐለ ብሎ ዋለ ይላል። ከአራት ቀለም በላይ ያለ ግስ ሁሉ የንኡስ አንቀጹ መካከሉ ሳድስ መድረሻው ሳብዕ ይሆናል። ምሳሌ አንቀልቀለ-ተነዋወጠ ይልና አንቀልቅሎ አንቀልቅሎት-መነዋወጥ ይላል። ሦስትም አራትም ቀለም የሆነ ግሥ በራብዕ፣ በኃምስ፣ በሳብእ ሲነሳ እንዲሁ ነው። ምሳሌ ሌለየ-ለየ ብሎ ሌልዮ ሌልዮት-መለየት ይላል።
- ሁለትም ሦስትም ቀለም ለሆነ ግስ የንዑስ አንቀጹ መካከሉ ሣልስ መድረሻው ሳድስ ነው። ምሳሌ ሖረ-ሄደ ብሎ ሐዊር ሐዊሮት መግደል ይላል። ክህለ-ቻለ ብሎ ክሂል ክሂሎት መቻል ይላል።
- በውስጥ ማሰሪያ የሚያወጡ አገባባት ፲፪ ናቸው። እኒህም በ፣ ውስተ፣ ለ፣ እስከ፣ ምስለ፣ እም፣ መንገለ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ ዘ፣ ከመ እና ኀበ ናቸው።

በ ሲያስር እግዙአብሔር በሰማይ ብሎ እግዙአብሔር በሰማይ አለ ይላል።

"ውስተ" ሲያስር ንጉሥ ውስተ ጽርሑ ብሎ ንጉሥ በአዳራሹ ውስጥ አለ ይላል።

እስከ ሲያስር ሄኖክ ወኤልያስ እስከ ይእዛ በገነት ብሎ ሄኖክና ኤልያስ በገነት እስከዚሬ አሉ ይላል።

ምስለ ሲያስር ማርያም አመ ወረደት ግብፀ ምስለ ዮሴፍ ወሰሎሜ ብሎ ማርያም ወደ ግብጽ በወረደች ጊዛ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ነበረች።

ቅድመና ድኅረ ሲያስሩ አመ ገብኡ ኢሎፍሊ ኢዮአብ ወአቢሳ ቅድመ/ድኅረ ዳዊት ብሎ ኢሎፍሊያውያን በተመለሱ ጊዛ ኢዮአብና አቢሳ በዳዊት ፊት/ኋላ ነበሩ ይላል።

ለ ሲያስር ስብሐት ለአብ ብሎ ለአብ ምስጋና ይገባል ይላል።

ዘ ሲያስር አምላክ ዘእማርያም ብሎ አምላክ ከማርያም የተገኘ ነው ይላል።

ከመ ሲያስር ሚካኤል ዘከመ አምላኩ ለርኅራኄ ብሎ ሚካኤል ለርኅራኄ እንደ አምላኩ ነው ይላል።

- ነባር አናቅጽ እንደ ዐበይት አናቅጽ እየተዘረዘሩ በሙሻ ዘር የሚወጡ አገባባትን ሁሉ ያወጣሉ። ሃይማኖት ቦቱ ለጊዮርጊስ ለእርሱ ለጊዮርጊስ ሃይማኖት አለው ይላል። ሎቱ እንደወጣ አስተውል። እምኔሁ ሲወጣ ሃይማኖት አልቦቱ ለንስጥሮስ ይላል ትርጉሙ ከእርሱ ለንስጥሮስ ሃይማኖት የለውም ይላል። እንበለ ሲወጣ ክህደት አልቦቱ ለዲያብሎስ ይላል ትርጉሙ ያለ እርሱ ለዲያብሎስ ክህደት የለውም ማለት ነው።

በእንቲኣሁ ሲወጣ አምላክ ቦቱ ለሙሴ በታቦር ይላል ትርጉሙ ስላእርሱ በታቦር ለሙሴ አምላክ አለው ይላል። እስከኔሆሙ ሲወጣ አምላክ ቦቶሙ ለአድማስ ወለናጌብ ይላል ትርጉሙ እስከ እነርሱ ለአድማስና ለናጌብ አምላክ አላቸው ይላል። ምስሌሁ ሲወጣ ዕዜራ ቦቱ ለሄኖክ በገነት ይላል ትርጉሙ ከእርሱ ጋራ በገነት ለሄኖክ ዕዜራ አለው ይላል።

- ንዑሳን አናቅጽ ሳቢ ከተሳቢ ዘርፍ ከባለቤት እየተናበቡ ፷፮ አገባባትን ያወጣሉ። አገባባቱም ለ፣ በ፣ በእንተ፣ ምስለ፣ ከመ፣ ኀበ፣ እስከ፣ እም፣ እንበለ፣ ግእዜ፣ ውስተ፣ ማእከለ፣ ላእለ፣ ታሕተ፣ የማነ፣ ፀጋመ፣ ኀበ:መንገለ:ወእደ ዘንድ ሲሆኑ፣ መጠነ፣ ጊዛ፣ ለለ፣ በበ፣ ዘዘ፣ ድኅረ፣ ቅድመ እና "ኢ" ሆኖ ሲሆን ናቸው።

አስሩን ከሙሻ ዘርፍ አይተናል። ቀሪዎቹን ቀጥለን እናሳያለን።

ድኅረ ሲገባ አፍቀረ አማኑኤል ዳዊት ንግሠተ ሐማ ሳኦል ይላል ትርጉሙ ከሐማ ሳኦል በኋላ መንገሥን አማኑኤል ዳዊት ወደደ ይላል።

መጠነ ሲገባ አፍቀረ አማኑኤል ሰሎሞን ንግሠተ ሐማ ዳዊት ይላል ትርጉሙ የሐማ ዳዊትን ያህል መንገሥን አማኑኤል ሰሎሞን ወደደ ይላል።

ቅድመ ሲገባ ፈተወ ሐማ ሳኦል ንግሠተ አማኑኤል ዳዊት ይላል ትርጉሙ ከአማኑኤል ዳዊት በፊት መንገሥን ሐማ ሳኦል ወደደ ይላል።

ላዕለ ሲገባ ገብረ አማኑኤል ስቅለተ መስቀል ይላል ትርጉሙ በመስቀል ላይ መሰቀልን አማኑኤል ወደደ።

ታሕተ ሲገባ አፍቀረ ገብር ንብረተ እግዙኡ ይላል ትርጉሙ ከጌታው በታች መቀመጥን አገልጋይ ወደደ።

ማእከለ ሲገባ ሠምረ አብ አማኑኤል ንብረተ ፈያት አበው ይላል ትርጉሙ ከአባቶች ሽፍቶች ጋር መቀመጥን አማኑኤል አባት ወደደ ይላል።

በንዑስ አንቀጽም በአምስቱ አእማድ ይህንኑ መስሎ ይሄዳል። ምሳሌ ፀጋመ ሲገባ ለኃጥዓን ቀዊመ አምላክ ይላል ትርጉሙ በአምላክ ግራ መቆም ለኃጥኣን ይገባል ማለት ነው።

ጊዜ ሲገባ አፍቀረ ጲላጦስ አስተቃትሎተቀትር አምላከ ምስለ ፈያት ይላል ትርጉሙ ከሽፍቶች ጋር አምላክን በቀትር ጊዛ ማገዳደልን ጲላጦስ ወደደ ይላል።

በሳድስ ቅጽል ሲገባ ምሳሌ የማነ ሲገባ ወልድ ንቡረ አብ ይላል ትርጉሙ በአብ ቀኝ የተቀመጠ ወልድ ማለት ነው።

ኢ ሲገባ አምላክ ምውተ ሰብእ ይላል ትርጉሙ ሰው ሆኖ የሞተ አምላክ ማለት ነው።

ረድኤተ እግዙአብሔር አይለየን።

ካፊ ግስ ክፍል ፪

- "እም" በዘንድ ሲወድቅ ሕጸቱ እንጂ ምልአቱ አይስማማውም። ይህም እምይብላእ ይላል እንጂ እምነ ይብላዕ አይልም። እስከም እንዲሁ ነው። አገባባት ሁሉ ከዘር፣ ከነባር፣ ከስም፣ ከግብር እየተናበቡ አዋጅ አያፈርሱም። "እም" ብቻ ያፈርሳል። ሲያፈርስም በሳድስ እየተናበበ ነው።

ምሳሌ እምድር ይላል። "ሰ" ቀለም ይለውጣል። ሲለውጥም አነ ያለውን አንሰ ይላል።

አገባብ ሲዘረዜር ራሱን ወደ ሣልስ ወደራብእ ወደኀምስ እየመለሰ ይዘረዘራል። "እንተ፣ዘ፣እለ" ራሳቸውን ወደ ሣልስ እየመለሱ ባዕድ ቀለም "ኣ"ን ያመጣሉ። ሲገቡም ዙኣሁ፣ እንቲኣሁ፣ እሊኣሁ ይላል። እንዲህ እያለ በአስሩም መራሕያን ይዘረዘራል።

ከመ ከአገባባት ተለይቶ በገቢር አንቀጽ ይሳባል ሲሳብም በዐቢይነቱ ነው። ምሳሌ ተነበዩ ነቢያት ከመ ይመጽእ ክርስቶስ ይላል። ነቢያት ክርስቶስ እንደሚመጣ ተነበዩ (ተናገሩ) ማለት ነው። ተነበዩ ተሳቢ ያስፈልገው ነበር 'ከመ' ስላለ ግን ተሳቢ እንደቀረ አስተውል። የሚስቡት አናቅጽ ፭ ናቸው። እነዚህም ተነበየ፣ ሰበከ፣ አእመረ፣ ጠየቀ፣ ሰምዐ፣ ገብረ እና ለበወ ናቸው።

ከነባር አናቅጽ ለከመ ውእቱን ይዝም ሳይዜም አፍዚዥነት ያላቸው ሳቢዎች አሉት። እኒህም እንጋ፣ እንዳኢ ናቸው። ሲገቡ 'ከመ' ባለቤት ይሆናል። ምሳሌ እንጋ/እንዳኢ ከመ ብዕለ ሰብእ እስመ ይሜሕር ነዳየ ወምስኪነ ይላል ትርጉሙ ሰው ባዕለ ጸጋ እንደሆነ እንጃ ለነዳይና ለምስኪን ይመጸውታልና ይላል። በዚህ ጊዜ ባለቤቱ "ከመ" ነው። ሰብእ የማንጸሪያ ባለቤት ነው። "እመ"ም እንደ ከመ ይገባል። ንጉሥ እመቦ ነበመንበሩ ንቅንት ሎቱ ይላል ትርጉሙ ንጉሥ በወንበሩ ካለ እንታጠቅለት ይላል። ንጉሥ የማንፀሪያ ባለቤት እመ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው።

"ወ" በትእዚዜና በትእዚዜ መካከል ገብቶ "ና" ይሆናል። ተንሥእ ወሑር ሲል ተነሥና ሂድ ማለት ነው።

'ሁ፣ኑ፣እንጋ' ወይ፣ን ይሆናሉ። "ሁ" እመን ሶበን ይዝ ይነገራል። "ኑ" በስምና በእርባ መካከል ይነገራል።

"እንጋ" ሁን ምን ይከተላል። ሲገቡም ዘመጽኡ ሰብአ ሰገል ሶበሁ ተወልደ ክርስቶስ ይላል ትርጉሙ ሰብአ ሰገል የመጡ ክርስቶስ ቢወለድ ነውን? /ነው ወይ? ይላል። ተወልደኑ እንጋ ይላል ትርጉሙ ተወልዶ ይሆንን ይላል።

- ዘንድ አንቀጽ 'ከመ'ን ይዝ ሳይዜም መፍትው፣ ድሎት፣ ጽድቅ፣ ፍትሕ፣ ርትዕ፣ ሥርዐት፣ ኩነት፣ ርቱዕ በማሰሪያነት ሲነገሩ ባለቤት ይሆናል። ምሳሌ መፍትው ከመ ያድኅኖ ለአዳም አምላክ ይላል ትርጉሙ አምላክ አዳምን ያድነው ዘንድ ይገባል ይላል። ያድኅኖ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አምላክ የዘንድ ባለቤት ነው።

እመ፣ሶበ፣ከመ ባለቤት ይሆናሉ። ከመ ሲገባ ተነግረ በነቢያት ወተሰብከ በሐዋርያት ከመ አንተ በአብ ወአብ ብከ ይላል ትርጉሙ አብ በአንተ አንተም በአብ እንዳለህ በሐዋርያት ተሰበከ በነቢያትም ተነገረ ይላል።

ሶበ ሲገባ እምኄሶ ለሰብእ ሶበ ይምሕር/ከመ ይምሕር ነዳየ ወይገብር ሰናየ ይላል ትርጉሙ ለሰው ለነዳያን ቢመጸውት መልካምንም ቢሰራ ይሻለው ነበር ይላል። ኄሶ በእም የታገዘ ማሰሪያ አንቀጽ ነው።

እም ደግሞ ማሰሪያ አገዝ ነው።

በመካከል ሆነው የሚቆጥሩ የሚጠቀልሉ "ህ" እና "እ" ናቸው። በዘር በነባር ይቆጥራሉ ይጠቀልላሉ።

ልዕልና ትሕትና ሲል ይጠቀልላሉ ይቆጥራሉ። ድርድሮች የወ ሳድስ የየ ራብዕ ከሆኑ ይቆጥራሉ ይጠቀልላሉ። አዕዋም፣ አውያን ይላሉ። አይቴ፣ ባሕታዊ ይቆጥራሉ ይጠቀልላሉ። "አ" በራሱ ሳድስ ተደርድሮ ድርድሩን የረ፣ የነ፣ የደ፣ የጸ ካዕብ የጸ ሳድስ የበ ራብዕ ሲቀበላቸው ይቆጥራሉ ይጠቀልላሉም። አዕጹቅ፣ አዕኑግ፣ አዕጽምት፣ አዕሩግ፣ አዕባን፣ አዕዱግ ይላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

የሀገር ስም ሰው ሲያመጣ ለሴት ለወንድ ለአንድ ለብዘ ይሆናል። ምሳሌ ወተፈሥሑ ግብፅ በጸአቶሙ ግብፆች (እስራኤላውያን) በመውጣታቸው ተደሰቱ ይላል።

በ'ወ' የጨረሰ እርባ ሳድስ ቅጽሉ ካዕብ ቀለም የለውም። ፍትው፣ ድልው፣ ውርዜው ይላል።

"ቀ፣ተ፣ደ፣ጠ፣ጸ" ከሴቲቱ ሳድስ ቅጽል ሲደርሱ ቀለማቸውን ያጠብቃሉ። ተ ሲያጠብቅ ምውት፣ ትሕት ይላል። ደ ሲያጠብቅ ዋሕድ፣ ንእድ ይላል። ጠ ሲያጠብቅ ሥልጥ ይላል። ቀ ሲያጠብቅ ጥምቅ፣ መጥምቅ ይላል። ጸ ሲያጠብቅ ሕንጽ፣ ድንግጽ ይላል።

- "ዘ" ን የሚበዘብዝ (እንዳያስር የሚያደርጉ) አገባባት ፲፫ ናቸው። እኒህም በ፣ ለ፣ እስከ፣ ምስለ፣ በእንተ፣ እም፣ ውስተ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ አመ፣ ከመ፣ ኀበ፣ እንበለ ናቸው።

በ ሲበዘብዝ በዘፈጠረነ ነአምን ይላል ትርጉሙ በፈጠረን እናምናለን ማለት ነው።

ለ ሲበዘብዝ ለዘፈጠረነ ንሰግድ ይላል ትርጉሙ ለፈጠረን እንሰግዳለን ማለት ነው።

ምስለ ሲበዘብዜ ተሰቅለ ወልድ ምስለ ዘሰረቁ ፈያት ይላል ትርጉሙ ወልድ ከሰረቁ ሽፍቶች ጋር ተሰቀለ ይላል።

በእንተ ሲበዘብዝ ሞተ አምላክ በእንተ ዘበልዐ በለሰ አዳም ይላል ትርጉሙ አዳም በለስን ስለበላ አምላክ ሞተ ይላል።

እም ሲበዘብዜ ተንሥአ ወልድ እምዘአተወ መቃብር ይላል ትርጉሙ ወልድ ከገባበት መቃብር ተነሳ ይላል።

ውስተ ሲበዘብዝ ኀደረ ንጉሥ ውስተ ዘተጎንጸ ማኅደር ይላል ትርጉሙ ንጉሥ በታነጸ ቤት ውስጥ አደረ ይላል።

ቅድመ ሲበዘብዜ ዳዊት ነግሠ ቅድመ ዘወለዶ ሰሎሞን ይላል ትርጉሙ ዳዊት ከወለደው ሰሎሞን በፊት ነገሠ ይላል።

ትምህርተ ልሳነ ግእዝ ቀዳማይ

ድኅረ ሲበዘብዜ ሰሎሞን ነግሠ ድኅረ ዘወለዶ ዳዊት ይላል ትርጉሙ ሰሎሞን ከወለደው ዳዊት በኋላ ነገሠ።

አመ ሲበዘብዜ ዐደውእስራኤል አመ ዘከፈለ ባሕረ ሙሴ ይላል ትርጉሙ እስራኤል ሙሴ ባሕርን በከፈለ ጊዛ ተሻገሩ።

ከመ ሲበዘብዜ ተሰቅለ ጴጥሮስ ከመ ዘተሰቅለት ዶርሆ ይላል ትርጉሙ ጴጥሮስ እንደተሰቀለች ዶሮ ተሰቀለ ይላል።

ኀበ ሲበዘብዜ ተፈነወ ገብርኤል ኀበ ዘተወልደት እምሐና ድንግል ይላል ትርጉሙ ገብርኤል ከሐና ወደተወለደች ድንግል ተላከ ይላል።

እንበለ ሲበዘብዜ ኢነአምን ካልአ እንበለ ዘፈጠሩ ሰማየ ወምድረ ሥላሴ ይላል ትርጉሙ ሰማይና ምድርን ከፈጠረ ሥላሴ በቀር በሌላ አናምንም ይላል።

በልዐ ኀብስቶ ለማዕዱ ለሞሶቡ ለባዕል ይላል። ይህም በ፫ ለ ማለት ነው። ትርጉሙ በልዐ ኀብስተ ማዕደ መሶበ ባዕል ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። በ፫ "ዘ"ም ይቻላል። ይሄውም በልዐ ኀብስተ ዘማዕድ ዘመሶብ ዘባዕል ይላል። ትርጉሙ የሁሉም የባዕለ ጸጋ የመሶብ የማዕድ እንጀራን በላ ማለት ነው።

ውጥን ጨራሽ ቀለማት የሚሆኑ ቀለማት ወ፣ ከመ፣ ሰ፣ መጠነ፣ ዳእሙ ናቸው። ወ ሲገባ በልዐ ኀብስተ ወመዓረ ይላል ትርጉሙ እንጀራ በላ ማርም በላ ማለት ነው። ከመ ሲገባ ዐገቱኒ ከመንህብ መዓረ ይላል ትርጉም ንብ ማርን እንደሚከብ ከበቡኝ ማለት ነው። ሰ ሲገባ አፍቅራ ለማርያም እምከ ወፈድፋደሰ ለእግዙአብሔር ይላል ትርጉሙ ድንግል ማርያም እናትህን ውደዳት ይልቁንም እግዙአብሔርን ውደደው ይላል።

ርሕቅት ማርያም እም ኃጢአት መጠነ ሰማይ እምድር ይላል ትርጉሙ ሰማይ ከምድር የራቀውን ያህል ድንግል ማርያም ከኃጢአት የራቀች ናት። ዳዕሙ ሲገባ መኑ ይትዔረዮ ለተክለሃይማኖት ዳዕሙ ገብረ ሕይወት ይላል ትርጉሙ ገብረ ሕይወት ይተካከለዋል እንጂ ተክለ ሃይማኖትን ማን ይተካከለዋል ይላል።

- ተደራራቢ አገባባት ስምንት ናቸው። እነዙህም አመ፣ ከመ፣ ድኅረ፣ ኀበ፣ ዘ፣ እስከ፣ እንዘ፣ እመ ናቸው።

አመ ሲገባ አመ አመ ሙሴ ተከፍለ ባሕር ዐደው እስራኤል ይላል ትርጉሙ በሙሴ ጊዜ ባሕር በተከፈለ ጊዜ እስራኤል ተሻገሩ ይላል።

ከመ ሲገባ ከመ ከመ ሙሴ ከፈለ ባሕረ ኤርትራ ኤዎስጣቴዎስ ከፈለ ባሕረ ኢያሪኮ ነአምን ይላል ትርጉሙ ሙሴ የኤርትራን ባሕር እንደከፈለ ኤዎስጣቴዎስም የኢያሪኮን ባሕር እንደከፈለ እናምናለን ይላል።

ኀበ ሲገባ ኀበ ኀበ ማርያም ተፈነወ ገብርኤል ተወልደ አምላክ ይላል ትርጉሙ ወደማርያም ገብርኤል ከተላከ ዘንድ አምላክ ተወለደ ይላል።

ድኅረ ሲገባ ድኅረ ድኅረ ሳኦል ነግሠ ዳዊት ተመይጠት ጽዮን ይላል ትርጉሙ ሳኦል ከነገሠ በኋላ ዳዊት ከነገሠ በኋላ ጽዮን ተመለሰች ይላል።

ዘ ሲገባ ዘዘፈቀደ ይገብር እግዙአብሔር ይላል ትርጉሙ እግዙአብሔር የወደደውን የሚሰራ ይላል።

እንዘ ሲገባ እንዘ እንዘ ይወርድ መቅሰፍት ላዕለ አሕዚብ ይሬእዩ እስራኤል ለምንት ሰቀልዎ ለአምላክ ይላል ትርጉሙ መቅሰፍት በአሕዚብ ላይ እየወረደ እያዩ እስራኤል አምላክን ለምን ሰቀሉት ይላል።

እስከ ሲገባ እስከ እስከ እግሩ ይውሕዜ ተቀብዐ ወሬዚ ዕፍረተ ይላል ትርጉሙ እስከ እግሩ እስኪፈስ ወጣት ሽቱን ተቀባ ይላል።

እመ ሲገባ ክርስቶስ እመ እመ ይምሕል ይሰቀል ድኅነ አዳም ይላል ትርጉሙ ክርስቶስ ቢምል ቢሰቀል አዳም ዳነ ይላል።

- ✓ በግዕዜ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ አቤል፣ ረዓብ፣ አዛብ፣ አሞጽ፣ ሰሎሞን ይላል። በግዕዝ በራብዕ ተነስቶ የመድረሻው ኋላ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል።ምሳሌ ሰባልዮስ፣ ባስልዮስ፣ ሰንድሮስ ይላል። በግዕዜ በራብዕ ተነስቶ የመድረሻው አጠገብ ሣልስ ሳብዕ የሆነ ስም አይነሳም። ምሳሌ አቡቀለምሲስ፣ ናብሊስ፣ ናቡከደነጾር ይላል። በግዕዝ በካዕብ ተነስቶ ድርድሩ አንድ ካዕብ፣ አንድ ራብዕ፣ አንድ ኃምስ

የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ ሱቱኤል፣ ዱማቴዎስ፣ ደማቴዎስ፣ ቡኤዜ ይላል።

- ✓ በካዕብ ተነስቶ ሁለት ደካማ ቀለም ያለበት ስም አይነሳም ምሳሌ ሩፋኤል፣ ዑራኤል፣ ሱራፌል ይላል። በሣልስ ተነስቶ ድርድሩ ሳብዕ ራብዕ የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ ኪራም፣ ሲሞን፣ ቂሮስ፣ ኢሳይያስ፣ ሲድራቅ፣ ቂርቆስ፣ ጢሞቴዎስ ይላል።
- ✓ በሣልስ ተነስቶ ሁለት ደካማ ቀለም ሲደረደር የመድረሻው ኋላ ሣልስ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም አይነሳም ምሳሌ ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል፣ ጲላጦስ፣ ሊባኖስ ይላል።
- ✓ በራብዕ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል ናባል፣ ናጌብ፣ ባሮክ፣ ባሦር፣ ሳሙኤል ይላል።
- ✓ በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ ዛውስ፣ ኔባል፣ ሜሬቅ፣ ሴኬም፣ ሴዶቅያስ፣ ቄርሎስ፣ ሄኖክ ይላል። በኃምስ በሣልስ ተነስቶ ድርድሩ ሦስት ደካማ ቀለም ያለው ስም አይነሳም ምሳሌ ሄሮድስ፣ ኢያቄም ይላል። በግእዜ በራብዕ በሳድስ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ ኃምስ ሳድስ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ ግያዜ፣ ብርያል፣ ብልዮስ፣ ግዮን፣ ገብርኤል፣ አቤሴሎም፣ እለእስክንድሮስ ይላል።
- ✓ በሳድስ ተነስቶ በመካከሉ ሦስት ደካማ ሲሆን አይነሳም ምሳሌ እግዙአብሔር፣ እስጢፋኖስ ይላል። ፍጹም ሳድስ የሆነ ስም አይነሳም ምሳሌ እስክንድር፣ ግብጽ፣ ቅምር ይላል።
- ✓ በሳብዕ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ ኃምስ ሳብዕ የሆነ ስም ይነሳል ምሳሌ ቶማስ፣ ሮቤል፣ ሶፎር፣ ኮቦር ይላል። ሁለት ቀለም የሆነ ስም አይነሳም ምሳሌ ሴም፣ ካም፣ ኖብ፣ ኖኅ ይላል። ደካማ ቀለማት የሚባሉት ካዕብ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ናቸው።

- ➢ የሚበዳደሩ ቀለማት ስምንት ናቸው እነዙህም ጐ፣ ቈ፣ ኰ፣ ጕ፣ ኀ፣ ቀ፣ ከ፣ ገ ናቸው። ለምሳሌ ከ ሲበደር ተኬነወ-ብልሀት ሰራ ብሎ ኵናት ይወጣል። ኰ ሲበደር ለሐኰ-ፈጠረ ብሎ ለሐኩ-ፈጠረው ይላል።

- ሌሎችም እንዲሁ ነው።በኃምስ በሣልስ የሚነሱ ዘርና ነባር በአመል ሲረቡ ሣልሱን ኃምሱን ሳድስ ያለ አመል ሲረቡ ግእዜ እያደረጉ የየን ራብዕ ያመጣሉ። በአመል ቤዜ-ኮከብ ብሎ አብያዜ-ኮከቦች ይላል። ቢጽባልንጅራ ብሎ አብያጽ ባልንጀራዎች ይሆናል። ያለ አመል ቴፈን-ወይፈን ብሎ ተያፍን-ወይፈኖች ይላል።
- ሌሊት-ሌሊት ብሎ ሲበዚ ለያልይ ይላል። "የ" በራሱ ግስ ከሴቲቱ ውስጠዘ ሲታጣ ሳድሱን በሣልስ ይጎርዳል። ይሄውም ተርእየት፣ ተሴሰየት፣ ውዕየት ፣ ተላጸየት ካለው ግሥ ሉጺት፣ ርኢት፣ ሲሲት፣ ውዒት ይወጣል።
- በቀተለ ቤት በወ ተነስቶ በማናቸውም ሲደርስ መስም ቅጽሉ ይጠብቃል መነሻው አይፈርስም። መወልድ መወርድ ማለቱን ያሳያል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።